በኢትዮጵያ ብሔራዊ የወሰን ክልል ውስጥ በተዘጋጀው የጋሻ መደብ ላይ የሕብረተሰቡን የተለያዩ ማኅበራዊ ክፍሎችንና ታሪካዊ ገፅታዎችን የሚያሳየው የመጽሐፉ የፊት ሽፋን በግራፊክ አርቲስት ምናሴ መላኩ እንዲሁም የአገሪቱ የቀድሞው የጠቅላይ ግዛትና የዛሬው የሪፐብሊኩ ክልል ካርታዎች በገፅ 300—301 በካርቶግራፈር ዳንኤል ሰይፉ የተዘጋጁት በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት ነው ።

# የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም

## 1900 - 1966


ሁለተኛ መጽሐፍ

To my first and best teacher Bedford Lapsely with my best wishes
11/4/91

ከ

ዶክተር ላጵሶ ጌ. ድሌቦ

አዲስ አበባ
1983



ደራሲው ላጵሶ ጌ· ድሌቦ

# ማውጫ

ገጽ

መቅድም ........................................................ 15

## ክፍል አንድ

## የገባር ሥርዓት ዕድገትና ውድቀት

1900 —1933

ምዕራፍ 1

ማዕከላዊው መንግሥትና የገባሩ ሥርዓት ........................ 19

የማዕከላዊው መንግሥት የምዕክልና ሂደት ........... 19

የጉልተኛው መደብ ........................................ 28

የጉልተኛው መደብ ታሪካዊ መነሻ .............. 28

የኃይለ ሥላሴ ሥርወ መንግሥት መነሻና ሚና ... 31

የመሳፍንት የሹመትና የጉልት መብት ........... 32

የገባሩ መደብ ........................................ 33

የገባርና የጢሰኛ አንድነትና ልዩነት .............. 33

የገባር ሕግና ሥራ ........................................ 33

የጢሰኛ ሕግና ሥራ ........................................ 36

የባርያ ሥራና ንግድ ........................................ 39

ምዕራፍ 2

ብሔራዊ ኢንቴሌጄንሲያውና የገባሩ ሥርዓት .................... 41

የገባር ሥርዓትና የካፒሊታሊዝም ቅራኔ .................. 41

የአፈወርቅ ገብረኢየሱስ ትምህርት .................... 43

የአስቤ ኃይሉ ትምህርት ................................ 47

የገብረሕይወት ባይከዳኝ ትምህርት .................... 50

የደሬሳ አመንቴ ትምህርት ............................. 56

የጃፓን ያገር ግምባታ ሞዴልና ልምድ ለኢትዮጵያ ...... 62

የዘመነ ገባር ፍጻሜ ........................................ 67

ምዕራፍ 3

የ1928 —1933 ጦርነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ውጤቶች ........ 67

## ክፍል ሁለት

## የጅምር ካፒታሊዝም ላዕላይ መዋቅር

1933 - 1966


ምዕራፍ 1

ፍጹማዊው የዘውድ ሥርዓት ምዕክልና ... 75

- የመንግሥት አደረጃጀትና አገልግሎት ... 75
- የላዕላይ መዋቅር ግምባታ ... 79
- የቢሮክራሲ ግምባታ ... 83
- የመንግሥት ሥራና ገንዘብ ... 85

ምዕራፍ 2

የሃይማኖት የትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ ... 90

- የሃይማኖት ፖሊሲ ... 90
- የትምህርት ፖሊሲ ... 95
  - የመንግሥት ትምህርት ... 95
  - የሚሲዮን ትምህርት ... 106
- የቋንቋ ፖሊሲ ... 111

ምዕራፍ 3

የኢትዮጵያ መንግሥት ቋንቋ ... 111

- የቋንቋ ሳይንሳዊ ግንዛቤ ... 111
- የኢትዮጵያ መንግሥት ቋንቋ ... 116
- በአገው ዘመነ መንግሥት የአማርኛ ቋንቋ ክስተት ... 119
- የአማራ ማህበረሰብ ዕድገት ... 120
- የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ዕድገትና አገልግሎት ... 122
- ማጠቃለያ ... 127

ምዕራፍ 4

የሥርዓት አመፅና ቅጣት ... 129

- የእንግሊዝ ወታደራዊ ግዛት በኢትዮጵያ ... 129
- አዲሱ የአስተዳደር ሥርዓት ... 132
- የጐጃም አመፅ ... 133
- የትግራይ አመፅ ... 136
- የአመፅ ውጤት በሰሜን ኢትዮጵያ ... 146
  - የፖሊሲ ለውጥና የልማት ጥያቄ ... 146
  - የአዘቦና የራያ ቅጣት ... 148
- የአደሬ አመፅ ... 154

ምዕራፍ 5

የጌዴኦ የመሬት ሙግትና አመፅ ... 161

- የምሥራቅ ደጋው ኩሻውያን ... 161
- የጌዴኦ ጥንታዊ ታሪክ ... 164
- የገባር ሥርዓት በሲዳሞ ... 166
- የጌዴኦ የመሬት ጥያቄ 1882 - 1952 ... 169
- የጌዴኦ የምችሌ ጦርነት ... 173

ምዕራፍ 6

የባሌ የመሬት ውርስና አመፅ ... 180

- የባሌ ሕዝብና ታሪክ ... 180
- የገባር ሥርዓት በባሌ 1882 — 1955 ... 182
- የባሌ የ1955 — 1962 አመፅ ... 187

ምዕራፍ 7

የጉራጌ በሀወርታዊ ሕብረተሰብ ዕድገት ... 190

- የጉራጌ ሕዝብና ታሪክ ... 190
- የጉራጌ ጦርነት 1867 — 1881 ... 192
- የገባር ሥርዓት በጉራጌ ... 194
- ጉራጌ በአዲስ አበባ ... 197

ምዕራፍ 8

የደቡብ ኢትዮጵያ የዕድገት ሂደትና ኃይሎች ... 199

ምዕራፍ 9

የውጭ ኃይሎች ተፅዕና ... 204

- የውጭ አገር እርዳታ ... 204
- የጦር ድርጅት ... 205
- የጸጥታ ድርጅት ... 209
- የንጉሡ ልዩ ካቢኔ ... 211
- የ1953 አመጽ ታሪካዊ መነሻ ... 213


## ክፍል ሦስት

## የጅምር ካፒታሊዝም ታህታይ መዋቅር

1933 — 1966


ምዕራፍ 1

የኢኮኖሚ አደረጃጀትና አገልግሎት ... 215

- የታህታይ መዋቅር ግምባታ ... 215
- እርሻና የመሬት ግብር ... 219
- የመሬት ይዞታና የአርሶ አደሩ ሕይወት ... 222
- የቡና ምርትና ብሔራዊ የውጭ ምንዛሪ ... 228

ዕደ ጥበብ ............ 230
ንግድ ............ 232
ኢንዱስትሪ ............ 236
~~የውጭ አገር ካፒታል ሚና~~ ............ 239
የወዛደሩ ሥራና ሕይወት ............ 251
የወዛደሩ ታሪካዊ መነሻና ዕድገት ............ 251
የወንጂ ወዛደር የሥራና የኑሮ ሁኔታ ............ 253
ምዕራፍ 2
በጥገኛ ሥርዓት የማህበራዊ ዕድገት ሁኔታ ............ 259

## ክፍል አራት

## አብዮታዊ የሕዝብ አመፅ

## 1953 — 1966

ምዕራፍ 1
የሕዝብ አመፅ ............ 264
የሕዝብና የከተማ ዕድገት ............ 264
የአርሶ አደሮችና የብሔረሰቦች አመጽ ............ 269
የወዛደሮች አመፅ ............ 273
የወዛደሩ ብሔራዊ ዕድገትና ስርጭት ............ 273
የወዛደሩ የትግል ስልትና ድል ............ 273
የወታደሮች አመፅ ............ 276
ምዕራፍ 2
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ............ 279
የተማሪዎች አመፅ ............ 279
የተማሪዎች አብዮታዊ ትምህርት ............ 279
የተማሪዎች እንቅስቃሴና የኤርትራ ተገንጣዮች ............ 281
የተማሪዎች እንቅሲቃሴ የትግል ስልትና ውጤት ............ 285
በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ የአንጃዎች ክስተት ... 286
ምዕራፍ 3
የአብዮቱ ፍንዳታ ............ 289
የመንግሥቱ የቅጣት እርምጃ ............ 289
የተማሪዎች አመፅ በገጠር ............ 291
የመምህራን አመፅ ............ 292
የኢመማ የደሞዝና የትምህርት ጥያቄ ............ 293
የደሞዝ ጥያቄ ............ 294
የሥርዓተ ትምህርት ጥያቄ ............ 294
የኢመማ ታሪካዊ ትግል በአጼው መጨረሻ ችሎት ............ 295
የአብዮቱ የየካቲት 1966 ፍንዳታ ............ 298



# ፎቶግራፍ

ገጽ
ደራሲው ............ 3
1. አጼ ቴዎድሮስ (1811 —1960) ............ 19
2. አጼ ዮሐንስ (1823 —1881 ) ............ 20
3. አጼ ምኒልክ(1836 —1906 )፣ ............ 22
4. የኢትዮጵያ ሠራዊት በዘመቻ ስምሪት በ1887 ............ 25
5. ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ (1837 —1905 ) ............ 27
6. ወህኒአዛዥ ወልደጻድቅ (1831 —1901 ) ............ 31
7. የሐረሩ ኤሚር አብዱላሂ (1835 —1910ዎቹ) ............ 34
8. የከፋው ታቶ ጋኪ ሼሮቾ (1850 —1912፡) ............ 38
9. የወላይታው ካዎ ጦና ጋጋ (1861 —1901 ) ............ 40
10. የጂማው አባጅፋር አባጉመል (1853-1925) ............ 45
11. የወለጋው፡ደጃዝማች ገብረእግዚአብሔር ሞሮዳ (1864 —1916 ) 49
12. የቤኒሻንጉሉ ሆጃሌ አልሀሰን (1818 —1930 ) ............ 53
13. የአፋሩ አቡበከር (1808 —1879 ) ............ 55
14. የሶማሌው ኡጋዝ ሮቢሌ ፋራሂ በ1870ዎቹ ............ 58
15. አፈወርቅ ገብረየሱስ (1860 —1939፥) ............ 61
16. ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ (1877 —1911 ) ............ 64
17. የገባር አገልግሎት በ1870ዎቹ በሸዋ ............ 66
18. አቡነ ማቴዎስ (1837 —1910) ............ 78
19. የሀዲያ ሴት ጥንታዊ አለባበስና የጸጉር አሠራር ............ 89
20. የሐረር ካቶሊክ ሚሲዮን ትምህርት በ1900 ............ 106
21. ሰብሮ ዎሮሮ ሹጉጤ ዳዳና አባጉሌ ኑነሞ በ1972 ............ 109
22. ራስ፡አሉላ አባነጋ (1833 —1891 ) ............ 144
23. የአደሬ ጥንታዊ አለባበስና የከተሜ ባህል በ1840ዎቹ ............ 156
24. የዝሆን ጥርስ ምርትና ንግድ በ1910ዎቹ ............ 165
25. ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ (1855 —1928 ) ............ 178
26. ራስ ጉበና (1814 —1881 ) ............ 193
27. የጉራጌው ሼክ ኢሳ ሐምዛ (1855-1941) ............ 196
28. ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ (1844 —1919 ) ............ 197
29. አለቃ አጥመጊዮርጊስ ገብረ መሲህ (1825 —1907 ) ............ 198
30. የሀዲያ ጥንታዊ ለቅሶ ሥነሥርዓት በ1920 ............ 203

31. በአንደራቻ መዲና አካባቢ በሾሻ ተራራ የወግና የክብር ዕቃ የሚገኝበት የከፋ ነገሥታት የመቃብር ላይ ሐውልት ......... 214
32. አፈ ንጉሥ ነሲቡ መስቀሎ ......... 219
33. ጥንታዊ የቡና እርሻ በሐረር በ1870ዎቹ ......... 227
34. የወንጂ — ሸዋ የሸንኮራ አገዳ እርሻ በ1956 ......... 251

# ሰንጠረዥ

1. በ1928 — 1932 በኢትዮጵያ በፋሽቶች የተሰራ የመንገድና የድልድይ ሥራ ብዛትና ወጪ በሊራ ......... 68
2. በ1928 — 1933 በፀረ ፋሽስት ጦርነት በልዩ ልዩ ግምባሮች የተሳተፉ የኤርትራ ተወላጆች ......... 72
3. በድህረ ጦርነት በኢትዮጵያ ያገር ግምባታ ተግባር የኤርትራ ተወላጆች በልዩ ልዩ መስኮችና ደረጃዎች......... 73
4. የኢትዮጵያ የ1938 የመንግሥት ገንዘብ ገቢና ወጪ በሚሊዮን ብር ......... 86
5. በ1940 የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የአስተዳደር ሹማምንቶች ብዛት ......... 87
6. በ1940ዎቹ የአስተዳደር ሹማምንቶች የደሞዝ ናሙና ......... 87
7. በ1940 የአገር ግዛት ሚኒስትር ሹማምንቶች ብዛትና ደሞዝ ......... 88
8. እ.አ.አ . በ1865 — 1900 የኢትዮጵያ በምኒልክ አመራር ሥር የሆኑት አካባቢዎች ......... 94
9. እ.አ.አ. በ1900 — 1934 የኢትዮጵያ በዓለም ገበያ የተሸጠ የዝሆን ጥርስ ከጋምቤላ በኪሎግራም ......... 94
10. በ1957 በክፍለ ሀገር የኢትዮጵያ የአብያተ ክርስቲያናት ስርጭትና የቦታ ይዞታ ......... 102
11. ተዛማጅ አሞአዊ የጋሞ — ወላይታ የቋንቋ ማህበረሰቦች ሊንጉዊስቲካዊ የቃላት ግንኙነት ከመቶ፣ ......... 109
12. ተዛማጅ ኩሻዊ የሀዲያ ሲዳማ የቋንቋ ማህበረሰቦች ሊንጉዊስቲ ካዊ የቃላት ግንኙነት ከመቶ ......... 109
13. በ1973 ፣ በ1982 የኢትዮጵያ የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ምዕመናን ብዛት በከፊል ......... 110



14. በ1817 — 1937 የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር መጽሐፍ ቅዱስን ያሳተመባቸው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች 112
15. በ1900 ፣ በ1945 ፣ በ1976 በአዲስ አበባ የብሔረሰብና የቋንቋ ጥንቅርና መስተጋብር ......... 124
16. በ1900 ፣ በ1945 ፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ የሙያና ማህበራዊ ጥንቅር ......... 124
17. በ1877 የሐረር ኤሚሪያት የሕዝብ ብዛትና ጥንቅር ......... 154
18. የምሥራቅ ደጋው ኩሻዊ ማህበረሰቦች ሊንጉስቲካዊ የቃላት ግንኙነት ከመቶ ......... 161
19. በ1976 የምሥራቅ ደጋው ኩሻውያን የሕዝብ ብዛትና የመሬት ስፋት ......... 161
20. በ1894 — 1927 በጅቡቲ በር የኢትዮጵያ፡ወደ ዓለም ገበያ የተላኩ የዝሆን ጥርስ በኪሎግራም ......... 163
21. የሲዳሞ ሰፋሪዎች የመነሻ ምንጭና ብዛት ከመቶ......... 168
22. የሲዳሞ አስገባሪዎችና ገባሮች በ1882 - 1966 ......... 179
23. በ14ኛው ምዕተ ዓመት የባሌ ሱልጣኔት የመሬት ስፋትና የጦር ብዛት ከአጎራባች ሱልጣኔቶች ጋር በንጽጽር ......... 180
24. በ1954 — 1959 የባሌ የጋሻ ቀላድና ውዝፍ የመሬት ግብር 184
25. በ1962 የባሌ የጋሻ መሬት ይዞታ ዓይነትና መጠን በጋሻና ከመቶ ......... 186
26. በ1946 — 1956 የባሌ ውዝፍ የመሬት ግብርና የተወረሰ መሬት 186
27. በ1950 ከውጭ የአማካሪዎች ቡድን የቀረበ የፖለቲካ መዋቅር 212
28. የኢትዮጵያ የ1927 የገንዘብ ገቢና ወጪ በሚሊዮን ብር ...... 216
29. የኢትዮጵያ የገጠር መሬት ይዞታና ግብር በጥቅል 1933—1966 220
30. በ1960 በየክፍለ ሀገሩ የአርሶ አደሩ የመሬት ማሳ ዓይነትና መጠን ከመቶ......... 223
31. በ1960 በየክፍለ ሀገሩ የአርሶ አደሩ የማሳ ስፋት ከመቶ ......... 224
32. በ1960 በየክፍለ ሀገሩ የታረሰ ማሳ ስፋት በሄክታር ......... 225
33. በ1960 የኢትዮጵያ በከተማ የሚኖሩ የገጠር ጉልተኞች ብዛት በየክፍለ ሀገሩ ......... 226
34. በ1955 — በ1966 በየዓመቱ በመንግሥት አካል ተመርምሮ ለገበያ የቀረበ የቡና ምርት መጠን በቶን ......... 220
35 ወደ ዓለም ገበያ ለሚላኩ የእርሻ የደንና የዱር ምርቶች ባንክ ከሚፈቅደው የውጭ ምንዛሪ የቡና ድርሻ ......... 230
36. በ1940 — 1966 የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ሚዛን በሚሊዮን ብር ......... 233

37. በኖሙና ዓመታት የኢትዮጵያ መንግሥት የገንዘብ ገቢ ዓይነትና መጠን በሚሊዮን ብር ........................ 234
38. በ1950 — 1966 የኢትዮጵያ መንግሥት የአገር ውስጥ የገንዘብ ገቢና ወጪ ሚዛን በሚሊዮን ብር .................... 236
39. በአብዮቱ ዋዜማ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት በዓይነትና በመጠን ...................................... 237
40. በ1953 በተሠራበት መደበኛ ዋጋ የተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ለጠቅላላ ያገር ውስጥ ምርት አስተዋጽኦ በብርና ከመቶ ......... 238
41. በ1958 በተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች የውጭ አገር የግል ካፒታል ስርጭትና መጠን ...................................... 242
42. ከጠቅላላ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የምግብና የጨርቃ ጨርርቅ ፋብሪካዎች የካፒታል የሠራተኛና የምርት ድርሻ ...... 243
43. በ1962 አንዳንድ በኢትዮጵያ የሚሠሩ የኢንዱስትሪ ዕቃዎችን የሚወዳደሩ ተመሳሳይ ዕቃዎች ከውጭ አገር እንዳይገቡ ለማድረግ የወጣ የታሪፍ ዋጋ ከመቶ ........................... 247
44. በ1964 በ273 የኢንዲዱስትሪ ድርጅቶች ውስጥ የውጭ አገር ሠራተኞች ብዘትና ደሞዝ ...................................... 248
45. ከጠቅላላ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ደሞዝ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሠሩ የውጭ ዜጐች ድርሻ ................ 248
46. በ1966 በኢትዮጵያ በመንግሥትና በግል ፋብሪካዎች ውስጥ የውጭ አገር ሠራተኞች ብዛትና ደሞዝ ......................... 249
47. በ1958 በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች የክፍለ ሀገር ስርጭት................................................................ 250
48. በአብዮቱ ዋዜማ የኢንዱስትሪና የመንግሥት ሠራተኞች ብዛትና ደሞዝ በንጽጽር .............................................. 252
49. በ1947—1966 የኢትዮጵያ የስኳር ኢንዱስትሪ ምርት በቶንና በኩንታል ................................................... 258
50. በአብዮቱ ዋዜማ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዕድገትና ብዛት በጥቅል 263
51. በ1969 የገበሬና የከተማ ማህበራት ስታትስቲክስና በ1976 የሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት በ1966 የሕዝብ ብዛት ግምት 265
52. በአብዮቱ ዋዜማ በኢትዮጵያ ዋና ዋና የአስተዳደርና የንግድ ከተሞች የሕዝብ ብዛት ............................................ 257
53. በ1955—1966 የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር የቅ ርን ጫፍ ማህበራትና አባላት ..................................... 276
54. በ1976 አማርኛ ተናጋሪ ቤተሰብ ብዛት በከተማና በገጠር ... 312



# ካርታ

1. የተድሞ የጠቅላይ ግዛት ካርታ በ1966 ........................ 300
2. የሪፐብሊኩ ክልል ካርታ በ1980 ............................ 301

# መረጃና ማስታወሻ

1. የግርጌ ማስታወሻ ................................ 303

2. የታሪክ የመረጃ ምንጮች ........................ 325

# መቅድም

በድህረ አብዮት የኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ እስካሁን በተገኙትና በታወቁት የፓሌአንቶሎጂ ፣ የአርኪኦሎጂ ፣ የትውፊትና ፣ የስነልሳን መረጃዎች መሠረት ፣ የሕዝብ ታሪክ ፤ የመንግሥት ታሪክ ፣ የአብዮት ታሪክ ፣ የሪፐብሊክ ታሪክ ተብሎ በሥፍራ ፣ በጊዜና በተግባር እንደሰንሰለት በተያያዙ ፈርጆች በጥናት ተገናዝቦ ሊቀርብ ይችላል ። ካሁን በፊት የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ አንደኛ መጽሐፍ በሚል ርዕስ ባቀረብኩት ጥናት በተለይ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በሚመለከት ከጥንት እስከ 1900 ድረስ በዘመናዊ የታሪክ ጥናት ስልትና ቅንብር ተዘጋጅቶ ቀርቧል ።

ይህ “ የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም ” ሁለተኛ መጽሐፍ በሚል ርዕስ ያቀረብኩት ታሪክ ደግሞ የመጀመሪያው መጽሐፍ ከቆመበት ከ1900 እስከ 1966 ድረስ ለታላቁ አብዮት ታሪካዊ መነሻ የሆኑ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችንና ኃይሎችን በሥፍራና በጊዜ ያገናዘበ ጥናት ነው ።

በጥናቱ ይዘትና ሂደት በዝርዝር እንደተገለጸው ፣ የታላቁ አብዮት ታሪካዊ መነሻ የተጠነሰሰው በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ከ1850 እስከ 1900 ድረስ ለጥንታዊውና በሀውርታዊው የአጼ መንግሥት የፖለቲካ ምዕክልና ከውስጥና ከውጭ ተጻራሪ ኃይሎች ጋር በተካሄደው ብሔራዊ የአንድነት ትግል ሂደት ነው ።

በዚህ ረጅምና መራራ የትግል ዘመን በአንድ በኩል በአገሪቱ በሰሜንና በምስራቅ የባህር ጠረፎች አራት እስትራቴጂያዊ አካባቢዎች “ ኤርትራ ” ፤ “ የፈረንሳይ ሶማሊያ ላንድ ” ፣ “ የእንግሊዝ ሶማሊያ ላንድ ” እና “ የኢጣሊያ ሶማሊያ ላንድ ” ተብለው ከአያሌ ብሔረሰቦችና ማህበረሰቦች ጋር በፈረንሳይ ፣ በእንግሊዝና በኢጣሊያ ኢምፔሪያሊስቶች በቀጥታ ተያዙ ። የተጠቀሱት የውጭ ኃይሎች ለረጅም ጊዜ የአገሪቱን ጠረፎች በቀለበት ከበው በኢትዮጵያ ብሔራዊና ማህበራዊ የዕድገት አቅጣጫና ጉዳና ላይ በፖለቲካ ፣ በእስትራቴጂ በኤኮኖሚና ፣ በባህል ከባድ ጂኦፖለቲካዊ ተፅዕና አሳደሩ ።

በሌላ በኩል ከውጪ ዓለም ጋር የሚገናኙባቸው የቀይ ባህርና
የአባይ ሸለቆ ብሔራዊ የጠረፍ አካባቢዎቹና በሮቹ በተጻራሪ የውጭ
ኃይሎች ለተያዙበት ለኢትዮጵያ መንግሥት ለአገር ግምባታ የሚያ
ስፈልጉ ዘመናዊ የትምህርት ፣ የሳይንስ ፣ የቴክኖሎጂ ፣ የመገናኛ ፣ የከ
ተማ ፣ የንግድ ፣ የገንዘብ ፣ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የባህል ድርጅቶች ፣
አሳቦችና ሥራዎች በነጻ የሚያድጉበትና የሚስፋፉበት አመቺ ሁኔታ አል
ተፈጠረም ። በመሆኑም የአገሪቱ ጥንታዊ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች
በአገር አቀፍ ደረጃ የበለጠ ተስፋፉ ። በገባር ሥርዓትና ኢኮኖሚ የተደ
ራጀ ብሎም ዘመናዊ ትምህርትና አዲስ የፖለቲካ አሳቦችን የሚቃረን
በነገሥታት ፣ በመሳፍንቶችና በጦር አለቆች ኃይልና ሕብረት የሚመ
ራው ጉልተኛ የገዥው መደብ በአምራቹ የገባር መደብ ላይ የፖለቲካ
በላይነቱን አረጋገጠ ። በአንጻሩ በጉልተኛ የገዥው መደብ ሥር በአ
ገሪቱ ማህበራዊ ለውጥና ዕድገት የሚፈልጉ አዳጊና ብሔራዊ የኢን
ቴሌጀንሲያውና የነጋዴው ወገኖች ከመንግሥት ሥልጣንና ተግባር
ተገለሉ ። ባጭሩ የመንግሥት ሥልጣንና የፖለቲካ አመራር ማህበራዊ
ለውጥና ዕድገት በተግባር በሚጻረረው ጉልተኛ የገዥው መደብ እጅ ሆኖ
የአገር ግምባታ እርምጃና ሂደት ለረጅም ጊዜ ተገታ ። በሥፍራና በጊዜ
በማያቋርጥ በነገሥታቱና በመሳፍንቱ የሥልጣን ጦርነት በአገሪቱ ላይ
በሕይወትና በንብረት ታላቅ ጥፋት ተፈጸመ ። የገባር ፣ የባርያ ፣ የብሔ
ረሰብ ፣ የሃይማኖት ፣ የቋንቋ ፣ የትምህርት ፣ የመሬትና የአገር መከላ
ከል ጉዳዮች የአገሪቱ መሰረታዊ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የሥርዓት
ችግሮች ሆኑ ።

በመጨረሻ በ1928 — 1933 ጦርነት የአገሪቱ ጥንታዊ የገባርና
የባርያ ሥርዓቶች በአካባቢ ኢኮኖሚና ጦር ከተደራጁ ጉልተኛ የክፍለ
ሀገር መሳፍንቶችና የጦር አበጋዞች ጋር ተደመሰሱ ። በኋላ በድህረ
ጦርነት ከ1933 እስከ 1966 ድረስ በአዲሱ የኃይለ ሥላሴ ሥርወ መን
ግሥት አመራር ፍጹማዊው የዘውድ ሥርዓትና ሥልጣን ምዕከልና ፣
አዲስ የመንግሥትና የኢኮኖሚ አደረጃጀት እንዲሁም የአገሪቱ የውጭ
አገር የኢኮኖሚ እርዳታና የፖለቲካ ተጽዕኖ እንዴት እያደገ እንደመጣ
በጥናቱ ይዘት በዝርዝር ይታያል ።

በተጠቀሰው የፖለቲካ ሥርዓትና የሽግግር ዘመን የኢትዮጵያ የዘ
ውዳዊ መንግሥት የኢኮኖሚ ታህታይ መዋቅርና የፖለቲካ ላዕላይ መዋ
ቅር ከስልተ ምርትና ሥርዓተ ማህበር ዕድገት አኳያ ሳይጣጣሙ ቀሩ ።
የኢኮኖሚው መሰረት የፖለቲካና ማህበራዊ መዋቅርን መሸከም አቃ
ተው ። ባጭሩ አንዱ ለሌላው ማህበራዊ ዕድገት ውስጣዊ የሥርዓት ፣
የፖለቲካና ፣ የኢኮኖሚ እንቅፋት ሆነ ። የገዥውና የሰርቶ አደሩ መደ
ቦች ሥርዓታዊ ልዩነትና ቅራኔ በሕግና በአስተዳደራዊ ለውጥ ወደማይ



ታረቅበትና ወደማይፈታበት ከፍተኛ የውድቀት ደረጃ ደረሰ ። በተ
ጨማሪም የውጭ ኃይሎች የኢኮኖሚ ግፊትና የፖለቲካ ተጽዕኖ የሥር
ዓቱን አብዮታዊ ፍጻሜ የበለጠ አፋጠኑት ።

ይህ የሥርዓቱ የታህታይና የላዕላይ መዋቅሮች ቅራኔና ግጭት የኢት
ዮጵያን ሕብረተሰብ በሥርዓቱና በውጭ ኃይሎች ተጽዕኖ ላይ በአብዮ
ታዊ አመጽ አስነሳ ። በዚህ ሥርዓታዊ የመደቦች ቅራኔና ግጭት ሂደት
የሕብረተሰቡ የተለያዩ የአመጽ ኃይሎች ማለትም የአርሶ አደሮች ፣
የብሔረሰቦች ፣ የማህበረሰቦች ፣ የወዛደሮች ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ፣
የከተማ ነዋሪዎች ፣ የወታደሮች ፣ የተማሪዎችና የመምህራን ታሪካ
ዊና ማህበራዊ ዕድገት ፣ ድርጅትና የአመጽ እንቅስቃሴ እስከ የካቲት
1966 ሕዝባዊ አብዮት ድረስ በጥናቱ ይዘትና ሂደት ፈርጅ በፈርጅ ተዘ
ርዝረው ቀርበዋል ።

ከትምህርታዊ ግንዛቤ አኳያ ደግሞ ጥናቱ በአብዮቱ ዋዜማ ፣ ፍንዳ
ታና ሂደት በልዩ ልዩ መልክ ፣ የተነሱ የፖለቲካ ኃይሎችን፣ ቡድኖችንና
ተዋንያንን ታሪካዊ መነሻ እንዲሁም አብዮቱ በኢትዮጵያ በሀውርታዊ
ሕብረተሰብ ዘንድ በተለያዩ ታሪካዊ አካባቢዎችና ማህበራዊ ክልሎች
ማለትም በከተማ ፣ በገጠር ፣ በመሥሪያ ቤት ፣ በፋብሪካ ፣ በዶቡብ ፣
በመሀል ሰሜንና በኤርትራ ክፍላተ ሀገር የሚያስከትለውን አንጻራዊ
ሁኔታና ሂደት ለማጥናትና ለማወቅ ለሚፈልግ የታሪክ ተማሪና አንባቢ
የሚያገለግል የመረጃ ፣ የስልትና የግንዛቤ መጽሐፍ ነው ። የመሬትን
ይዞታ ፣ የመንግሥትን የገንዘብና የግብር ፖሊሲ ፣ የንግድ ፣ የኢንዱስት
ሪና የትምህርት ሥራዎችንና ድርጅቶችን ዕድገትና መስተጋብር በሚመ
ለከት በመጽሐፉ በሰንጠረዥ የቀረቡ ሰፊና ዝርዝር መረጃዎች የታሪኩ
መሠረታዊ የትምህርት ምንጮች ናቸው ። ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል
ጥናቱ በስልት ሆነ በይዘት ፍጹማዊነት የለውም ። ለተጨማሪ ጥናት
የሚቀሰቅስ የሚጋብዝ ሥራ ነው ።

በመጨረሻም የሥራ አስተዋጽኦና ምስጋና በሚመለከት ፣ ከ1953
ታሪካዊው ኩዴታ ወይም የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ወዲህ በተከ
ታታይ አሥርታት የትምህርት ፣ የጥናትና የሥራ ዘመን በአገር ውስጥና
በውጭ አገር ለዚህ የጥናት ሥራዬ ዝግጅትና መሳካት ጉልህ የስልት ፣
የመረጃና የግንዛቤ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሁኔታዎች ሰዎች የትምህርትና
የባህል ተቋማት ፣ የሙያና የሥራ ባልደረቦች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶ
ችና ሠራተኞች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው ።

ከእነዚህ ጥቂቱን ብቻ ለማስታወስ ያህል ፣ በ1958 ለከፍተኛ ትም
ህርት ወደ አሜሪካ ከመሄዴ በፊት የአገሪቱን የመሬት ፣ የአርሶአደር ፣
የብሔረሰቦችና የሠራተኞች ሥርዓታዊ ችግር በሚመለከት በ1950ዎቹ

የጻፍኩትን ጅምር የታሪክ ጥናት ረቂቅ በውጭ አገር ከፍተኛ ትምህርት ጨርሼ በ1968 ወደ አገሬ እስከመለስ ድረስ በአደራ ያቆየችልኝ ታናሽ እህቴ ወይዘሮ እቴነሽ ድሌቦ ነች ። የጅሌ ነባር ማህበረሰብ ከወንጂ ሚዳው በሆላንዳዊው ዓለም አቀፍ የስኳር ኩባንያ ከመባረሩ በፊት የነበረውን የማህበረሰቡን ጥንታዊ ታሪክና የገዳ ሥርዓት በአካባቢው በነበርኩበት ዘመን በዝርዝር ያስተማሩኝ ባአንድ የማህበረሰቡ አዛውንት በአቶ ከለቻ ደንቤ አስተባባሪነት የማህበረሰቡ ታዋቂ ሽማግሌዎች ናቸው ። የተባለው ኩባንያ በጅሌ ነባር ማህበረሰብና በወንጂ ሠራተኞች ላይ የፈጸመው ታላቅ የጥፋትና የብዝበዛ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ጥናት በስፋት ቀርቧል ።

የኢትዮጵያ የመሬትና የአርሶአደሩን መሰረታዊ የሥርዓት ችግር በሚመለከት ፣ እንዲሁም የአርሶአደሮችን ፣ የብሔረሰቦችን ፣ የወዛደር ችን ፣ የወታደሮችን የተማሪዎችንና የመምህራንን ብሔራዊ የአመጽ እን ቅስቃሴ ታሪካዊ መነሻና ሂደት በሚመለከት በአብዮቱ ዋዜማ አጠቃላይ ጥናት ያካሄድኩት በአሜሪካ በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ በሆዋርድ ዩኒቨር ስቲና በታላቁ የአሜሪካ የኮንግሬስ ቤተ መጻሕፍት ነው ። ዝርዝር ጥናቱ ለሕትመት ሥራ በአሁኑ መልክ የተዘጋጀው በአብዮቱ ዘመን ከውጭ አገር ከተመለስኩ በኋላ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ፣ በባህል ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት የማጠናከሪያ ጥናት ካካሄድኩ በኋላ ነው ።

በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሆኑት የኢትዮጵያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ደግሞ የቀድሞ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር ፣ የቀድሞ ያገር ግዛት ሚኒ ስቴር ፣ የስታትስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ፣ የማስታወቂያ ሚኒ ስቴር ፣ የባህል ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ናቸው ። በዚህ አጋጣሚ ለእነዚህና ለሌሎችም ለጥናት ሥራዬ ምርምርና ምርት በአገር ውስጥና በውጭ አገር በልዩ ልዩ መንገዶች ፣ መግሪያዎችና ምክንያቶች ጉልህ አስተዋጽኦ ላደረጉት ሰዎችና ድርጅቶች በሙሉ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ላ. ጌ. ድ.



# ክፍል አንድ

## የገባር ሥርዓት ዕድገትና ውድቀት


## 1900 — 1933

## ምዕራፍ 1

### ማዕከላዊው መንግሥትና የገባሩ ሥርዓት

### የማዕከላዊው መንግሥት የምዕክልና ሂደት

የኢትዮጵያ አብዮት ታሪካዊ መነሻ የተከሰተው በአለፈው ምዕተ ዓመት ለአገሪቱ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት የፖለቲካ ምዕክልና በተካሄደው ብሔራዊ የአንድነት ትግል ወቅትና ሂደት በአገር አቀፍ ደረጃ በተስፋፋው የገባር ሥርዓት ውስጥ ነው ።



1. አፄ ቴዎድሮስ (1811 - 1860)
ምንጭ ፣ የፐረስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል አዲስ አበባ

በተጠቀሰው የሽግግር ዘመን በአጼ ነገሥታት ቴዎድሮስ ፣ ዮሐንስና ምኒልክ ተከታታይ ዘመናት የኢትዮጵያ ጥንታዊ በሀውርታዊና ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት በአካባቢ መሳፍንቶችና በውጭ ተጻራሪ ኃይሎች ላይ

የጻፍኩትን ጅምር የታሪክ ጥናት ረቂቅ በውጭ አገር ከፍተኛ ትምህርት ጨርሼ በ1968 ወደ አገሬ እስከመለስ ድረስ በአደራ ያቆየችልኝ ታናሽ እህቴ ወይዘሮ እቴነሽ ድሌቦ ነች ። የጅሌ ነባር ማህበረሰብ ከወንጂ ሜዳው በሆላንዳዊው ዓለም አቀፍ የስኳር ኩባንያ ከመባረሩ በፊት የነበረውን የማህበረሰቡን ጥንታዊ ታሪክና የገዳ ሥርዓት በአካባቢው በነበርኩበት ዘመን በዝርዝር ያስተማሩኝ ባአንድ የማህበረሰቡ አዛውንት በአቶ ከለቻ ደንቤ አስተባባሪነት የማህበረሰቡ ታዋቂ ሽማግሌዎች ናቸው ። የተባለው ኩባንያ በጅሌ ነባር ማህበረሰብና በወንጂ ሠራተኞች ላይ የፈጸመው ታላቅ የጥፋትና የብዝበዛ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ጥናት በስፋት ቀርቧል ።

የኢትዮጵያ የመሬትና የአርሶአደሩን መሰረታዊ የሥርዓት ችግር በሚመለከት ፣ እንዲሁም የአርሶአደሮችን ፣ የብሔረሰቦችን ፣ የወዛደሮችን ፣ የወታደሮችን የተማሪዎችንና የመምህራንን ብሔራዊ የአመጽ እንቅስቃሴ ታሪካዊ መነሻና ሂደት በሚመለከት በአብዮቱ ዋዜማ አጠቃላይ ጥናት ያካሄድኩት በአሜሪካ በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ በሆዋርድ ዩኒቨርስቲና በታላቁ የአሜሪካ የኮንግረስ ቤተ መጻሕፍት ነው ። ዝርዝር ጥናቱ ለሕትመት ሥራ በአሁኑ መልክ የተዘጋጀው በአብዮቱ ዘመን ከውጭ አገር ከተመለስኩ በኋላ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ፣ በባህል ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት የማጠናከሪያ ጥናት ካካሄድኩ በኋላ ነው ።

በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሆኑት የኢትዮጵያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ደግሞ የቀድሞ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር ፣ የቀድሞ ያገር ግዛት ሚኒስቴር ፣ የስታትስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ፣ የባህል ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ናቸው ። በዚህ አጋጣሚ ለእነዚህና ለሌሎችም ለጥናት ሥራዬ ምርምርና ምርት በአገር ውስጥና በውጭ አገር በልዩ ልዩ መንገዶች ፣ መዛሪያዎችና ምክንያቶች ጉልህ አስተዋጽኦ ላደረጉት ሰዎችና ድርጅቶች በሙሉ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

. ላ. ጌ. ድ.



# ክፍል አንድ

## የገባር ሥርዓት ዕድገትና ውድቀት

## 1900 — 1933

### ምዕራፍ 1

### ማዕከላዊው መንግሥትና የገባሩ ሥርዓት

### የማዕከላዊው መንግሥት የምዕክልና ሂደት

የኢትዮጵያ አብዮት ታሪካዊ መነሻ የተከሰተው በአለፈው ምዕተ ዓመት ለአገሪቱ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት የፖለቲካ ምዕክልና በተካሄደው ብሔራዊ የአንድነት ትግል ወቅትና ሂደት በአገር አቀፍ ደረጃ በተስፋፋው የገባር ሥርዓት ውስጥ ነው ።



1. አጼ ቴዎድሮስ (1811 - 1860)
ምንጭ ፣ የፕሬስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል አዲስ አበባ

በተጠቀሰው የሽግግር ዘመን በአጼ ነገሥታት ቴዎድሮስ ፣ ዮሐንስና ምኒልክ ተከታታይ ዘመ፣ ት የኢትዮጵያ ጥንታዊ በሀውርታዊና ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት በአካባቢ መሳፍንቶችና በውጭ ተጻራሪ ኃይሎች ላይ

በፖለቲካዊ ምዕክልና ተጠናክሮ በተገነባ ወቅት በሰሜንና በምስራቅ
አራት ታሪካዊ የጠረፍ አካባቢዎች ከአያሌ ብሔረሰቦችና ማህበረሰቦች
ጋር በአዲስ ስያሜ “ ኤርትራ ” ፣ “ የፈረንሳይ ሶማሌያ ላንድ ” ፣
“ የእንግሊዝ ሶማሊያላንድ ” እና “ የኢጣሊያ ሶማሊያ ላንድ ” ተብለው
በፈረንሳይ ፣ በእንግሊዝና በኢጣሊያ ኢምፔሪያሊስቶች እንደ ቅኝ
ግዛቶች ተያዙ ።



2. አፄ ዮሐንስ (1823 - 1881)
ምንጭ ፣ W.W. Loring. Soldier in Egypt (1884)

የተባሉ የውጭ ኃይሎች የአገሪቱን የጠረፍ አካባቢዎች በኃይል
ይዘው ለረጅም ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ የአገር ግምባታ ፖሊሲና ተግ
ባር ላይ ሁልአቀፍ የፖለቲካ ፣ የዲፕሎማሲ ፣ የጸጥታ ፣ የኢኮኖሚና
የባህል ማዕቀብና ቁጥጥር አደረጉ ። በመጨረሻም በ1928 የኢት
ዮጵያ ምድርና ሕዝብ ሁለንተናው የኢጣሊያ የቅኝ ግዛት እንዲሆን
ተስማሙ ።[1]

በኢትዮጵያ ብሔራዊ የአገር ግምባታ ፖሊሲና የተግባር እርምጃዎች
ላይ የተጠቀሰው የውጭ ኃይሎች የፖለቲካ ተጽዕኖና ቁጥጥር በ1928
እስከ ኢጣሊያ ወረራ ድረስ በአንድ በኩል ዘመናዊ ትምህርትና የልማት



ሥራ በአገሪቱ በነጻ እንዳያድግና እንዳይስፋፋ ሥርዓታዊ ተጽዕና አሳ
ደረ ። በሌላ በኩል ደግሞ በአገር ውስጥ በአጼው ማዕከላዊ መንግሥት
ሥር ለጥንታዊ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች የበለጠ ዕድገትና መስፋፋት
ከፍተኛ አስተዋጽኦ አደረገ ።

በዘመኑ ጥንታዊ የገባር ሥርዓትን ዕድገትና መስፋፋት በሚመ
ለከት ዳግማዊ ቴዎድሮስ ለአጼው መንግሥት የፖለቲካ ምዕክልና በአ
ካባቢ ተጻራሪ ኃይሎች ላይ በወሰዱት እርምጃ የአካባቢ መሳፍንቶችንና
የቤተ ክርስቲያንን የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሰረት በማፍረስ ማዕከላዊ
ውን መንግሥት በዘመናዊ ጦርና አስተዳደር ለማጠናከር ያደረጉት ጥረት
ይታወሳል ። ነገር ግን የአጼው የአገር ግምባታ ፖሊሲ በመሳፍንቶች
በቤተ ክርስቲያንና በእርሶ አደሩ እመጽ ፈረሰ ። ቀጥሎም አጼ ዮሐንስ
ሃይማኖትን ዋና የፖለቲካ መሣሪያ አድርገው በመጠቀም በውስጥና በው
ጭ ተጻራሪ ኃይሎች ላይ ማዕከላዊውን መንግሥት ለማጠናከር ያደረጉት
ጥረትም እንዲሁ በልዩ ልዩ የውስጥና የውጭ ግፊቶች ፈረሰ ።[2]

ከሁለቱ አጼዎች ቀጥለው የተነሱ አጼ ምኒልክ በቀደምት ነገሥታቱ
የአገር ግምባታ ፖሊሲ ላይ የስልት ለውጥ በማድረግ በእርሶ አደሩ
መደብ ላይ የቤተ ክርስቲያኑን ፣ የመስፍኑን ፣ የሹሙንና የወታደሩን
የኢኮኖሚ ጥቅም በከፍተኛ ደረጃ አጠናከሩት ። ጥንታዊውን በገባሩ
ጉልበትና ምርት የሚኖረውን የጦር ድርጅትና ሥርዓት የበለጠ አስፋ
ፉት ። በቤተ ክርስቲያን ፣ በመስፍንና በወታደር ድጋፍና አገልግሎት
በቀደምት ነገሥታት የተጀመረውን የአጼውን መንግሥት ምዕክልና
ፖሊሲ በጠንካራ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የድርጅት መሰረት የበለጠ
አጠናከሩት ። በዚህ በተጠቀሰው ያገር ግምባታ ስልትና ሂደት አጼምኒልክ
በአንድ በኩል በሰሜን ኢትዮጵያ በመሬትና በእርሶአደሩ የገባር መደብ
ላይ ላካባቢው ጉልተኛ የመሳፍንት ቤተሰቦችና ሹሞች በማዕከላዊ መን
ግሥት ሥር ልዩ ሥልጣንና ጥቅም በመስጠት በሌላ በኩል ደግሞ
በደቡብ ኢትዮጵያ በነባር ሕዝብ ላይ በሰፋሪ ጦር አማካይነት በግብርና
በአገልግሎት የማዕከላዊ መንግሥትን ሕግና ቁጥጥር በቀጥታ በመመ
ሥረት በአገሪቱ ሁለት ታሪካዊ አካባቢዎች በአንድ ጊዜ ሁለት የተለያዩ
የገባር ሕጐችንና የአስተዳደር ፖሊሲዎችን መሰረቱ ።

የዚህን የሰሜንና የደቡብ መንትያ የገባር ሥርዓት ታሪካዊ መነሻ
በሚመለከት ፣ በመጋቢት 1881 አጼ ዮሐንስ በመተማ ጦርነት ከሞቱ በ
ኋላ በሰሜን የየጁ ፣ የወሎ ፣ የዋግ ፣ የላስታ ፣ የበጌምድር ፣ የደምቢያ ፣ የስ
ሜን፣የጐጃምና የትግራይ የአካባቢ መሳፍንቶች፣ባላባቶችና የጦር አበጋዞች
በሰላም ለአጼ ምኒልክ ገበሩ ። አጼ ምኒልክም የተጠቀሱ መሳፍንቶችን ፣
ባላባቶችንና የጦር አለቆችን በማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ሥር በየት

ውልድ አካባቢያቸው መልሰው ሾሙአቸው ። [3] በሸዋ ደግሞ የአንኮበር ፡ የመንዝ ፡ የአዲስጌና የቱለማ የአካባቢ መሳፍንቶች ፡ ባላባቶችና የጦር አበጋዞች ከመጀመሪያ ጀምረው የምኒልክ ታማኝ ተከታዮችና የቤተ መንግሥት አገልጋዮች እንደነበሩ የሚታወስ ነው ። [4]



3. አፄ ምኒልክ ( 1836 - 1906 )
ምንጭ ፡ የፕሬስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል አዲስ አበባ

በዝርዝር ሲታይ በምኒልክ ዘመን በሰሜኑ መሀል ደጋ አውራጃዎች ማለትም በትግራይ የአጼ ዮሐንስ ፡ በየጁ ፡ በስሜን ፡ በበጌምድርና በደምቢያ የእቴጌ ጣይቱ ፡ በወሎ የራስ ሚካኤል ፡ በዋግ—ላስታ የዋግሹም ብሩ በጐጃም የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፡ በዳሞት —አገው ምድር



የራስ ቢትወደድ መንገሻ ፡ በአንኮበር የንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ፡ በመንዝ የአፈንጉሥ ነሲቡ ፡ በአዲስጌ የደጃዝማች ናደው በቱለማ የራስ ጐበና ባላባታዊ ቤተሰቦች ፡ ዘመዶችና ተዛማጅ ተከታዮች በዘመኑ የኢትዮጵያ ጥቂት በአካባቢ ኢኮኖሚና ጦር የተደራጁ የአካባቢውን መሬትና አርሶ አደሩን የገባር መደብ በማዕከላዊው መንግሥት ስም የሚገዙ ለከፍተኛ

የመንግሥት ሥልጣንና ሹመት እርስ በርሳቸው የሚዋጉ ፡ ከአጼው ማዕከላዊ መንግሥት ሹመትና የመሬት ጉልት ሲያጡ ደግሞ የየአካባቢያቸውን ሕዝብ በመንግስቱ ላይ ለአመጽ የሚቀሰቅሱ ፡ በማዕከላዊው የአጼ ዙፋንና ዘውድ ጥያቄ በየጊዜው በአገሪቱ ላይ የእርስ በርስ ጦርነት የሚቀሰቅሱ በአካባቢና በሥልጣን ጉዳዮች በማዕከላዊው መንግሥት ላይ ከውጭ ኃይሎች ጋር የሚያብሩ በጥንታዊ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች ላይ ለውጥ የማይፈልጉ አውራ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች ነበሩ ።

በሌላ በኩል በተፈጥሮ ለምና ሰፊ በሆነው ከአባይ—ወሎ በመለስ በሚገኘው የደቡብ ክፍል ማለትም በደቡብ ሸዋ ፡ በአርሲ ፡ በሐረርጌ ፡ በባሌ ፡ በሲዳሞ ፡ በጋሞጐፋ ፡ በከፋ ፡ በኢሉባቦርና በወለጋ የአጼ ምኒልክ የአስተዳደር ፡ የመሬት ፡ የግብርና የገባር ፖሊሲ በሰሜን በአካባቢው የመሳፍንትና የባላባት ቤተሰቦች አማካይነት ከተመሠረተው የአስተዳደር ፡ የመሬት ፡ የግብርና የገባር ፖሊሲ በዓይነት ልዩ ነው ።

በዚህ ረገድ ፡ ከሁሉ በፊት የደቡብ ነባር ሕዝቦችና የገዥ መደቦች ለምኒልክ የገበሩት ተዋግተው በጦርነት ከተሸነፉ በኋላ በማዕከላዊው መንግሥት ሰፋሪ ጦርና ሹማምንት ቁጥጥር ሥር በመሆን ነበር ። በመሆኑም ከጦርነት በኋላ የአካባቢው ሕዝብና መሬት በሰፋሪ የመንግሥት ጦርና ሹማምንት ቁጥጥር ሥር " የገባር መሬት " ፡ " የባላባት መሬት " እና " የመንግሥት መሬት " ተብሎ በሶስት የይዞታ ፈርጆች ተመደበ ። በዘመኑ በደቡብ የገባር መሬት ሲባል የአካባቢው ነባር ብሔረሰቦችና አርሶ አደሮች ለሰፋሪ ወታደሮች ፡ ሹማምንቶችና ቄሶች እንዲሁም ለማዕከላዊው መንግሥት ለሚሰጡ ልዩ ልዩ መንግሥታዊ የምግብ ፡ የጉልበት ፡ የሥራ ፡ የአሥራት ፡ የምርትና የግብር አገልግሎቶች ዋጋ በግል ይዞታ የሚሰጣቸው ፡ የአገልግሎት ግዴታውን ባያሟሉ ግን በመንግስት " ግብረ ጠል " ተብሎ የሚወረስ መሬት ነው ። የባላባት መሬት ደግሞ የአካባቢው የቀድሞ የጐሳ ተጠሪዎች የገዥ መደብ መሪዎችና አባሎች አሁን በሕዝቦቻቸው ላይ የማዕከላዊው መንግሥትና ሰፋሪ የመንግሥት ሹማምንቶች ጉዳይ አስፈጻሚ ወኪሎች በመሆን ለሚሰጡ የሥራ አገልግሎት ከመንግሥት በግል ይዞታ የሚሰጥ ፡ ባላባቱ የሚፈልግበትን አገልግሎት ለተጠቃሚው ክፍል በወቅቱ ባይሰጥ ግን "ግብረ ጠል" ተብሎ በመንግሥት የሚወረስ መሬት ነው ።

በአጼ ምኒልክ የአስተዳደር ሥርዓት በደቡብ "የመንግሥት መሬት"
ሲባል ደግሞ ቋሚ ይዞታው የማዕከላዊው መንግሥት ሆኖ "የገንደበል
መሬት"፣ "የማደሪያ መሬት"፣ "የሰሞን መሬት"፣ "የቤተ መንግ
ሥት መሬት" እየተባለ ለተወሰነ የአገልግሎት ዘመን ከነጻ የገባር
አገልግሎት ጋር የመሬቱን ፍሬ አበል እንዲጠቀሙበት ለወታደር፣
ለሹም፣ ለመስፍን፣ ለቤተክርስቲያን ለንጉሥ የሚታደል በተጠቃሚው
ግለሰብና ድርጅት ግን እንደ የግል ሀብትና ንብረት የማይሸጥ የማይለወጥ
በውርስም ለሌላ የማይሰጥ የሕብረተሰቡ ብሔራዊ ሀብትና ንብረት ነው።

በመሆኑም በምኒልክ ዘመን በደቡብ በአንድ በኩል የአገሪቱ
ሶስቱ የመሬት ባለቤቶች ማዕከላዊው መንግሥት ገባርና ባላባት ሲሆኑ
በሌላ በኩል ለመንግስት፣ ለጦርና ለቤተ ክርስቲያን ለተወሰነ ጊዜ
የተወሰነ አገልግሎት የሚሰጡ ሰፋሪ ወታደሮች፣ ሹማምንቶች፣ መሳፍ
ንቶች፣ ቄሶችና ሠራተኞች ከንጉሡ ጋር ፍሬ አበሉን ከነጻ የገባር
አገልግሎት ጋር በሚጠቀሙበት መሬት ላይ የግል ይዞታ መብት አል
ነበራቸውም። ነገር ግን ከምኒልክ በኋላ በደቡብ በመንግሥት ስም የተ
ያዘው የሕብረተሰቡ መሬት ለመንግሥት፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለጦር
ባለሥልጣኖችና አገልጋዮች የግለሰብና የድርጅት ርስት ወይም የሚሸጥ፣
የሚለወጥ የሚወረስ የግል ይዞታ የሚሆንበት ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት
ተፈጠረ። በመጨረሻም የተባለው አዲሱ የመሬት ይዞታ ለውጥ
በአገሪቱ ረጅም ታሪክ አብዮታዊ የሥርዓትና የስልተ ምርት ለውጥ
ያስከትላል።


በተጠቀሰው ዘመን በሰሜን ኃይለኛ የመሳፍንት ቤተሰቦች በአም
ራች የገባሩ መደብና በማዕከላዊው መንግሥት መካከል በአካባቢ ኢኮ
ኖሚና ጦር ተደራጅተው በሥልጣን ጥያቄ የአጼውን መንግሥት ምዕክልና
የሚቃረኑ አዲስ የፖለቲካ ኃይሎች እየሆኑ ያደጉትን ያህል በደቡብ ግን
በአካባቢው አምራች የገባሩ መደብ ላይ የሰፈሩ ወታደሮች፣ ሹማምንቶ
ችና ቄሶች ከሁሉ በፊት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅማቸውና ህልውናቸው
በአካባቢው ነባር ሕዝብ ላይ ከማዕከላዊው መንግሥት ጋር የተያያዘ ስለ
ሆነ ዘወትር የመንግሥቱን የፖለቲካ ምዕክልናና ጥንካሬ የሚደግፉ ታማኝ
አገልጋዮችና ሠራተኞች ሆነው ተገኙ።

ከሰሜንና ከደቡብ መንትያ የአስተዳደር ሥርዓት ባሻገር የምኒልክ
አንድ ሌላ መሠረታዊ ሥራ ከአድዋ ጦርነት በኋላ በአዲስ አበባ መዲና
ማዕከላዊ መንግሥትን ለማጠናከር በከተማ ሥሪት በመንገድ፣ በኢኮኖ
ሚ፣ በአስተዳደር፣ በውጭ ግንኙነት የተካሄደው የካፒታሊዝም ግም
ባታ ጅምር ነው።



በዚህ ረገድ ከአድዋ በኋላ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣሊያን ጨምሮ
የዘመኑ የዓለም ኃያላን መንግሥታት የኢትዮጵያን መንግሥታዊ ሉአላዊ
ነት በመቀበል ከአገሪቱ ጋር የዲፕሎማሲና የንግድ ግንኙነት መሠረቱ።
በተጨማሪም በአዲስ አበባ-ጂቡቲ የምድር ባቡር ሀዲድ አማካይነት በኢ
ትዮጵያና በውጭ ዓለም መካከል እያደገ የሚሄድ ንግዳዊና ዓለም አቀፋዊ
የሥራ ግኑ መስተጋብር ተፈጠረ። በአገርም ውስጥ በንግድ በአስተዳደርና
በግብር በአዲስ አበባ መዲናና በጅምር የክፍለ ሀገር ከተሞች መካከል
እያደገ የሚሄድ አዲስ የንግድ የገበያ የሥርዓትና የባህል ግንኙነት ተፈ
ጠረ። በአዲስ አበባ መዲና ዘመናዊ የመንገድ፣ የመገናኛ፣ የንግድ፣ የገ
በያ፣ የገንዘብ፣ የባንክ፣ የትምህርት፣ የአስተዳደር ማዕከላት ሥራዎችና
አገልግሎቶች ጅምር ታየ።

ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓትና የሥራ ጅምር በሚመለከት፣ ከ1900
በፊት በአገሪቱ ንጉሡ ጸሐፊ ትእዛዝ፣ አፈንጉሥ፣ የግቢ ሊጋባና የጦር
አበጋዝ የተባሉ አራት አማካሪዎችንና ረዳት ሹማምንቶችን ይዞ የመን



4. የኢትዮጵያ ሠራዊት በዘመቻ ሰምሪት በ1887
ምንጭ፣ Vanderheym, Expedition (1896)

ግስትን ሥልጣንና ሥራ በአፄአዊ ፈላጭ ቆራጭነት ብቻውን ያከናውን
እንደነበር የሚታወስ ነው።[5] በመጨረሻ ግን በአጼ ምኒልክ አዋጅ
የመንግሥትን የሥልጣን ሥራ በንጉሡ ስም በውክልና የሚያከናውን
አዲስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፈረንሳይ አማካሪዎች ምክርና እርዳታ
ተቋቋመ። በምክር ቤቱ የአገሪቱ የመጀመሪያ ቢሮክራሲያዊ የፍርድ፣
የጦር፣ የግቢ፣ የጽሕፈት፣ ያገር ግዛት፣ የገንዘብ፣ የውጭ ጉዳይ፣ የን

በአጼ ምኒልክ የአስተዳደር ሥርዓት በደቡብ “ የመንግሥት መሬት ” ሲባል ደግሞ ቋሚ ይዞታው የማዕከላዊው መንግሥት ሆኖ “ የግንደበል መሬት” ፣ “ የማደሪያ መሬት ” ፣ “ የሰሞን መሬት ” ፣ “ የቤተ መንግሥት መሬት ” እየተባለ ለተወሰነ የአገልግሎት ዘመን ከነጻ የገባር አገልግሎት ጋር የመሬቱን ፍሬ አበል እንዲጠቀሙበት ለወታደር ፣ ለሹም ፣ ለመስፍን ፣ ለቤተክርስቲያን ለንጉሥ የሚታደል በተጠቃሚው ግለሰብና ድርጅት ግን እንደ የግል ሀብትና ንብረት የማይሸጥ የማይለወጥ በውርስም ለሌላ የማይሰጥ የሕብረተሰቡ ብሔራዊ ሀብትና ንብረት ነው ።

በመሆኑም በምኒልክ ዘመን በደቡብ በአንድ በኩል የአገሪቱ ሶስቱ የመሬት ባለቤቶች ማዕከላዊው መንግሥት ገባርና ባላባት ሲሆኑ በሌላ በኩል ለመንግስት ፣ ለጦርና ለቤተ ክርስቲያን ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ አገልግሎት የሚሰጡ ሰፋሪ ወታደሮች ፣ ሹማምንቶች ፣ መሳፍንቶች ፣ ቄሶችና ሠራተኞች ከንጉሡ ጋር ፍሬ አበሉን ከነጻ የገባር አገልግሎት ጋር በሚጠቀሙበት መሬት ላይ የግል ይዞታ መብት አልነበራቸውም ። ነገር ግን ከምኒልክ በኋላ በደቡብ በመንግሥት ስም የተያዘው የሕብረተሰቡ መሬት ለመንግሥት ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለጦር ባለሥልጣኖችና አገልጋዮች የግለሰብና የድርጅት ርስት ወይም የሚሸጥ ፣ የሚለወጥ የሚወረስ የግል ይዞታ የሚሆንበት ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት ተፈጠረ ። በመጨረሻም የተባለው አዲሱ የመሬት ይዞታ ለውጥ በአገሪቱ ረጅም ታሪክ አብዮታዊ የሥርዓትና የስልተ ምርት ለውጥ ያስከትላል ።

በተጠቀሰው ዘመን በሰሜን ኃይለኛ የመሳፍንት ቤተሰቦች በአምራች የገባሩ መደብና በማዕከላዊው መንግሥት መካከል በአካባቢ ኢኮኖሚና ጦር ተደራጅተው በሥልጣን ጥያቄ የአጼውን መንግሥት ምዕክልና የሚቃረኑ አዲስ የፖለቲካ ኃይሎች እየሆኑ ያደጉትን ያህል በደቡብ ግን በአካባቢው አምራች የገባሩ መደብ ላይ የሰፈሩ ወታደሮች ፣ ሹማምንቶችና ቄሶች ከሁሉ በፊት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅማቸውና ህልውናቸው በአካባቢው ነባር ሕዝብ ላይ ከማዕከላዊው መንግሥት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ዘወትር የመንግሥቱን የፖለቲካ ምዕክልናና ጥንካሬ የሚደግፉ ታማኝ አገልጋዮችና ሠራተኞች ሆነው ተገኙ ።

ከሰሜንና ከደቡብ መንትያ የአስተዳደር ሥርዓት ባሻገር የምኒልክ አንድ ሌላ መሠረታዊ ሥራ ከአድዋ ጦርነት በኋላ በአዲስ አበባ መዲና ማዕከላዊ መንግሥትን ለማጠናከር በከተማ ሥሪት በመንገድ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በአስተዳደር ፣ በውጭ ግንኙነት የተካሄደው የካፒታሊዝም ግምባታ ጅምር ነው ።



በዚህ ረገድ ከአድዋ በኋላ እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይና ኢጣሊያን ጨምሮ የዘመኑ የዓለም ኃያላን መንግሥታት የኢትዮጵያን መንግሥታዊ ሉአላዊነት በመቀበል ከአገሪቱ ጋር የዲፕሎማሲና የንግድ ግንኙነት መሠረቱ ። በተጨማሪም በአዲስ አበባ-ጂቡቲ የምድር ባቡር ሀዲድ አማካይነት በኢትዮጵያና በውጭ ዓለም መካከል እያደገ የሚሄድ ንግዳዊና ዓለም አቀፋዊ የሥልጣኔ መስተጋብር ተፈጠረ ። በአገርም ውስጥ በንግድ በአስተዳደርና በግብር በአዲስ አበባ መዲናና በጅምር የክፍለ ሀገር ከተሞች መካከል እያደገ የሚሄድ አዲስ የንግድ የገበያ የሥርዓትና የባህል ግንኙነት ተፈጠረ ። በአዲስ አበባ መዲና ዘመናዊ የመንገድ ፣ የመገናኛ ፣ የንግድ ፣ የገበያ ፣ የገንዘብ ፣ የባንክ ፣ የትምህርት ፣ የአስተዳደር ማዕከላት ሥራዎችና አገልግሎቶች ጅምር ታየ ።

ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓትና የሥራ ጅምር በሚመለከት ፣ ከ1900 በፊት በአገሪቱ ንጉሡ ጸሐፌ ትእዛዝ ፣ አፈንጉሥ ፣ የግቢ ሊጋባና የጦር አበጋዝ የተባሉ አራት ኦማካሪዎችንና ረዳት ሹማምንቶችን ይዞ የመን



4. የኢትዮጵያ ሠራዊት በዘመቻ ስምሪት በ1887
ምንጭ ፣ Vanderheym, Expedition (1896)

ግስትን ሥልጣንና ሥራ በአጼአዊ ፈላጭ ቆራጭነት ብቻውን ያከናውን እንደነበር የሚታወስ ነው ።[5] በመጨረሻ ግን በአጼ ምኒልክ አዋጅ የመንግሥትን የሥልጣን ሥራ በንጉሡ ስም በውክልና የሚያከናውን አዲስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፈረንሳይ አማካሪዎች ምክርና እርዳታ ተቋቋመ ። በምክር ቤቱ የአገሪቱ የመጀመሪያ ቢሮክራሲያዊ የፍርድ ፣ የጦር ፣ የግቢ ፣ የጽሕፈት ፣ ያገር ግዛት ፣ የገንዘብ ፣ የውጭ ጉዳይ ፣ የን

ግድ ፡ የእርሻ ፡ የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ፡ የሥራና የትምህርት መሥሪያ ቤቶች ተዋቀሩ ። [6] በተጨማሪም ለአስተዳደርና ለግብር ሥራ በሚያመች መንገድ የአገሪቱ መላው ሕዝብና መሬት በአዲስ አበባ በቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ በአዲሱ የፍርድ ሚኒስቴር ሥር በስድስት የሕግና የፍርድ ጉባኤዎች ተዋቀሩ ። በስድስቱ የሕግና የዳኝነት ጉባኤዎች ሥር በዘጠና የሚቆጠሩ የአስተዳደር ክልሎች ተመደቡ ። በስድስቱ ጉባኤዎች ሥር ከክልሎቹ ለበላይ ውሳኔ በይግባኝ የሚመጡ የአስተዳደር ጉዳዮችን መርምረው የሚወስኑ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ተሾሙ ። [7]

ይህ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአገሪቱ የገባር መደብ ላይ የጉልተኛው መደብ ማለትም የመሳፍንቱ ፡ የመኳንንቱ ፡ የጦርና የቤተክርስቲያን ሹማምንቱ የተባበረ መደብ የፖለቲካ መሣሪያና መግለጫ ሆነ ። በዚህ አኳያ <u>የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግመት</u> <u>ታሪክ</u> በተሰኘው መጽሐፌ በኢትዮጵያ ታሪክ የሕዝብንና የመንግሥትን ግንኙነት አስመልክቶ በቀረበው ሥርዓታዊ ትንተና በአገሪቱ ታሪክ የሥልጣን ፡ የሹመት ፡ የጉልትና የግል ሀብት ሕጋዊ ሥርዓትና ወሰን አለመኖር በመላ ሕብረተሰቡ ላይ እንዴት ለንጉሡ ፍጹም አጼአዊ ሥልጣን ሥርዓታዊ መሠረት ፡ መሣሪያና ምክንያት እንደሆነ ተገልጾአል ።

ነገር ግን በመጨረሻ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የውጭ ኃይሎች ግፊትና የአጼው መንግሥት የፖለቲካ ምዕክልና ከአዲሱ የአስተዳደር ሥርዓት ጋር በተጠቀሰው ጥንታዊ የፖለቲካ ሥርዓት መሠረታዊ ለውጥ ማስከተል ጀመሩ ። የዚህ የሥርዓት ለውጥ ጅምር ለመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ መዲና ከተማዊ ዕድገትና በ1900 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ምሥረታ ነው ። በሚኒስትሮች ምክር ቤት ምሥረታና ሹመት ጉልተኛ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች በንጉሡ ስም በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግሥትን ሥልጣን በውክልና ይዘው በአምራቹ የገባር መደብ ላይ የጉልተኛውን መደብ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያጠናክሩ ብዙ ተከታታይ ሕጋዊ እርምጃዎችን ወሰዱ ።

በዚህ አንጻር በጥቅምት 1900 የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተመሠረተ በአራተኛ ቀን በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ የከተማ መሬት በግለሰቦችና በመንግሥት የሚሸጥበትና የሚገዛበት አዲስ ሕግ ባአዋጅ ወጣ ። [8] ቀጥሎም በሐምሌ 1900 የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመጀመሪያ ጉባኤው በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ የፍርድ ፡ የዳኝነት ፡ የፍትሐብሔር ፡ የወንጀል የግል መሬት ይዞታ ፡ የመንግሥት ሀብት ፡ የግል ሀብትና ውርስ ሕጎችን እንደሚከተለው ደነገገ ።

“ በወንጀል እየተያዘ መሬቱን የሚነቅል ሰው ሁሉ ወንጀልም ቢገኝበት በከብቱና በሰውነቱ ይቀጣ እንጂ መሬቱን አይነቀል ። ነገር



ግን ነፍስ ገድሎ የሄደ በመንግሥት ክፉ ሥራ የሠራ ይነቀል ። ርስትም ማለት ያባት የናት መሬት ደግሞ በወርቁ የገዛው መሬት ነው እንጂ የመንግሥት መትከያ የሆነ አይደለም ።

“ ደግሞ የመትከያም መሬት ቢሆን መንግሥት ርስት ያደረገለት ይረጋል ። መካንም የሞተ እንደሆነ አባቱ እናቱ ገንዘቡንም ርስቱንም ይውሰዱ እንጂ ሹም አይውረስ ። እናትም አባትም የሌለው እንደሆነ ወንድሙ እህቱ ይውረሱ ። እናት አባት እህት ወንድም የሌለው እንደሆነ ግን እስከ አራት ትውልድ ላለ ለቅርብ ዘመዱ ይሁን ። ደግሞም ከዘመዶቹ ለይቶ ለእገሌ ይሁን ብሎ የተናዘዘ እንደሆነ የተናዘዘለት ይውሰድ ። ከአራት ትውልድ ወዲያ የሆነ ግን ውርሱ ለሹም ይሁን ብለው ሥራት ሠሩ ። ይኸውም ምክር በመኳንንቱም በሠራዊቱም የተወደደ ሆነ ። በጃንሆይ ፈቃድ በነጋሪት አደባባይ አዋጅ ተነገረ ። [9]

ቀጥሎም በ1923 የኢትዮጵያ በአካባቢ ኢኮኖሚና ጦር የተደራጁ ጉልተኛ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች በአጼ ኃይለ ሥላሴ መሪነት ተሰብስበው በአዲሱ ሕገ መንግሥት የአገሪቱን መሬት ከሕዝቡና ከመንግስት ሥልጣን ጋር ፍጹም መደባዊ ንብረታቸው የሚያደርግ አዲስ ሥርዓት ደነገጉ ። [10]



5. ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ (1837 - 1905)
ለአርባ ዓመታት ጸሐፌ ትዕዛዝ

<u>ምንጭ</u> ፡ ገብረ ሥላሴ ፡ <u>ምኒሊክ</u> (1959)

# የጉልተኛ መደብ

## የጉልተኛው መደብ ታሪካዊ መነሻ

በየትም ስፍራና በምንም ጊዜ የአንድ የገዥ መደብ ስርዓታዊ ባህርያትና መግለጫዎች የግል ሀብትና የመንግስት ስልጣን ጥያቄዎች ናቸው ። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ከውጭ የወራሪዎችና የኢምፔሪያሊስቶች ግፊት በአገር ውስጥ ደግሞ የአጼው መንግስት የፖለቲካ ምዕክልና የሕብረተሰቡን ሀብት ከመንግሥት ሥልጣን ጋር በአካባቢ ኢኮኖሚና ጦር በተደራጀው የጉልተኛ መደብ ቁጥጥር ስር አደረጉ ።

ከሁሉ በፊት በዘመኑ ከወራሪዎችና ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ለብሔራዊ አንድነት የተካሄደውን የመከላከል ጦርነት ያደረጁና የመሩ የኢትዮጵያ የአካባቢ ጉልተኛ መሳፍንቶች ፣ ባላባቶችና ፣ የጦር አለቆች ናቸው ።

በተጨማሪም ከውጭ ኃይሎች ጋር ለብሔራዊ አንድነትና መንግሥታዊ ሉአላዊነት ብተካሄደው የመከላከል ጦርነት ወቅትና ሂደት የጉልተኛውን መደብ ሊተካ የሚችል ዘመናዊ የሠራተኛ ፣ የገበሬ ፣ የምሁር ፣ የነጋዴ ድርጅትና የፖለቲካ ኃይል በአገሪቱ ገና አልተከሰተም ። በመሆኑም የአገሪቱ መሬትና የገባር ጉልበት ከመንግሥት ሥልጣን ጋር በአካባቢ ኢኮኖሚና ጦር በተደራጀው የጉልተኛ መደብ እጅ ገባ ።

ቡተጠቀሰው የሽግግር ዘመን የጉልተኛው መደብ የሕብረተሰቡን የመሬትና የጉልበት ሀብት በሹመትና በጉልት ስሪት አማካይነት ያዘ ። በሚኒስትሮች ምክር ቤት አማካይነት ደግሞ የመንግሥትን ሥልጣን ያዘ ። በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት የኤኮኖሚን መሰረት ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር በእጁ ይዞ የጉልተኛው መደብ መደባዊ የፖለቲካ በላይነቱን በሕብረተሰቡ ላይ ቀስ በቀስ ማረጋገጥ ጀመረ ።

እንደዚህ በአካባቢ ኢኮኖሚ ፣ ጦርና የመንግሥት ሥልጣን የተደራጀው የኢትዮጵያ ጉልተኛ የገዥው መደብ ከ1900 እስከ 1910 ድረስ በፖለቲካ ውሳኔዎችና በወታደራዊ እርምጃዎች እቴጌ ጣይቱን ጨምሮ የምኒልክን የቀድሞ ባለሥልጣኖች ከፖለቲካ አመራር አስወገደ ። ልጅ ኢያሱን በአመጽ ሽሮ የመንግሥቱን አዲስ ርዕስ ብሔርና የመስተዳደር መሪ በሥልጣኑ መርጦ ሾማቸው ።

በተጨማሪም የጉልተኛው መደብ በፊት በማዕከል የተያዘውን የሕብረተሰቡን የመሬት ሀብት ከገባሩ ጉልበት ጋር ለራሱ የሚሸጥ ፣ የሚለውጥና የሚወረስ የግል ሀብት የሚያደርጉ ሕጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ ጀመረ ። ይህ የጉልተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣንና የኢኮኖሚ ይዞታ በሕጋዊ መሰረት በግልጽ የተከሰተው በመደቡ መሪዎችና አባሎች መካከል ከ1900 እስከ 1922 ድረስ የሥልጣን ጦርነት ከተካሄደ በኋላ በ1923



በአጼ ኃይለ ሥላሴ ሕገ መንግሥት ነው ። ሕገ መንግሥቱን በሐምሌ 9 ቀን 1923 ከአጼው ጋር በፊርማቸው ያጸደቁ ጉልተኛ ጳጳሳት ፣ መሳፍንት ፣ ሚኒስትር ባለሥልጣኖችና መኳንንት ጠቅላላ ቁጥር 24 ነበር ። [11]

በዘመኑ የጳጳሳትን ሥልጣንና ሥራ በሚመለከት ፣ በ1922 አቡነ ቄርሎስ የአዲስ አበባ ፣ የሸዋ ፣ የአርሲና የሐረርጌ ፣ አቡነ አብርሃም የጐጃምና የቤጌምድር ፣ አቡነ ይስሐቅ የትግራይ ፣ የላስታና የዋግ ፣ አቡነ ጴጥሮስ የወሎና የየጁ ፣ አቡነ ሚካኤል የከፋ ፣ የኢሉባቦርና የወለጋ ፣ አቡነ ሳዊሮስ የደቡብ ምዕራብ ሀገረ ስብከት ኃላፊ ሆነው እንደተሾሙ ይታወሳል ። [12]

በ1923ቱ ሕገ መንግሥት ውይይትና ውሳኔ ወቅት በጉልተኛ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች መካከል የነበረውን የሀሳብ ግጭትና ስምምነት አጼ ኃይለ ሥላሴ እንደሚከተለው በስፋት አብራርቷል ። በአጼው ቃል የሕገ መንግሥቱ የመጀመሪያ ረቂቅ በታዋቂ ሰዎች በኮሚቴ ተዘጋጅቶ ፣

"እኛ ከመረመርነው በኋላ ከመሳፍንቱ ወገን ራስ ካሳ ኃይሉ ፣ ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ፣ ራስ ሥዩም መንገሻ ፣ ራስ ጉግሳ አርአያ ፣ ራስ እምሩ ፣ ኃይለ ሥላሴ ከሚኒትሮችም ወገን የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል ያገር ግዛት ሚኒስትሩ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ጉሹ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴ የጽሕፈት ሚኒስትሩ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ታሪኩ ከመኳንንት ወገን ደጃዝማች ይገዙ በሀብቴ በጅሮንድ ተክለሐዋርያት ባንድነት እንዲመረምሩትና ለመፈረም የተዘጋጀ አድርገው እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጠን ።

"እነዚህም ነገሩን መርምረው ለመፈረም የተዘጋጀ አድርገው እንዲያቀርቡ የታዘዙት ሰዎች በአሳብ ሳይጋጠሙ ስለቀሩ ብዙ ጊዜ በእኛ ፊት ሲከራከሩበት ቆይተው ነበር ። ከመሳፍንቱ ራስ እምሩ ብቻ አሳቡን ከሚኒስትሮችና ከመኳንንቱ ጋራ አድርጐ ነበር እንጂ የቀሩት አራቱ መሳፍንት በአሳብ አንድ ሆነው ነበር ።

"የመሳፍንቱ አሳብ ኢትዮጵያ በትልልቁ አውራጃ ተከፍሎ ለመሳፍንቱ ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ርስት እየሆነ እንዲሰጥ በንጉሠ ነገሥቱና በመንግሥቱ ላይ ትልቅ የወንጀል ሥራ ሠርተው ካልተመሰከረባቸው በቀር ዘራቸው እንዳይነቀል በየውስጣቸውም ያለው የያውራጃው ባላባት የያዘው ግዛት ርስት ሆኖለት ለመሳፍንቱ እየገበረና እየታዘዘ እንዲኖር ነበር ።

"የሚኒስትሮችና የመኳንንቱ አሳብ ግን " ኢትዮጵያ በየትልልቁ አውራጃ ተከፍሎ ለመሳፍንትና ለባላባቶች ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ርስት ሆኖ ከተሰጠና ሹመት በዘር ይሁን ከተባለ ወደፊት የሚነሳው ትውልድ እንደምን ሊሆን ነው ? ቢማርስ ቢያገለግልስ ሹመትና ግዛት ካላገኘ ኢት

ዮጵያ አገሬ ናት ለማለት እንደምን ይችላል ? ስለዚህ አሁን ያሉት መሳፍንትና ባላባቶች ጥፋት ካልተገኘባቸው ባገረገዥነት ብቻ ይቆዩ ጥፋት ተገኝቶባቸው ቢሻሩ ወይም ቢሞቱ ግን በግዛታቸው ዕውቀትና ችሎታ ያለው ማንም ኢትዮጵያዊ እንዲሾምበት ይሁን እንጂ ለዘር ማለፉ የሚገባ ነገር አይደለም ። ዳሩ ግን ልጆቻቸው በዕውቀትና ባገለግሎት እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሆነው ቢገኙ ንጉሠ ነገሥቱ እንዳወቀ በአባቶቻቸው ግዛት ወይም በሌላ ማዕረግ ስፍራ ይሾማቸው እንጂ ግዛታቸው ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ርስት መሆኑ በሕገ መንግሥት ሲጻፍ አይታየንም" የሚል ነበር ።

" መሳፍንቱም ይህን ያቀረቡትን አሳብ ሚኒስትሮችና መኳንንቱ እንዳልተቀበሉዋቸው ባዩ ጊዜ ይህም ካልሆነ ከዚያው ከግዛታችን ከብዙ አውራጆች ውስጥ አንዳንዱ አውራጃ ብቻ ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ነው ተብሎ በሕገ መንግሥት ይጻፍልን የሚል አሳብ አቀረቡ ሚኒስትሮችና መኳንንቱ ግን ይህንም አሳብ አንቀበልም ብለው በፊተኛው አሳባቸው ጸኑ ።

" እኛም ለዚህ ሥራ የመረጥናቸው ሰዎች በአሳብ መለያየታቸውን በሰማን ጊዜ ሁለቱም ወገኖች አሳባቸውን ከነማስረጃው በጽሕፈት እንዲያቀርቡ አድርገን ከመረመርነው በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ለመሳፍንቱም ቢሆን ለሌሎችም የመንግሥት አገልጋዮች ቢሆን ርስትና ጉልት ለመትከል ይችላል የሚል አንድ ክፍል በሕገ መንግሥቱ ይጻፍና ወደፊት አገልግሎታቸው እየታየ እንደሚያስፈልግ ይደረጋል እንጂ የፊውዳል መንግሥት በዓለም ላይ መቅረቱን እያወቅን አሁን እንደገና ያንኑ አጽንተን በሕገ መንግሥት መዳፍ ወይም ያለ ሕገ መንግሥት መግዛት የማይገባ መሆኑን ለመሳፍንቱ አስረድተን ተጣርቶ ተጽፎ እንዲፈረም ይሁን በማለት ነገሩን ቆጠርን ። " [13]

ነገር ግን የሕገ መንግሥቱ ዋናው ዓላማና ተግባር በ1909 በተፈሪ ኃይለ ሥላሴ መሪነት በጉልተኛው መደብ ለተያዘው የመንግሥት ሥልጣን ሕጋዊ መሰረት ማስገኘት ነበር ። ከዚህ ሌላ ብሔራዊ ፋይዳ አልነበረውም ። በመሆኑም በኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ የአገሪቱ መሰረታዊና ብሔራዊ የነበሩት ያገር መከላከያ የመሬት ፡ የገባር ፡ የባርያና የልማት ጥያቄዎች በሕገመንግሥቱ ውይይት ሆነ አንቀጽ አልተነሱም ። የአጼው ተቀዳሚ ፍላጐት በ1909 ኩዴታ የተያዘውን የመንግሥት ሥልጣን በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ከንግሥት ሳባና ከንጉሥ ሰለሞን ጋር አያይዞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሥርወ መንግሥት መገንባት ሲሆን የተቀሩ መሳፍንቶች ጥረት ደግሞ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በአዲሱ ሥርወ መንግሥት ሥር በዘር ውስር የሚተላለፍ የጉልትና የሹመት መብት በሕግ መሠረት ማግኘት ነበር ። እነዚህ የአጼውና የመሳፍንቱ መሰረታዊ ፍላጐቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጾች በግልጽ እንደሚከተለው ሰፍረው ይገኛሉ ።





አንቀጽ 2 ፡ " የኢትዮጵያ መሬትም ፡ ሕዝብም ፡ ሕጉም በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥት ነው ።

አንቀጽ 3 ፡ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰለሞንና ንግሥተ ሳባ ከተባለችው ከኢትዮጵያ ንግሥት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኖአል ።

አንቀጽ 5 ፡ " ንጉሠ ነገሥቱ የነጋሲ ዘር በመሆኑና ቅብአ መንግሥት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ ማዕረጉ የማይገሰስ ኃይሉ የማይደፈር ሆኖ በቆየው ልማድ ባዲሱም ሕግ በሚገባው ክብር ሁሉ ይከበራል ። ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የተነሳ ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል ።

አንቀጽ 15 ፡ "ንጉሠ ነገሥቱ የመስፍንነትና ሌላም የክብር ስም ለመስጠት ርስተ ጉልትም ለመትከል አዲስ ኒሻንም ለማውጣት ይችላል ።

አንቀጽ 19 ፡ "የንጉሠ ነገሥቱ ዘሮች እስከ አምስት ትውልድ ያሉት ለዘውድ የሚመረጡ ናቸውና የጋብቻቸውንና ባገር ውስጥም ለመኖር ካገርም ውጭ ለመውጣት ስለ ትዳራቸውም ስለመከለሳቸውም በሕግ ይወሰናል ። "



6. ወህዚ ሊዛዥ ወልደ ጸረቅ (1831-1901) ለአርባ ዓመታት ያገር ደህንነት ዘፋ

ምንጭ ፡ L. Traveski, Let Marefia (1931)

ዮጵያ አገሬ ናት ለማለት እንደምን ይችላል ? ስለዚህ አሁን ያሉት መሳፍ ንትና ባላባቶች ጥፋት ካልተገኘባቸው ባገረገዥነት ብቻ ይቆዩ ጥፋት ተገኝቶባቸው ቢሻሩ ወይም ቢሞቱ ግን በግዛታቸው ዕውቀትና ችሎታ ያለው ማንም ኢትዮጵያዊ እንዲሾምበት ይሁን እንጂ ለዘር ማለፉ የሚ ገባ ነገር አይደለም ። ዳሩ ግን ልጆቻቸው በዕውቀትና ባገለግሎት እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሆነው ቢገኙ ንጉሠ ነገሥቱ እንዳወቀ በአባቶቻቸው ግዛት ወይም በሌላ ማዕረግ ስፍራ ይሾሟቸው እንጂ ግዛታቸው ለልጅ ልጅ የሚ ያልፍ ርስት መሆኑ በሕገ መንግሥት ሲጻፍ አይታየንም" የሚል ነበር ።

"መሳፍንቱም ይህን ያቀረቡትን አሳብ ሚኒስትሮችና መኳንንቱ እን ዳልተቀበሉዋቸው ባዩ ጊዜ ይህም ካልሆነ ከዚያው ከግዛታችን ከብዙ አው ራጆች ውስጥ አንዳንዱ አውራጃ ብቻ ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ነው ተብሎ በሕገ መንግሥት ይጻፍልን የሚል አሳብ አቀረቡ ሚኒስትሮችና መኳን ንቱ ግን ይህንም አሳብ አንቀበልም ብለው በፊተኛው አሳባቸው ጸኑ ።

"እኛም ለዚህ ሥራ የመረጥናቸው ሰዎች በአሳብ መለያየታቸውን በሰማን ጊዜ ሁለቱም ወገኖች አሳባቸውን ከነማስረጃው በጽሕፈት እን ዲያቀርቡ አድርገን ከመረመርነው በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ለመሳፍንቱም ቢሆን ለሌሎችም የመንግሥት አገልጋዮች ቢሆን ርስትና ጉልት ለመት ከል ይችላል የሚል አንድ ክፍል በሕገ መንግሥቱ ይጻፍና ወደፊት አገልግ ሎታቸው እየታየ እንደሚያስፈልግ ይደረጋል እንጂ የፊውዳል መንግሥት በዓለም ላይ መቅረቱን እያወቅን አሁን እንደገና ያንኑ አጽንተን በሕገ መንግሥት መጻፍ ወይም ያለ ሕገ መንግሥት መግዛት የማይገባ መሆኑን ለመሳፍንቱ አስረድተን ተጣርቶ ተጽፎ እንዲፈረም ይሁን በማለት ነገ ሩን ቆጠርን ።" [13]

ነገር ግን የሕገ መንግሥቱ ዋናው ዓላማና ተግባር በ1909 በተፈሪ ኃይለ ሥላሴ መሪነት በጉልተኛው መደብ ለተያዘው የመንግ ሥት ሥልጣን ሕጋዊ መሰረት ማስገኘት ነበር ። ከዚህ ሌላ ብሔራዊ ፋይዳ አልነበረውም ። በመሆኑም በኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ የአገሪቱ መሰረታዊና ብሔራዊ የነበሩት ያገር መከላከያ የመሬት ፤ የግባር ፤ የባ ርያና የልማት ጥያቄዎች በሕገመንግሥቱ ውይይት ሆነ አንቀጽ አል ተነሱም ። የአጼው ተቀዳሚ ፍላጐት በ1909 ኩዴታ የተያዘውን የመ ንግሥት ሥልጣን በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ከንግሥት ሳባና ከንጉሥ ሰለ ሞን ጋር እያይዞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሥርወ መንግሥት መገንባት ሲሆን የተቀሩ መሳፍንቶች ጥረት ደግሞ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በአዲሱ ሥርወ መንግሥት ሥር በዘር ውርስ የሚተላለፍ የጉልትና የሹመት መብት በሕግ መሠረት ማግኘት ነበር ። እነዚህ የአጼውና የመሳፍንቱ መሰረታዊ ፍላጐቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጾች በግልጽ እንደሚከተለው ሰፍረው ይገኛሉ ።





**አንቀጽ 2 ፤** "የኢትዮጵያ መሬትም ፤ ሕዝብም ፤ ሕጉም በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥት ነው ።

**አንቀጽ 3 ፤** "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰለሞንና ንግሥተ ሳባ ከተባለችው ከኢትዮጵያ ንግሥት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኖአል ።

**አንቀጽ 5 ፤** "ንጉሠ ነገሥቱ የነጋሲ ዘር በመሆኑና ቅብአ መንግሥት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ ማዕረጉ የማይገሰስ ኃይሉ የማ ይደፈር ሆኖ በቆየው ልማድ ባዲሱም ሕግ በሚገባው ክብር ሁሉ ይከበራል ። ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የተነሳ ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል ።

**አንቀጽ 15 ፤** "ንጉሠ ነገሥቱ የመስፍንነትና ሌላም የክብር ስም ለመስ ጠት ርስተ ጉልትም ለመትከል አዲስ ኒሻንም ለማውጣት ይችላል ።

**አንቀጽ 19 ፤** "የንጉሠ ነገሥቱ ዘሮች እስከ አምስት ትውልድ ያሉት ለዘውድ የሚመረጡ ናቸውና የጋብቻቸውንና ባገር ውስ ጥም ለመኖር ካገርም ውጭ ለመውጣት ስለ ትዳራቸ ውም ስለመከለሳቸውም በሕግ ይወስናል ።"



ምንጭ ፤ L. Traveski, Let Marefia (1931)

6. ወህኒ አ.ዛዥ ወልደ ጻድቅ (1831-1901) ለአርባ ዓመታት ያገር ደህንነት ሹም

## የመስፍኑ የሹመትና የጉልት መብት

አንቀጽ 34 ፡ “ ባቅኝነትም በሌላም ለኢትዮጵያ በሚጠቅም አገልግሎት ከንጉሠ ነገሥቱ የመስፍንነት ማዕረግ የተቀበሉት ወደፊትም የሚቀበሉት ይህ አቅኝነትና አገልግሎት ከመስፍንነት ያደረሳቸው ስለሆነ ንጉሠ ነገሥቱ በምክር ቤት አስመክሮ ያቆመውን ሕግ ለሥራቸው ሁሉ ዋና መሪ እያደረጉ የመስፍንነታቸውን አገር እንዲገዙ ሆኖ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 35 ፡ “ ማንኛወም መስፍንና አገረገዥ ቢሆን ከንጉሠ ነገሥቱ በተቀበለው ሥልጣንና መብት ለኢትዮጵያ መተዳደሪያ ለመሆን ከንጉሠ ነገሥቱ የወጣውን ሕግና ደንብ ዋና መሪ እያደረገ የተሾመበትን እንዲገዛ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 36 ፡ “ ባቅኝነትም በሌላም ለኢትዮጵያ በሚጠቅም ሥራ አባቶቻቸው ያገለገሉ መሳፍንቶች የቅኝ ያገልጋይ ባለውለታና የባለውለታ ልጆች መሆናቸውን ንጉሠ ነገሥቱ እያስመረመረ አባቶቻቸው እያቀኑ ከያዙት ላይ ለትውልድ የሚያልፍ የመስፍንነት ርስተ ጉልት ሊተከላቸው ይችላል ።

አንቀጽ 37 ፡ “ደግሞ እንደዚሁ ባቅኝነ ትም በሌላም ለኢትዮጵያ በሚጠቅም ሥራ አባቶቻ ቸው ያገለገሉ መኳንንቶች ባላባቶች ያቅኝናያገልጋይ ልጆች ሆነው እነሱም ራሳቸው ያገለገሉ መሆናቸውን ወደፊትም ለሥራ የሚች ሉትን ንጉሠ ነገሥቱ እያስመረመረ ለትውልድ የሚያልፍ ርስተ ጉልት ሊተክላቸውይችላል ።

አንቀጽ 38 ፡ “መሳፍንቶችና አገረገዥዎች የዙፋኑና የዘውዱ አወራረስ በሕግ እንደተወሰነው ሆኖ ጸንቶ እንዲኖር የኢትዮጵያም አንድነቷና ነጻነቷ እንዳይጠፋ የንጉሠ ነገሥቱ ማዕረግ እንደተከበረ እንዲኖር በትጋት እንዲጠብቁ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 39 ፡ “መሳፍንቶች ካልጋ ወራሹ ቀጥለው መስፍን ከሆኑት ከነጋሲ ዘሮች ጋራ በማዕረግና በክብር ከሌሎች ባለማዕረጎች ይልቅ እንዲከበሩና እንዲታፈሩ በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 74 ፡ “ ንጉሠ ነገሥቱና የንጉሠ ነገሥቱ ቤተ ዘመዶች እስካሁን በጃቸው የነበረው ርስትና ገንዘባቸው ወደፊትም እንደ ሕዝቡ በገንዘባቸው የሚገዙት ርስት ሁሉ ስለርስት የቆመው ደንብ እየተጠበቀ ለራሳቸውም የሚጸና ለትውልዳቸውም የሚያልፍ እንዲሆን በሕግ ተወስኗል ።

አንቀጽ 75 ፡ “እንደዚሁ መሳፍንቶችና አገረገዥዎች ሌላውም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ ሁሉ ግናቸውም ዓይነት ወንጀል ከሠራ በሕግ እንደተጻፈው ይቀጣል እንጂ እስካሁን በጁ የነበረውን ወደፊትም በገንዘቡ የሚገዛውን ርስቱን እንዳይነቀል በሕግ ተወስኗል ። ”



# የገባሩ መደብ

## የገባርና የጢሰኛ አንድነትና ልዩነት

የግል ሀብትና የፖለቲካ ሥልጣን የገኘው መደብ ገላጭ ባህርያት እንደሆኑ ሁሉ የአንድ ማህበራዊ ሥርዓት መለያና መታወቂያ አምራቹ መደብ ነው ። በኢትዮጵያ ባለፈው የአጼ መንግስት የፖለቲካ ምዕክልና ዘመን የሕብረተሰቡ ዋናው አምራች ኃይል አራሹ ገባር ስለነበር ዘመኑ የገባር ዘመን የገባር ሥርዓት መባሉ ትክክለኛው ስያሜ ነው ። በመሆኑም በዘመኑ የነበረው ተጨማሪ የባርያ ሥራና ንግድ የዘመኑና የሕብረተሰቡ ገላጭ የኢኮኖሚ መሠረትና መሳሪያ አልነበረም ለማለት ይቻላል ።

በዘመኑ ታሪክ ገባርና ጢሰኛ ሁለቱም አምራች አርሶ አደሮች ስለሆኑ በዚህ ጥናት የሁለቱንም ሥርዓታዊ አንድነትና ልዩነት ለይቶ ማወቅ የዘመኑን ታሪክ በትክክል ለመረዳት የበለጠ ይረዳል ። ባጭር ተግባራዊ ትርጉም ፡ በተጠቀሰው ዘመን ገባር ማለት በራሱ መሬት ጉልበትና የምርት መሳሪያ የወታደር የሹም የመስፍን ፡ የንጉሥ ፡ የመንግስትና የቤተክርስቲያን አገልጋይ የሆነ አርሶ አደር ነው ። ጢሰኛ ግን በሌላ ሰው መሬት ላይ በውላዊ ስምምነት በራሱ ጉልበትና የምርት መሳሪያ እየሠራ የሥራውን ምርት ከባለመሬቱ ጋር በውሉ መሰረት የሚካፈል አምራች ነው ። በሰው መሬት በውል የሰፈረ ጢሰኛ ምንም ጊዜ በባለመሬቱ ውሳኔ ሊነቀል ይችላል ። ገባር ግን ባለመሬት በመሆኑ በፈቃዱ መሬቱን ለቆ ካልሄደ በቀር አይነቀልም ።

በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ከምኒልክ ዘመን እስከ የፋሽስቶች ወረራ ድረስ የገባር ሥርዓት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የደረሰበት ወቅት ነው ። በዚህ በተጠቀሰው የሽግግር ዘመን የገባርና የጢሰኛ ሥርዓታዊ አንድነትንና ልዩነትን በንጽጽር ከዚህ በታች የሚያሳየው ሕጋዊ ዝርዝር ገለጻ የተወሰደው <u>በኢትዮጵያ ከጥንታውያን የፍርድ መዛግብት የተገኘና የተዘጋጀ የፍትሐብሔር ሕጋዊ ድርጅት</u> በሚል ርዕስ በ1945 ከተዘጋጀው የሕግ መጽሐፍ ነው ። ከዚህ በታች ተመርጠው የተጠቀሱት ቁጥሮች ደግሞ የሕጉ ተራ ቁጥሮች ናቸው ። ሕጉ በጠቅላላው ከ1 እስከ 7276 ተራ ቁጥሮች አሉት ።

## የገባር ሕግና ሥራ

ቁ.5349 ፡ የሻለቃ በግዛት በሚያስተዳድርበት ሀገር ውስጥ ገባር ተቆጥሮ ሁለት እጅ ለሻለቃ አንድ እጅ ለመንግሥት ግድቤት እንዲሆን ከተከለለ በኋላ ከመንግስት አስፈቅዶ ግዘግ ሳይቀበል እመንግሥት ግድቤት ውስጥ ገብቶ መቀሜና

ግብር ሊቀበል አይችልም ። ቢቀበልም ተቀብሎ የነበረውን ገንዘብ በደረሰኙ ተሳስቦ ሊመልስ ይገባዋል ።

ቁ.5463 ፤ አንድ ባላባት በሀገሩ ገባር ሳያስቆጥር መንግሥት በፈቀደለት ልክ ከሀያ ወይም ከአስር አንድ ገባር በምርጥ የተፈቀደለት እንደሆነ ያንኑ ባለሲሶ የተፈቀደለትን ገባር ያው ባለርስት የሆነው ባላባት ግብሩን ይቀበላል እንጂ አገረገዡው ሊወ ስድበት አይገባም ።

ቁ.1063 ፤ መልከኛና መልከኛ በገባር ተጣልተው ገባሩ የተከሳሹ ገባር ነኝ ብሎ ቃሉን ቢሰጥ አንደኛው መልከኛ ሌላ መሬት ካለው በመሬቱ ልክ ሊገብር ይገባዋል እንጂ ገባርህ አይደለሁም ብሎ ተከራክሮ ቢረታ አንድነት ግብረአበር ሆኖ የተረታው መልከኛ መልከኝነቱን ገባሩም ርስቱን ሊነቀሉ አይገባቸውም ።

ቁ.5033 ፤ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚገባውን ግብር መንግሥት ለሌላ ሰው ከሰጠው ለመንግሥት የሚገባውን ግብር ገባሮች ይሰጣሉ እንጂ እንቢ ማለት አይገባቸውም ።



7. የሐረሩ ኤሚር አብዱላሂ (1836 - 1910ዓም)
ምንጭ ፤ P. Paulitschke, Harar (1888)



ቁ. 5435 ፤ የገባር መሬት ያለው ሰው ብዙ ጊዜ ለንጉሠ ነገሥቱ ሲገብር ቢኖርም ለመንግሥት የሚገባውን ግብር ለሻለቃም ሆነ ለሌላ ሰው ቢሰጥ ገባሩ ለታዘዘለት ሰው ግብሩን ይሰጣል እንጂ ለንጉሠ ነገሥቱ ግምጃ ቤት ካልሆነ በቀር አልገብርም ማለት አይገባም ።

ቁ. 5363፤ የገባር መሬት ያለው ለባለመሬቱ ሦስት ጊዜ ጭነት መጫን አንድ ጊዜ አንድ ሸክም እንጨት አምጥቶ እከተማ መስጠት አራተኛ በሰኔ ለንጉሥ ጭነት መጫን አንድ ሸክም እንጨት መስጠት ስለ አለበት በታዘዘ ጊዜ እህሉን ተቀብሎ ወይም አልቀበልም ብሎ ሳይጭን እንጨቱን ሳይከፍል የከረመ እን ደሆነ ለባለጉልቱ ዳፈን ይሰጣል ። እንጨቱንም እህሉንም ከነውዝፉ ይሰጣል እንጂ ሳይጭን መክረሙን ካመነ ወይም ከተመሰከረበት ዳፈን አልከፍልም ብሎ ሊከራከር አይገባ ውም ።

ቁ. 5370፤ የገባር መሬት ያለው በዓመት ባመቱ ለተፈቀደለት የሻለቃ ወይም ለባለ ጉልት ማር ሲሰፍር ከአንድ ቁና የሩብ ግማሽ በአንድ ጉንዶ በአንድ ሩብ የደብዳቤ ፀሐፊ ሊሰጥ ይገባ ዋል እንጂ በአንድ መልከኛ አንድ ሩብ ብቻ መክፈል አይ ገባውም ።

ቁ. 5320 በመሬቱ ጭቃ ሹም ሆኖ የመንግሥት ከብት እገባር ዘንድ እንዲመራ ከበላይ ታዞ ለገባሩ ከመራ በኋላ የተመራው ከብት ከገባሩ እጅ ቢጠፋ የጣለው ገባር ኃላፊ ሆኖ ይከፍላል እንጂ በጭቃ ሹምነቱ ከበላይ ባለሥልጣን ታዞ የመራ ጭቃ ሹሙ ሊከፍል አይገባውም ።

ቁ. 5680 ገባር በገባርነቱ ዘብ እንዲጠብቅ ጭቃ ሹም አዞት አዛዡና ታዛዡ በተካካዱበት የትእዛዝ ነገር ጭቃ ሹም ለማዘዝ ሲሄድ ምስክር እየያዘ አይዞርም የራሱ የጭቃ ሹሙ ምስክር ነት ብቻ በቂ ይሆናል እንጂ ሌላ ምስክር አያስፈልግም ።

ቁ. 5477፤ ለቤተ ክህነት ሆነ ለሻለቃ ግብር የሚገብሩ ገባሮች እህ ሉን በሚያስረክቡበት ጊዜ መንግሥስት ባወጣው ባሥራት ቁና ይሰጣሉ እንጂ ተቀባዮቹ በፈቀዱት ለመጠየቅ አይች ሉም ።

ቁ. 5476 ለቤተ ክርስቲያን የሚገብሩ ገባሮች ገዳሙ ያለበት ዕርቀቱ በጣም የበዛ ካልሆነ በቀር እገዳሙ ድረስ ይጭናሉ እንጂ እፋፉ ከደረስን ገዳሙ አለበት ድረስ አንወስድም ለማለት አይችሉም ።

ቁ. 5398 የገባር መሬት ያለው ግብር የሚከፍልበትን ጊዜ አሳልፎ ሲከፍል የዳፈን ጭምር መክፈል ይገባዋል ።

ቁ. 5319 እየገበረ መሬት የሚበላ ሰው አቅም ወይም ገንዘብ ከማጣት የተነሳ ግብሩን ለመገበር አልችልም ለቅቄአለሁ ብሎ ለመልከኛው ሆነ ለባላባቱ መሬቱን የለቀቀ እንደሆነ እየገበረ የሚበላ ቢገኝ በፈቃዱ ይተክልበታል ቢታጣ ግን በጠፍነት በባለሥልጣን እጅ መሬቱ ይቆያል እንጂ ግብሩን አልችልም ብሎ መሬቱን ከለቀቀ በኋላ ያለውን ግብር ሊከፍል አይገደድም ።

ቁ. 5385 ማናቸውም ሰው በገባር መሬቱ ግብር መገበር አቅቶት መሬቱን ለመንግሥት ለቆ መሬቱ በጠፍነት ሲኖር መንግሥት ለሌላ ሰው ከሸጠው ወይም ከሰጠው በኋላ ልዩ የሆነ የንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ከሌለበት በቀር መሬቱን በፈቃዱ ለመውሰድ አይችልም ።

ቁ. 5485 የገባር መሬት ያለው ሰው አልችልም ብሎ የሚለቅ ቢሆን የመሬቱን ሰብል እስከ በላበት ዘመን ድረስ ያለውን ግብር ከፍሎ ይለቃል እንጂ ሰብሉን በልቶ ግብሩን ሳይከፍል ለቆ መሄድ አይችልም ።

ቁ. 1778፤ ገባር መሬቱን ለቆ ሄዶ ሰው በይርጋው ዘመን ልክ ከገበረበት ለገበረው ሰው ይፀናለታል እንጂ ለቆ የሄደው ሰው በኋላ መጥቶ የኔ ከነበረ እወስዳለሁ ለማለት አይችልም ።

## የጢሰኛ ሕግና ሥራ

ቁ. 3273፤ እሰው መሬት ላይ በጢሰኝነት ቤት ሠርቶ የጢሰኝነት ግብር እየገበረ የሚኖር ሰው ባለመሬቱ ልቀቅልኝ ካለው በቀር የጢሰኝነት ግብሩን እየገበረ ይቀመጣል እንጂ የመሬት ግምት ወይም እሌላ ዘንድ ካለው መሬት ነጠሮ ( ምትክ) ልስጥ ብሎ ሊከራከር አይገባውም ።

ቁ. 3272፤ ሌላ ሰው በተቀበለው ማደሪያ መሬት በጢሰኝነት ቤት ሠርቶ የተቀመጠ ሰው ከባለመሬቱ ሳይስማማ የቀረ እንደሆነ ባለመሬቱ ተነስተህ ሂድ ባለው ጊዜ መሄድ አለበት።

ቁ. 3275፤ የገባር መሬት ያለው ሰው ከመልከኛው መሬት ላይ ቤት ሠርቶ የተቀመጠ እንደሆነ መሬቴን ልቀቅልኝ ባለው ጊዜ እገባር መሬቱ ላይ ሄዶ ይሠራል እንጂ ከመልከኛው ሊከራከር አይችልም ።

ቁ. 3225፤ ጢሰኛ ሆነው በገዳም ውስጥ የሚቀመጡ ሰዎች ከገዳሙ ካህናት ጋር ተጣልተው ከጢሰኞቹ አንድ ሰው ሞቶ ገዳዩን



በሞት ፍርድ ቤት ካስፈረደበት በኋላ ጢሰኞቹ ከገዳሙ ካህናቶች ደመኛ ከሆኑ እነሱ አያዙንም በሻለቃ እንታዘዛለን ማለት አይገባቸውም ። መታዘዝን ባይፈልጉ ግን ጢሰኝነታቸውን ለቀው ይሄዳሉ ።

ቁ. 3368፤ በርስቱ ላይ ጢሰኞችን ያስቀመጠ ሰው ተፋልመውኛልና ይነሱልኝ ብሎ ለፍርድ ቤት ካመለከተ ጢሰኞቹ ልዩ ውለታ ከሌላቸው ቤታቸውን አፍርሰው ሀብታቸውን ይዘው ሊለቁ ይገባቸዋል ።

ቁ. 711፤ ባለመሬቱ ጢሰኛውን መሬቴን ልቀቅ ባለው ጊዜ በጢሰኝነት በያዘው መሬት ላይ የተከለው የአትክልት ግምት መሬቱ ከሚያወጣው ዋጋ በላይ ሆኖ ባለመሬቱ የአትክልቱን ግምት መስጠት የማይችል በመሆኑ ጢሰኛው ለባለመሬቱ የመሬቱን ግምት ልስጥ ያለ እንደሆነ ባለመሬቱ አለስልሶ ለጢሰኛው የሰጠው ከሆነ ለሠራተኛና ላትክልቱ ዋጋ ለመሬት ግብር የከፈለው ጢሰኛው ግምቱን ተቀብሎ መሬቱን ይለቃል ።

ቁ. 3287፤ ባለርስቱ በፈቃዱ ካላኖራቸው በቀር በጢሰኝነት ገብተው ከሰው መሬት ላይ እርቦ እያፈሰሱ ግር እየገዙ የቆዩ ሰዎች በዘመን ብዛት እንኳም ይረጋልናል ብለው በግዴታ ለመቀመጥ ወይም ለመከራከር አይችሉም ።

ቁ. 3299፤ በሰው መሬት ላይ ጢሰኛ ሆኖ የሚኖር በጢሰኝነት መሬቱ ላይ ሌላ ጢሰኛ ተክሎ ለራሱ ግብር መቀበል አይችልም ።

ቁ. 3295፤ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን የተጣጣሉ ባለመሬትና ጢሰኛ አብረው ሊኖሩ የማይችሉ ስለሆነ ባለመሬቱ ጢሰኛውን ከመሬቱ ላይ ሊያስነሳው ይገባል ።

ቁ. 3321፤ ጢሰኛ የሆነ ሰው ከሰው ቦታ ቢኖር የውሃ ጉድጓድ ምሶ አትክልት ተክሎ ብዙ ዘመን ቢቀመጥ ባለቦታው ልቀቅ ሲለው የውሃውና ቢፈቅድ የአትክልቱን የቤቱን ግምት ተቀብሎ ይለቃል እንጂ የውሃ ጉድጓድ ምሼ አትክልት ተክዬ ብዙ ዘመን ከተቀመጥኩ አልለቅም ብሎ ሊከራከር አይችልም ።

ቁ. 3418፤ ጢሰኛ የሆነ ከባለርስቱ ተስማምቶ ካልተቀመጠ በግዴታ እቀመጣለሁ ለማለት የተከራከረ እንደሆነ ቤቱን አፍርሶ መሄድ ይገባዋል ።

ቁ. 4394፤ ጢሰኛ ወይም ተጠሪ ሆነው በሌላ ሰው መሬት ላይ የሚኖሩ ሰዎች ያሉበት መሬትም በሚሸጥበት ጊዜ ይኸው የሚሸጠው መሬት ተገባሪ አለቃ ወይም ምንዝር ኖሮበት

ልገዛ ይገባኛል ቢል ሊገዛ ይገባዋል እንጂ ጢሰኛው ወይም ተጠሪ ነበርኩ እኔ እገዛለሁ ብሎ ሊከራከር አይገባውም ።

ቁ. 3425፤ በጢሰኝነት የተቀመጠ ሰው ለባለ መሬት የሚገባውን ግብር መክፈል ካልቻለ ይለቃል እንጂ አልገብርም ወይም አል ለቅም ማለት አይገባውም ።

ቁ. 3447፤ ሲሶ አራሹ በራሱ በሮች አርሶ ዘሩን ዘርቶ ባለመሬቱ አንድ እጅ አራሹ ሁለት እጅ ይካፈላል ።

ቁ. 3454፤ በጢሰኝነት እሰው ቦታ ላይ የተቀመጠ ሰው ስለ ግብሩም ሆነ ስለቦታው አጠባበቅ ባለመሬቱ ዋስ ጥራ ባለው ጊዜ መቀመጥ ቢያስፈልገውም ዋስ ጠርቶ ይቀመጣል እንጂ አልጠራም ማለት አይገባውም ።

ቁ. 3372፤ የተወሰነ መሬት ከባለርስቱ ወስዶ በየዓመቱ እህል ወይም ገንዘብ ለመስጠት በቁጥር የተከናተረ ሰው አዝመራው ቢጠ ፋበትና አንበጣ ሆነ ሌላ ነገር ቢበላበት የተለየ ውል ከሌ ለው ለባለርስቱ ለመስጠት ግዴታ የገባበትን አበል ይከፍ ላል እንጂ በተዘረዘረው ምክንያት ጠፍቶብኛል አልከፍ ልም ለማለት አይችልም ።



8. የከፋው ታቶ ጋኪ ሼሮች (1850 - 1912)
ምንጭ፤ O. Bieber. Kaffa (1948)



## የባርያ ሥራና ንግድ

የባርያ ሥራና ንግድ በኢትዮጵያ ታሪክ ከጥንት ጀምሮ የታወቀ የኢ ኮኖሚና ማህበራዊ ገጽታ ቢሆንም ከአለፈው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ እስከ 1928 ድረስ ከውጭ ብዙ ጠመንጃ ወደ አገሪቱ መግባ ትና ረጅም የመንግሥት ምዕከልና ጦርነት በአገሪቱ የባርያ ሥራንና ንግድን ከመቼውም የበለጠ አሳደገ ። በተለይም በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ በምዕራቡ ዓለምና በዓለም መንግስታቱ ሊግ ዘንድ የባርነት ጥያቄ የኢ ትዮጵያ አንድ ታላቅ ዓለም አቀፍ ጉዳይ ሆነ ። [14]

በተጠቀሰው ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት ቴዎድሮስ በ1840ዎቹ ዮሐንስ በ1870 ዎቹ ምኒልክ በ1880ዎቹ ዘውዲቱና ተፈሪ - ኃይለ ሥላሴ በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ ሥርዓቱን ለማስቀረት የነበራቸውን ዓላማ በብዙ ተከታታይ አዋጆች ቢገልጹም [15] የአገሪቱ ጉልተኛ የገዥው መደብ አባ ላትና መሪዎች ባርነትን ሕጋዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሥርዓት አድር ገው ይደግፉት [16] ስለነበር እስከ ፋሽስቶች ወረራ ድረስ የነገሥታቱ ጸረ ባርነት አዋጆች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አልሆኑም ። በዘመኑ የኢ ትዮጵያ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የእምነትና የትምህርት መሠረት የነበረው የፍትሐ ነገሥት ሕግ እንደሚለው በተፈጥሮ ሁሉም ሰዎች ነጻና እኩል ናቸው ። ነገር ግን የጦርነት ሕግ የተሸነፉትን ሰዎች የአ ሸናፊዎች አገልጋዮች ያደርጋቸዋል ። [17]

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የቤተ መንግሥት ሐኪም የነ በረው ዶክተር ፓል ሜራብ እንደገመተው ፤በ1900 አካባቢ በስልሳ ሺህ ከሚቆጠረው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሀያ ሺህ ወይም 33 በመቶ እንዲሁም ከአሥር ሚሊዮን እስከ አሥራ ሁለት ሚሊዮን ከሚቆጠረው ከአገሪቱ ሕዝብ ከሶስት እስከ አራት ሚሊዮን ወይም 33 በመቶ ባሮች ነበሩ ። [18]

በዘመኑ በኢትዮጵያ የባርያ ዋና ምንጮች የደቡብና ምዕራብ አካባቢ ዎች ሲሆኑ ባሮች የሚገኙባቸው መንገዶች ደግሞ ጦርነትና ፍንጋላ ፤ የባርያ የውጭ ገበያዎች ደግሞ በዛንዚባር ፤ በዜላ ፤ በታጁራ ፤ በበርበራ ፤ በቤይሉልና በምፅዋ የወደብ በሮች ሕንድ ፤ ፋርስ ፤ አረቢያና ቱርክ በመተማ በር ሱዳንና ግብጽ እንደነበሩ ታውቋል ።[19] የተጠቀሱ የጠረፍ በሮች በኋላ የአካባቢውን ጠረፎች በያዙ በእንግሊዝ ፤ በፈረንሳይና በኢ ጣሊያ ኢምፔሪያሊስቶች [20] እስኪዘጉና በአፍሪካ ቀንድ የባርያ ንግድ በአዲስ የውጭ ምንዛሪ ዕቃዎች ማለትም በቡናና በቆዳ እስኪተኩ ድረስ ከኢትዮጵያ በየዓመቱ ቢያንስ በ25,000 የሚቆጠሩ ሰዎች በባ

ልገዛ ይገባኛል ቢል ሊገዛ ይገባዋል እንጂ ጢሰኛው ወይም ተጠሪ ነበርኩ እኔ እገዛለሁ ብሎ ሊከራከር አይገባውም ።

ቁ. 3425፤ በጢሰኝነት የተቀመጠ ሰው ለባለ መሬት የሚገባውን ግብር መክፈል ካልቻለ ይለቃል እንጂ አልገብርም ወይም አል ለቅም ማለት አይገባውም ።

ቁ. 3447፤ ሲሶ አራሹ በራሱ በሮች አርሶ ዘሩን ዘርቶ ባለመሬቱ አንድ እጅ አራሹ ሁለት እጅ ይካፈላል ።

ቁ. 3454፤ በጢሰኝነት እሰው ቦታ ላይ የተቀመጠ ሰው ስለ ግብሩም ሆነ ስለቦታው አጠባበቅ ባለመሬቱ ዋስ ጥራ ባለው ጊዜ መቀመጥ ቢያስፈልገውም ዋስ ጠርቶ ይቀመጣል እንጂ አልጠራም ማለት አይገባውም ።

ቁ. 3372፤ የተወሰነ መሬት ከባለርስቱ ወስዶ በየዓመቱ እህል ወይም ገንዘብ ለመስጠት በቁጥር የተኮናተረ ሰው አዝመራው ቢጠ ፋበትና አንበጣ ሆነ ሌላ ነገር ቢበላበት የተለየ ውል ከሌ ለው ለባለርስቱ ለመስጠት ግዴታ የገባበትን አበል ይከፍ ላል እንጂ በተዘረዘረው ምክንያት ጠፍቶብኛል አልከፍ ልም ለማለት አይችልም ።



8. የከፋው ታቶ ጋኪ ሼሮቾ (1850 - 1912)
ምንጭ ፤ O. Bieber. Kaffa (1948)



## የባርያ ሥራና ንግድ

የባርያ ሥራና ንግድ በኢትዮጵያ ታሪክ ከጥንት ጀምሮ የታወቀ የኢ ኮኖሚና ማህበራዊ ገጽታ ቢሆንም ከአለፈው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ እስከ 1928 ድረስ ከውጭ ብዙ ጠመንጃ ወደ አገሪቱ መግባ ትና ረጅም የመንግሥት ምዕክልና ጦርነት በአገሪቱ የባርያ ሥራንና ንግድን ከመቼውም የበለጠ አሳደገ ። በተለይም በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ በምዕራቡ ዓለምና በዓለም መንግስታቱ ሊግ ዘንድ የባርነት ጥያቄ የኢ ትዮጵያ አንድ ታላቅ ዓለም አቀፍ ጉዳይ ሆነ ።[14]

በተጠቀሰው ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት ቴዎድሮስ በ1840ዎቹ ዮሐንስ በ1870 ዎቹ ምኒልክ በ1880ዎቹ ዘውዲቱና ተፈሪ - ኃይለ ሥላሴ በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ ሥርዓቱን ለማስቀረት የነበራቸውን ዓላማ በብዙ ተከታታይ አዋጆች ቢገልጹም [15] የአገሪቱ ጉልተኛ የገዥው መደብ አባ ላትና መሪዎች ባርነትን ሕጋዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሥርዓት አድር ገው ይደግፉት [16] ስለነበር እስከ ፋሽስቶች ወረራ ድረስ የነገሥታቱ ጸረ ባርነት አዋጆች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አልሆኑም ። በዘመኑ የኢ ትዮጵያ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የእምነትና የትምህርት መሠረት የነበረው የፍትሐ ነገሥት ሕግ እንደሚለው በተፈጥሮ ሁሉም ሰዎች ነጻና እኩል ናቸው ። ነገር ግን የጦርነት ሕግ የተሸነፉትን ሰዎች የአ ሸናፊዎች አገልጋዮች ያደርጋቸዋል ።[17]

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የቤተ መንግሥት ሐኪም የነ በረው ዶክተር ፓል ሜራብ እንደገመተው ፤በ1900 አካባቢ በስልሳ ሺህ ከሚቆጠረው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሀያ ሺህ ወይም 33 በመቶ እንዲሁም ከአሥር ሚሊዮን እስከ አሥራ ሁለት ሚሊዮን ከሚቆጠረው ከአገሪቱ ሕዝብ ከሶስት እስከ አራት ሚሊዮን ወይም 33 በመቶ ባሮች ነበሩ ።[18]

በዘመኑ በኢትዮጵያ የባርያ ዋና ምንጮች የደቡብና ምዕራብ አካባቢ ዎች ሲሆኑ ባሮች የሚገኙባቸው መንገዶች ደግሞ ጦርነትና ፍንጋላ ፤ የባርያ የውጭ ገበያዎች ደግሞ በዛንዚባር ፤ በዜላ ፤ በታጁራ ፤ በበርበራ ፤ በቤይሉልና በምፅዋ የወደብ በሮች ሕንድ ፤ ፋርስ ፤ አረቢያና ቱርክ በመተማ በር ሱዳንና ግብጽ እንደነበሩ ታውቋል ።[19] የተጠቀሱ የጠረፍ በሮች በኋላ የአካባቢውን ጠረፎች በያዙ በእንግሊዝ ፤ በፈረንሳይና በኢ ጣሊያ ኢምፔሪያሊስቶች [20] እስኪዘጉና በአፍሪካ ቀንድ የባርያ ንግድ በአዲስ የውጭ ምንዛሪ ዕቃዎች ማለትም በቡናና በቆዳ እስኪተኩ ድረስ ከኢትዮጵያ በየዓመቱ ቢያንስ በ25,000 የሚቆጠሩ ሰዎች በባ

ርነት በውጭ ዓለም ገበያዎች ይሸጡ እንደነበር በአንድ ጥናታዊ ግምት ተመልክቷል ። [21]

በመስከረም 1914 የኢትዮጵያ መንግስት የዓለም መንግስታት ሊግ አባል በሆን ጊዜ በግዛቱ ውስጥ ባርነትንና የባርያን ንግድ ለማጥፋትና ከዓለም የጸረ ባርነት ማህበር ጋር በቅርብ ተባብሮ ለመሥራት መስማማቱ ይታወሳል ። [22] በዚሁ ዓለም አቀፍ ግዴታ መሠረት የባርያ ንግድን ወዲያውኑ ለማስቀረት የባርያ ሥርዓትን ደግሞ እስከ 1943 ድረስ በሙሉ ከአገሪቱ ለማጥፋት [23] የኢትዮጵያ መንግሥት ያደረገው ጥረት እስከ ፋሽስቶች ወረራ ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ በ1000 ለሚቆጠሩ ባሮች አርነት እንደ አስገኘላቸው ታውቋል ። [24]



9. የወላይታው ካዎ ጦና ጋጋ (1861 - 1901)
ምንጭ ፤ ከሞቱ ፊታውራሪ ደስታ ጦና (1972)



## ምዕራፍ 2 ብሔራዊ ኢንቴሌጀንሲያውና የገባሩ ሥርዓት


## የገባር ሥርዓትና የካፒታሊዝም ቅራኔ

ከአገሪቱ ረጅም ታሪክ አኳያ ሲታይ የኢትዮጵያ የምኒልክ ዘመነ መንግስት ከመካከለኛው ዘመን ወዲህ ያልታየ የሰላምና የጸጥታ ወቅት ነው ። ዘመኑ " ዘመነ መሳፍንት" የተባለው ረጅም የጦር አበጋዞች የሽብርና የስቃይ ዘመን አልፎ በውስጥና በውጭ ተጻራሪ ኃይሎች ላይ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼው መንግስት የፖለቲካ ምዕክልና በተሳካ ሁኔታ የተከናወነበት ፤ በወራሪዎችና በኢምፔሪያሊስቶች ላይ በዲፕሎማሲያዊና በወታደራዊ ትግል የአገሪቱ ሉአላዊነትና ብሔራዊ የግዛት አንድነት በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት የታወቀበትና የተከበረበት ፤ ከዘመኑ የዓለም መንግሥታት ጋር በዲፕሎማሲና በንግድ አዲስ ግንኙነት ተፈጥሮ " ኢትዮጵያውያን ዓለምን ረስተውና በዓለምም ተረስተው ለአንድ ሺህ ዓመት አንቀላፉ " [1] የተባለው ረጅም የገለልተኝነት ዘመን ያከተመበት ወቅት ነው ።

ነገር ግን በሌላ በኩል ከፖለቲካ ሥርዓትና ከአገር ግምባታ አኳያ በዚህ የሰላምና የጸጥታ ዘመን በዘመናዊ ትምህርትና አሠራር አዲስ የሥራ ፖሊሲና ፕሮግራም ሳይቀየስበት በተቃራኒው ከላይ እንደታየው ጥንታዊ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች የበለጠ ተጠናክረው በአገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፉ ። በንጉሣዊ ሹመትና ጉልት በአዲስ የተፈጠሩ የአካባቢ መሳፍንቶችና የጦር አለቆች በአካባቢ ኢኮኖሚ ተደራጅተው በገባርና በባርያ ሥርዓቶች ላይ መሻሻልና ለውጥ የማይፈልጉ ዘመናዊ ትምህርትና አዲስ የፖለቲካ አሳብ የሚቃወሙ ፤ በሥልጣን በአስተዳደርና በግብር ጉዳዮች የማዕከላዊውን መንግስት ሕግና አሠራር የሚጻረሩ የግል ጦር ይዘው የአገር ልማትና ዕድገት የሚቃረኑ ሆኑ ። በዘመኑ የተጠቀሱ መሳፍንቶችንና አገረ ገዥዎችን የድርጅትና የትጥቅ ሁኔታ በሚመለከት ፤ በአድዋ ጦርነት ማግሥት በ1895 ከንጉሡ ጋር ሀያ አምስት የሚሆኑ ታላላቅ አገረ ገዥዎችና የጦር አለቆች በውድ ዋጋ ገዝተው የሰበሰቡት በድምር በ600,000 የሚገመቱ ጠመንጃዎች ነበሩአቸው ። [2] ይህ የ1895 ታላቅ የመሣሪያ ክምችት ከሰባት ዓመታት በፊት በ1888 በአድዋ ጦርነት ጊዜ በመላ አገሪቱ የነበረው የጠመንጃ ብዛት በ100[3]000 የሚገመት እንደነበር ሲታሰብ በድህረ ጦርነት በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ለግል ጦር ግምባታ ብዙ ጥረት እንደ አደረጉ ያሳያል ። ከታሪክ አኳያ ይህ ታላቅ የጦር መሣሪያ ክምችት በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ በአመዛኙ በሥልጣንና በእርስ በርስ ጦርነት ዋለ።

ርነት በውጭ ዓለም ገበያዎች ይሸጡ እንደነበር በአንድ ጥናታዊ ግምት ተመልክቷል ። [21]

በመስከረም 1914 የኢትዮጵያ መንግስት የዓለም መንግስታት ሊግ አባል በሆነ ጊዜ በግዛቱ ውስጥ ባርነትንና የባርያን ንግድ ለማጥፋትና ከዓለም የጸረ ባርነት ማህበር ጋር በቅርብ ተባብሮ ለመሥራት መስማማቱ ይታወሳል ። [22] በዚሁ ዓለም አቀፍ ግዴታ መሠረት የባርያ ንግድን ወዲያውኑ ለማስቀረት የባርያ ሥርዓትን ደግሞ እስከ 1943 ድረስ በሙሉ ከአገሪቱ ለማጥፋት [23] የኢትዮጵያ መንግሥት ያደረገው ጥረት እስከ ፋሽስቶች ወረራ ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ በ1000 ለሚቆጠሩ ባሮች አርነት እንደ አስገኘላቸው ታውቋል ። [24]



9. የወላይታው ካዎ ጦና ጋጋ (1861 - 1901)
ምንጭ ፤ ከሞቱ ፊታውራሪ ደስታ ጦና (1972)



## ምዕራፍ 2 ብሔራዊ ኢንቴሌጂንሲያውና የገባሩ ሥርዓት

### የገባር ሥርዓትና የካፒታሊዝም ቅራኔ

ከአገሪቱ ረጅም ታሪክ አኳያ ሲታይ የኢትዮጵያ የምኒልክ ዘመነ መንግስት ከመካከለኛው ዘመን ወዲህ ያልታየ የሰላምና የጸጥታ ወቅት ነው ። ዘመኑ " ዘመነ መሳፍንት" የተባለው ረጅም የጦር አበጋዞች የሽብርና የስቃይ ዘመን አልፎ በውስጥና በውጭ ተጻራሪ ኃይሎች ላይ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼው መንግስት የፖለቲካ ምዕክልና በተሳካ ሁኔታ የተከናወነበት ፤ በወራሪዎችና በኢምፔሪያሊስቶች ላይ በዲፕሎማሲያዊና በወታደራዊ ትግል የአገሪቱ ሉአላዊነትና ብሔራዊ የግዛት አንድነት በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት የታወቀበትና የተከበረበት ፤ ከዘመኑ የዓለም መንግሥታት ጋር በዲፕሎማሲና በንግድ አዲስ ግንኙነት ተፈጥሮ " ኢትዮጵያውያን ዓለምን ረስተውና በዓለምም ተረስተው ለአንድ ሺህ ዓመት አንቀላፉ " [1] የተባለው ረጅም የገለልተኝነት ዘመን ያከተመበት ወቅት ነው ።

ነገር ግን በሌላ በኩል ከፖለቲካ ሥርዓትና ከአገር ግምባታ አኳያ በዚህ የሰላምና የጸጥታ ዘመን በዘመናዊ ትምህርትና አሠራር አዲስ የሥራ ፖሊሲና ፕሮግራም ሳይቀየስበት ቡተቃራኒው ከላይ እንደታየው ጥንታዊ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች የበለጠ ተጠናክረው በአገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፉ ። በንጉሣዊ ሹመትና ጉልት በአዲስ የተፈጠሩ የአካባቢ መሳፍንቶችና የጦር አለቆች በአካባቢ ኢኮኖሚ ተደራጅተው በገባርና በባርያ ሥርዓቶች ላይ መሻሻልና ለውጥ የማይፈልጉ ዘመናዊ ትምህርትና አዲስ የፖለቲካ አሳብ የሚቃወሙ ፤ በሥልጣን በአስተዳደርና በግብር ጉዳዮች የማዕከላዊውን መንግስት ሕግና አሠራር የሚጻረሩ የግል ጦር ይዘው የአገር ልማትና ዕድገት የሚቃረኑ ሆኑ ። በዘመኑ የተጠቀሱ መሳፍንቶችንና አገረ ገዥዎችን የድርጅትና የትጥቅ ሁኔታ በሚመለከት ፤ በአድዋ ጦርነት ማግሥት በ1895 ከንጉሡ ጋር ሀያ አምስት የሚሆኑ ታላላቅ አገረ ገዥዎችና የጦር አለቆች በውድ ዋጋ ገዝተው የሰበሰቡት በድምር በ600,000 የሚገመቱ ጠመንጃዎች ነበሩአቸው ። [2] ይህ የ1895 ታላቅ የመሣሪያ ክምችት ከሰባት ዓመታት በፊት በ1888 በአድዋ ጦርነት ጊዜ በመላ አገሪቱ የነበረው የጠመንጃ ብዛት በ100,000 የሚገመት እንደነበር ሲታሰብ በድህረ ጦርነት በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ለግል ጦር ግምባታ ብዙ ጥረት እንደ አደረጉ ያሳያል ። ከታሪክ አኳያ ይህ ታላቅ የጦር መሣሪያ ክምችት በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ በአመዛኙ በሥልጣንና በእርስ በርስ ጦርነት ዋለ።

በሌላ በኩል በዘመኑ በኢትዮጵያ መንግስትና ባለሥልጣኖች ዘንድ ለዘመናዊ ትምህርትና አዲስ የፖለቲካ አሳብ ዕድገት የተደረገው ጥረት ለፖለቲካ ሥልጣንና ለጦር መሣሪያ ግምባታ ከተሰጠው ትኩረት ያነሰ ነበር ። በዚህ ነገር ዘመናዊ የአገር ግምባታ ዋናው መሣሪያ ዘመናዊ ትምህርት እንደሆነ ከሥልጣኔ ልምድ በተጨባጭ የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ ዘመናዊ ትምህርትና አዲስ የፖለቲካ አሳብ (ለምሳሌ የሃይማኖትና የባሮች ነጻነት ፤ ሕገ መንግስት ፤ ዲሞክራሲ ፤ የዜጎች መብት ፤ ሕዝባዊ ሥልጣን ሪፑብሊክ . . . ወዘተ ) በዘመኑ በአገሪቱ በመስፋፋት ላይ የነበሩ የገባርና የባርያ ሥርዓቶችን የሚቃረን ሆኖ በመገኘቱ በኢትዮጵያ መንግስትና ባለሥልጣኖች ዘንድ ከ1900 በፊት በጥሞና አልተፈለገም ።

በዚህ ረገድ ለምሳሌ አንደኛ በዘመኑ ለሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ከሃይማኖታቸው ጋር ዘመናዊ ትምህርት ማስተማር በፍጹም የተከለከለ ነበር [4] ። ሁለተኛ በምኒልክ ዘመነ መንግስት ፍጻሜ በ1901 ለወጣት መሳፍንት የውጭ አገር ቋንቋና የመንግስት አስተዳደር ሥራ ለማስተማር የምኒልክ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ መሀል ከተማ እሪ በከንቱ ድልድይ አጠገብ በስዊሳዊዉ አልፍሬድ አልግ የኢትዮጵያ መንግሥት አማካሪ ግቢ ከመከፈቱ በፊት በአገሪቱ መንግሥት በኩል አንድም ዘመናዊ ትምህርት ቤት አልተከፈተም ። ሶስተኛ በዘመኑ በልዩ ልዩ መንገዶችና ምክንያቶች በውጭ አገርና በኤርትራ በሚሲዮናውያን ዘንድ ዘመናዊ ትምህርት ተምረው አገራቸውን በትምህርት መሣሪያ ለማገልገል ለሚፈልጉ ወጣት ኢትዮጵያውያን ከአስተርጓሚነትና በነጋድራስ ማዕረግ ከጉምሩክ ሥራ በስተቀር በሌላ የመንግስት ሥራ የሥልጣንና የአላፊነት ሥፍራ አይሰጣቸውም ነበር ። ባጭሩ በጥቅምት 1909 በተፈሪ መኮንን በተካሄደው ኩዴታ የመንግስት አመራር ለውጥ እስኪደረግ ድረስ በዘመኑ በጉልተኛ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች ዘንድ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያን የነበራቸው አዲስ የአገር ግምባታ ፖሊሲና የተግባር ፕሮግራም ተቀባይነት አላገኘም ። ትምህርትና ምሁር በቤተ መንግስትና በመንግስት መሥሪያ ቤት ሥራና ሥፍራ አልነበራቸውም ።

በሌላ በኩል በምሁራን ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (1860-1939) ፤ የአንኮበሩ አስቤ ኃይሉ ፤ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ( 1878- 1911) እና ብላታ ደሬሳ አመንቴ (1860- 1868) ጽሑፎች በተለይ እንደ ተገለጸው ፤ በዘመኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ኢንቴሌጀንሲያው የአገር ግምባታ ፖሊሲና የተግባር ፕሮግራም ጥንታዊ የገባር ሥርዓትን አስወግዶ በምትኩ በጃፓን ሞዴል በዘውዳዊ መንግስት አመራር ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባታ ነው ።



በዚህ ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባታ አቋሙ የኢትዮጵያ ኢንቴሌጀንሲያ ማለትም የተማረው ክፍል በ1902 የአልጋ ወራሽ ልጅ ኢያሱን [5] አንጃ በእቴጌ ጣይቱ አንጃ ላይ በ1909 ኩዴታ ደግሞ በቀድሞ የምኒልክ ባለሥልጣኖችና የአካባቢ መሳፍንቶች ላይ የተፈሪ መኮንንን የተሳካ ተራማጅ አሳብና አመጽ ደገፈ ። [6] በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ በጉልተኛ የገዥ መደብ መሪዎችና አባሎች መካከል በተካሄደው ረጅምና መራራ የሥልጣን ትግል ኢንቴሌጂንሲያው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በንግሥት ዘውዲቱ ደጋፊ የቀድሞ ሹማምንቶች ፤ መሳፍንቶችና የጦር አለቆች ወግ አጥባቂ አንጃ ላይ ከአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ተራማጅ የፖለቲካ አንጃ ጐን ተሰለፈ [7] ።

## የአፈወርቅ ገብረእ.የሱስ ትምህርት

በ1901 ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረየየሱ Guide da Voyageur ማለትም የመንገደኛው መመሪያ ፤ እንዲሁም ከሀያ ዓመታት በኋላ በ1921 “ መዲወኤቦ ” ማለትም “ የአውሮፓውያን የመካከለኛ ዘመን ” በሚል ርዕስ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ባሳተሙት ጽሑፍ በኢትዮጵያ ገባር ሥርዓት ጉልተኛ ነገሥታትን ፤ መሳፍንቶችን ፤ መኳንንቶችን ሹማምንቶችን ወታደሮችን በሚመለከት የሚከተለውን መሠረታዊ ሂስ አቅርበው ለኢትዮጵያ የካፒታሊዝም አስፈላጊነቱን አስረድቷል ። ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ በመንገደኛው መመሪያ በኢትዮጵያ ገጸ ምድር ከአንድ አውሮፓዊ መንገደኛ ጋር እየተወያዩ ባቀረቡት ሥርዓታዊ ሂስ ፤ በገባሩ ጉልበትና ምርት የሚኖሩ የኢትዮጵያ መሳፍንቶችን ፤ መኳንንቶ ችን ፤ ሹማምንቶችን ፤ ወታደሮችን ነገሥታትን ፤ ማህበራዊ መሠረትና ተግባር እንደሚከተለው አጋልጧል ። በነጋድራሱ ቃል ፤ የኢትዮጵያ ሹማምንቶች ፤

1. “ ሥራቸው መብላት ፤ መጠጣት ፤ መተኛት እንደ ፋሲካ ሙክት መወፈር ብቻ ነው ። እሄ ሁሉ ከደሀው ጠዋትና ማታ ጨክነው በሚወርሱት ገንዘብ ነው ። [8]

2. “ የያገሩ ጭቃሹም ደሀውን በግድ እያዘዘ እንጀራውን ማሩን ሙክቱን እንቁላሉን ዶሮውን ጠጁን ጠላውን . . . እንዲአዋጣና እንዲሰጣቸው ያደርጋል ። [9]

3. “ አሁን የምናልፍበትን ሁሉ አገር አስተውለው ይዩትና ያበሻ ነገሥታት አገዛዝ ማወቅና አለማወቃቸውን በዚሁ ይፈርዱታል ። ተዚህ ምን የሚታይ ነገር አለ ። ደመቅ ያለ ከተማና ሞቅ ያለ መንደር የለም ። ላይን የሞላ እርሻ የለም ። በመንገዱ ምንም ሰው አይዛወርበትም ። በየሥፍራው የሚታየው እልፍ አእላፍ ወፍና እረጃጅም ሳር እሾህ ቅጠል ብቻ ነው ። ሌላ የለም ። ” [10]

4. " እንዲህ ያለ ማለፊያ አገር ይህነን የመሰለ ለምለም መሬት ተገ ዥዎቹ ከፋት ካልሆነ በቀር እንዲህ ምድረበዳው እንዲህ ድም ጥማጡ ባልወጣም ነበር ። መሀል አበሻም እንዲሁ ባዶውን ቀር ቷል ። መሬቱም እንዲያው ወድቋል ። " [11]

5. " . . ተመዝረፍና ደሀ ተማስጨነቅ በቀር ሌላ ምንም ስራ የማያ ውቅ የንጉሡ ሠራዊት ሁሉ በደሀው ላይ ተዘፍዝፎ ይኖራል ። ይሄው ደሀ በዚህ የተነሳ የወታደሩን ጡር ዘላለም የማይችለው ሲሆን ጊዜ እርስቱን እየተወ ተሰፋውን ቆርጦ ስደቱን ይሄዳል ። [12]

6. " ተማቱሳላ ያረጀ ምስጢሩ ተባቤል ከተማ ቋንቋ አብሶ ውጥንቅ ጡ የወጣ ፍትሐ ነገሥት የሚባል አንድ መጽሐፍ አለ ። ይሄ መጽሐፍ ግን እንደ ዛሬ የሰው እውቀት ባልተሰፋበት ጥበብ ባልተ ገለጠበት ጊዜ ከምስር ( ግብጽ) ባረብ ቋንቋ ተጽፎ ነበር ። ኋላ ደግሞ በግዕዝ ተቀድቶ ላበሻ መንግስት መጣ ። የቀድሞ ዘመን ሁሉ ሕግ እንደገና በጣም ታልታረመና ለዛሬ ዘመን ኑሮ እንዲስማማ ታልሆነ በቀር ለዛሬ ዘመን ሰው ለመሆን የተገባ አይደለም ። " [13]

7. " በኢትዮጵያ ነገሥታት ፊት ምንም ፍትሐ ነገሥት ምንም የእው ነተኛ ፍርድ የለም ። እነሱ እንደፈቃዳቸው ነው የሚያደርጉት። ስለምን በማናቸውም ነገር በተቀጡ ቁጥር ምንም በደል ያልተገ ኘበትን ሰው ቢቀጡ ቢፈልጡ ይሆንላቸዋል ። . . . . እኒሁ ነገሥ ታት እንዲህ ያለውን ጭካኔ ሲያደርጉ በዙሪያቸው አንዳንድ ወዳ ጆችም ቢኖሯቸው አንድም ቃል ለመናገር ምንም አይደፍሩም ። እነሱም ተመከራ እንዳይወድቁ ይፈራሉ ። " [14]

8. " ባንድ ወገን ጦርነት ባንድ ወገን እራቡ ሕዝቡን እየፈጀው አገ ሩስ እንዴት ይልማ ሰውስ እንዴት ይራባ ። " [15]

9. " . . . ባበሻ አንዱ ላንዱ ለጥ ብሎ መገዛት አያውቅም ። ንጉሥ በተለወጠ ቁጥር አንዱ አሸንፎ እስኪነግሥ ድረስ እርስ በርሱ መላ መጥና መዋጋት ብቻ ነው ። " [16]

10. " ባገራችን እንደዚህ ሰው አንሶ ጠፉ በዝቶ ላየ ለሩቅ አገር ሰው ያገራችን ያበሻ ሴቶች መውለድ የማያውቁ መካኖች በመሰለው። እንደ እውነት ግን የሰው እያደረ ማነሱና አገራችን የመከነው በወ ታደሩ አህዛብ ነት በሹማምንቱና በባለጉልቱ የደሀ ገንዘብ ለመው ረስ ባለመጥገብ ባልተገባቸው አልጋ በተቀመጡ ነገሥታት አረ መኔነት የተነሳ ነው ። " [17]

11. " ታመት አራትና አምስት ወር ሙሉ በየቤቱ ተሰሪ እያገቡ ደሀው በግድ ወታደሩ የፈለገውን ሁሉ ሳያጓድል እንዲቀልብ ያደርጉ ነበረ ። ደሀው ግን የነበረውን ሁሉ ወረት በዚሁ በተሰሪው ቀለብ ጨርሶ ለወታደሩ እንጀራ ቢያጣና እህል ቢጠፋበት ያ ተሰሪነት የገባው ወታደር በግድ እህል ታልወለደህ እያለ የፊጥኝ አስሮ ይገ



ርፈው ነበር ። ብዙ ጊዜም ሌሊቱን ተውርጭ ቀኑን ተጸሐይ ያው ለው ያሳድረው ነበር ። " [18]

12. " ያገራችን ባላገር በብርቱ ሥራ ወዳጅ ነው ። ለማረስና ለመቆ ፈር ደከምሁን አያውቅም ። ወታደሩ ነው በባላገሩ ተመሳቅና ተመ ሳለቅ መከራ ተማሳየት ተመዝረፍ በቀር ምንም መሥራት የማይ ወድ ሰነፍ ። " [19]

13. " በወዙ ያበቀለው ፍሬ ለወታደሩ ቀለብ ተሆን ተጨንቆ ተጠቦ ያሳደገው ከብቱ ለባለጉልቱ መወፈሪያ ተሆን የርቢ ላምና የርሻ በሬ እለው ጥበታለሁ ብሎ ያኖረው ፈረስና በቅሎ ተመልምሎ ላገረ ገዥ ተሄደ ተገጠር ሲያርስና ሲቆፍር ወሎ ደከሞት እርፋለሁ ሲል በቤቱ ኃይለኛ ወታደር ገብቶ ባለቤቱ ሆኖ ሲበይንበት ታገኘው ምን ያዳከመዋል በከንቱ ። " [20]

14. " አበሻ ለመኖር አንድ የሚሻለው ነገር ወታደር መሆን ብቻ ነው። እሄው መሆኑ እውነት ደስ ያለ ትዳር ለማግኘት አይደለም ። ነገር ግን ሲዘረፉና ሲገረፉ ከመኖር ሌላውን ሲዘርፉና ሲገፉ መኖር ይሻላል ለማለት ነው ። " [21]



10. የጂማው አባጅፋር አባጉመል (1853-1925)

ምንጭ ፤ የፕሬስ መምሪያ ዲፓርትመንት ክፍል

15. " ባለ ጉልትና የሻለቃ በየራሱ የገዛ ዜጋውን መናኘት ይቻለዋልና የደሀውን ከብት መውረስ ያገረው እንደሆነ ምንም በዚህ ዜጋ በደልና አበሳ ባይኖርበት ተዚያው በዚያው በምናምን ሰበብ ጥፋ ተኛ ሆኖ ይገኛል ። ቀጥሎም ይታሰርና ይወረስ ቤታ ተብሎ ይፈረ ድበታል ። [22]

4. “ እንዲህ ያለ ማለፊያ አገር ይህነን የመሰለ ለምለም መሬት ተገ ኘሮዎቹ ከፋት ካልሆነ በቀር እንዲህ ምድረበዳው እንዲህ ድም ጥማጡ ባልወጣም ነበር ። መሀል አበሻም እንዲሁ ባዶውን ቀር ቷል ። መሬቱም እንዲያው ወድቋል ። ”[11]

5. “ . . ተመዝረፍና ደሀ ተማስጨነቅ በቀር ሌላ ምንም ስራ የማያ ውቅ የንጉሡ ሠራዊት ሁሉ በደሀው ላይ ተዘፍዝፎ ይኖራል ። ይሄው ደሀ በዚህ የተነሳ የወታደሩን ጡር ዘላለም የማይችለው ሲሆን ጊዜ እርስቱን እየተወ ተስፋውን ቆርጦ ስደቱን ይሄዳል ።[12]

6. “ ተማቱሳላ ያረጀ ምስጢሩ ተባቤል ከተማ ቋንቋ አብሶ ውጥንቅ ጡ የወጣ ፍትሐ ነገሥት የሚባል አንድ መጽሐፍ አለ ። ይሄ መጽሐፍ ግን እንደ ዛሬ የሰው እውቀት ባልተሰፋበት ጥበብ ባልተ ገለጠበት ጊዜ ከምስር ( ግብጽ) ባረብ ቋንቋ ተጽፎ ነበር ። ኋላ ደግሞ በግዕዝ ተቀድቶ ላበሻ መንግስት ወጣ ። የቀድሞ ዘመን ሁሉ ሕግ እንደገና በጣም ታልታረመና ለዛሬ ዘመን ኑሮ እንዲስማማ ታልሆነ በቀር ለዛሬ ዘመን ሰው ለመሆን የተገባ አይደለም ። ”[13]

7. “ በኢትዮጵያ ነገሥታት ፊት ምንም ፍትሐ ነገሥት ምንም የእው ነተኛ ፍርድ የለም ። እነሱ እንደፈቃዳቸው ነው የሚያደርጉት። ስለምን በማናቸውም ነገር በተቀጡ ቁጥር ምንም በደል ያልተገ ኘበትን ሰው ቢቀጡ ቢፈልጡ ይሆንላቸዋል ። . . . . እኒሁ ነገሥ ታት እንዲህ ያለውን ጭካኔ ሲያደርጉ በዙሪያቸው አንዳንድ ወዳ ጆችም ቢኖሯቸው አንድም ቃል ለመናገር ምንም አይደፍሩም ። እነሱም ተመከራ እንዳይወድቁ ይፈራሉ ። ”[14]

8. “ ባንድ ወገን ጦርነት ባንድ ወገን እራቡ ሕዝቡን እየፈጀው አገ ሩስ እንዴት ይልማ ሰውስ እንዴት ይራባ ። ”[15]

9. “ . . . ባበሻ አንዱ ላንዱ ለጥ ብሎ መገዛት አያውቅም ። ንጉሥ በተለወጠ ቁጥር አንዱ አሽንፎ እስኪነግሥ ድረስ እርስ በርሱ መሳ መጥና መዋጋት ብቻ ነው ። ”[16]

10. “ ባገራችን እንደዚህ ሰው አንሶ ጠፉ በዝቶ ላየ ለሩቅ አገር ሰው ያገራችን ያበሻ ሴቶች መውለድ የማያውቁ መካኖች በመሰለው። እንደ እውነት ግን የሰው እያደረ ማነሱና አገራችን የመከነው በወ ታደሩ አህዛብ ነት በሹማምንቱና በባለጉልቱ የደሀ ገንዘብ ለመው ረስ ባለመጥገብ ባልተገባቸው አልጋ በተቀመጡ ነገሥታት አረ መኔነት የተነሳ ነው ። ”[17]

11. “ ታመት አራትና አምስት ወር ሙሉ በየቤቱ ተሰሪ እያገቡ ደሀው በግድ ወታደሩ የፈለገውን ሁሉ ሳያጓድል እንዲቀልብ ያደርጉ ነበረ ። ደሀው ግን የነበረውን ሁሉ ወረት በዚሁ በተሰሪው ቀለብ ጨርሶ ለወታደሩ እንጀራ ቢያጣና እህል ቢጠፋበት ያ ተሰሪነት የገባው ወታደር በግድ እህል ታልወለድህ እያለ የፈጥኝ አስሮ ይገ



ርፈው ነበር ። ብዙ ጊዜም ሌሊቱን ተውርጭ ቀኑን ተጸሐይ ያው ለው ያሳድረው ነበር ። ”[18]

12. “ ያገራችን ባላገር በብርቱ ሥራ ወዳጅ ነው ። ለማረስና ለመቆ ፈር ደከምሁን አያውቅም ። ወታደሩ ነው በባላገሩ ተመሳቅና ተመ ሳለቅ መከራ ተማሳየት ተመዝረፍ በቀር ምንም መሥራት የማይ ወድ ሰነፍ ። ”[19]

13. “ በወዙ ያበቀለው ፍሬ ለወታደሩ ቀለብ ተሆነ ተጨንቆ ተጠቦ ያሳደገው ከብቱ ለባለጉልቱ መወፈሪያ ተሆነ የርቢ ላምና የርሻ በሬ እለው ጥበታለሁ ብሎ ያኖረው ፈረስና በቅሎ ተመልምሎ ላገረ ገዥ ተሄደ ተገጠር ሲያርስና ሲቆፍር ወሎ ደክሞት አርፋለሁ ሲል በቤቱ ኃይለኛ ወታደር ገብቶ ባለቤቱ ሆኖ ሲበይንበት ታገኘው ምን ያዳክመዋል በከንቱ ። ”[20]

14. “ አበሻ ለመኖር አንድ የሚሻለው ነገር ወታደር መሆን ብቻ ነው። እሄው መሆኑ እውነት ደስ ያለ ትዳር ለማግኘት አይደለም ። ነገር ግን ሲዘረፉና ሲገረፉ ከመኖር ሌላውን ሲዘርፉና ሲገፉ መኖር ይሻላል ለማለት ነው ። ”[21]



10. የጂማው አባጅፋር አባጉመል (1853-1925)

ምንጭ ፤ የፕሬስ መምሪያ ፎቶግራፍ ክፍል

15. “ ባለ ጉልትና የሻለቃ በየራሱ የገዛ ዜጋውን መዳኘት ይቻለዋልና የደሀውን ከብት መውረስ ያማረው እንደሆነ ምንም በዚህ ዜጋ በደልና አበሳ ባይኖርበት ተዚያው በዚያው በምናምን ሰበብ ጥፋ ተኛ ሆኖ ይገኛል ። ቀጥሎም ይታሰርና ይወረስ በቃ ተብሎ ይፈረ ድበታል ።[22]

16. “ ባለ ጉልትና አገረ ገዥ የሚሉት ልማድ እስታለ ድረስ በኢትዮጵያ
መንግስት ትክክልነትና እንደልብ ተናግሮ መኖር እስከመቸ
ውም አይኖርም ። ” [23]

በ1901 ነጋድራስ አፈወርቅ ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሑፋቸው የገ
ባር ሥርዓትን የመከራና የብዝበዛ ባህርይ በትክክል አጋልጠዋል ። በ1921
“ መዲወኤቦ ” በሚል ርዕስ በቀረበው ጽሑፋቸው ደግሞ በኢትዮጵያ
የገባር ሥርዓትና በጥንታዊ የአውሮፓ የፊውዳሊዝም ሥርዓት መካከል
ያለውን ሥርዓታዊ ተመሳሳይነት በብቃት አገናዝበው በኋላ የአውሮፓው
ፊውዳሊዝም በትምህርት መሳሪያ በአዲሱ የካፒታሊዝም ሥርዓት እን
ዴት እንደ ተደመሰሰ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በታሪካዊ ትንተና እንደሚ
ከተለው ገለጹ ።

በነጋድራሱ የታሪክ ጥናት መሠረት ፤ በዘመነ ክርስትና ከ395 እስከ
1450 ድረስ በነበረው በአውሮፓውያን የመካከለኛው ዘመን የአውሮፓ
አህጉርና ሕዝብ በየአውራጃው በየተራራው በየጕጡ በየወንዙና በየደሴቱ
ተከፋፍሎ ማርኪዜ ፤ ባሮኔ ፤ ኮንቴ ፤ ቪስኮንቴ ፤ እየተባሉ የሚጠሩ ፊው
ዳል ባላባቶች ፤ መሳፍንቶች ፤ ጉልተኞችና አገረገዥዎች በአጀብ በወ
ታደር በገንዘብ በሥልጣንና በጌጥ ተጀንነው በታላቅ ትዕቢትና ትምክ
ህት “ ሕዝቡን እንደፈቀዳቸው ሲገዙ ሲዳኙ . . ይኖሩ ነበረ ። ” [24]

ይህ የነጋድራሱ ታሪካዊ ትምህርት በ1921 የኢትዮጵያ ጉልተኛ
የገዥው መደብ መሪዎችንና አባሎችን በስም እየጠሩ የመስደብ ያህል
ግልጽ ወቀሳና ስድብ እንደሆነ ተቆጥሮ በወቅቱ አንድ የሥርዓቱ ደጋፊ
የተጠቀሰው ጽሑፍ ጸረ መሳፍንት ቅስቀሳ ነው በማለት በደራሲው ላይ
በጋዜጣ ብርቱ የተቃውሞ ድምጹ አሰምቶ ነበር ።

ነጋድራሱ የአውሮፓ ፊውዳሊዝምን ታሪካዊ መነሻና ውድቀት
በሚመለከት ጨምረው እንዳብራሩት ፤ በአህጉሩ ከጊዜ በኋላ ትምህርትና
ሥልጣኔ እያደገና እየተስፋፋ በመሄዱ የአውሮፓ ፊውዳል የባላባት ክፍ
ሎችና ግዛቶች በጠንካራ ማዕከላዊ ነገሥታት ጦር እየተደመሰሱ በምት
ካቸው አዳዲስ ዘመናዊ ካፒታሊስት ብሔረ - መንግስታት ተፈጠሩ ።

በደራሲው እንደተባለው ፊውዳላዊ የመሳፍንቶች አጀብና የግል
ጦር ቀስ በቀስ እየቀረ ሄደ ። በአንጻሩ ደግሞ በአውሮፓ ከአዲስ የኢኮኖሚ
ልማት አኳያ እርሻው ሰፋ ። ንግዱ ተስፋፋ ። አገር ከበረ ። ችጋርና ድህ
ነት ጠፋ ። ገበያ አደገ ። ለደሀው አለፈለት ። ማህበራዊ ፍትህ ተገኘ ።
ንጉሦችም ከሕዝባቸው ፍቅርና ክብር እምነትና ምስጋና ባንድ ላይ አገኙ።
ሕዝቡ እንደዚህ ራሱን አገሩንና ንጉሡን የሚረዳበት እውቀትና ሥልጣኔ
እያደገ እየሰፋ መጣ።በዚህ የዕድገት ሂደት ለአውሮፓ ሕዝብ ሕጋዊና ብሔ
ራዊ የዜግነት ነጻነትና መብት በእንግሊዝ አገር በ1208 ፤ በፈረንሳይ አገር
በ1807 በኢጣሊያ አገር በ1840 ተገኘ በማለት ነጋድራሱ አስረድተዋል።



## የአስቤ ኃይሉ ትምህርት

በ1919 “ ስለ መንግስትና ሕዝብ ጉዳት ” በሚል ርዕስ ጸሐፊው
አስቤ ኃይሉ በብርሃንና ሰላ ጋዜጣ የገባር ሥርዓት በአንድ በኩል በራሱ
በአምራቹ ገባር ላይ ያደረሰውንና የሚያደርሰውን የሕይወትና የንብረት
ጥፋት በሌላ በኩል ደግሞ የገባር ባለቤቶች የሆኑት ጉልተኞች የሕብረ
ተሰቡን የመሬት ሀብት ከገባሩ ጉልበት ጋር ለራሳቸው በመጠቀም በገባ
ሩም በወታደሩም ፤ በሕብረተሰቡም በመንግስቱም ላይ ያመጡትን የኢ
ኮኖሚ ጉዳት በዝርዝር አስረድተው ጥንታዊው የገባር ሥርዓት በአገሪቱ
ላይ ከዚህ የበለጠ ጥፋት ገና ሳያስከትል ራሱ በአስቸኳይ ተደምስሶ በካ
ፒታሊዝም ሥርዓት እንዲተካ ብሔራዊ የለውጥ አሳብ አቅርበዋል ።

በወቅቱ በአስቤ ኃይሉ ግምት የአገሪቱ ጉልተኛ መኳንንቶች በድ
ምር በ100,000 የሚቆጠር የጋሻ መሬት በርስትነትና በማደሪያነት ስሪት
ይዘው በመሬታቸው ላይ ግን ለመንግስቱ የግብር የጉልበትና የአሥራት
አገልግሎቶችን አይከፍሉበትም ነበር ። በተጨማሪም ጉልተኞቹ በምር
ትና በጉልበት ከገባሩ አስጨንቀው የሚሰበስቡትን ሀብት ለራሳቸው
ከመብላትና ከመጠጣት በስተቀር ለአገርና ለሕብረተሰቡ በሚጠቅም
ሥራ ላይ አያውሉም ነበር ። በመሆኑም ጉልተኞች በአገሪቱ ለገባሩ አር
ነትና ለመንግስቱም የልማት ፖሊሲና ሥራ ታላቅ የእንቅፋት ድንጋይ
ናቸው በማለት ጸሐፊው ሥርዓታዊ ክስ መሰርቶባቸዋል ።

በአስቤ ኃይሉ የተገለጸው በጣም አስጨናቂና አሰቃቂ የሆነ የገባ
ሩና የጉልተኛው ሥርዓታዊ ግንኙነት በፋሽስቶች ወረራ ዋዜማ ሰሜን
ሸዋ ጨምሮ በመላው መሀልና ደቡብ በተለይ ተስፋፍቶ የነበረው የገባር
ሥርዓት ነው ። በደራሲው ገለጻ መሠረት በወቅቱ በመሀል አገር በተለይም
በሸዋ ከገባሩ ለመንግስትና ለጉልተኛ የግብር የጉልበት ፤ የምርትና የአ
ሥራት አገልግሎቶችን የሚሰበስቡ የወረዳ ምስለኔ የአሥራት እህል
ጸሐፊና የእህል ጐተራ ሹም የተባሉ ቀማኛ የበታች ሹማምንቶችነበሩ ።

በዘመኑ ጸሐፊው አስቤ ኃይሉ እንደመዘገቡት ፤ የወረዳ ምስለኔ ፤
የአሥራት እህል ፀሐፊና የእህል ጐተራ ሹም ለመንግስቱ ለጉልተኛውና
ለወታደሩ የሚሆኑ የጉልበት የማር ፤ የእህልና የግብር አገልግሎቶችን
ከገባሩ በማስከፈል ሥልጣናቸውና ተግባራቸው የገባሩን መደብ በሞትና
በስደት ከአገሪቱ በማጥፋት ላይ ነበሩ ። የተባሉ የጭቆናና የስቃይ ሹማም
ንቶች ለመንግስቱ ለጉልተኛውና ለወታደሩ አገልግሎት የሚውለውን
የአሥራትና የግብር ገቢ ከገባሩ በምርት ግለትም በዓይነት ለመንግስት
ጐተራ ሲቀበሉ በትልቁ ቁና እየሰፈሩ ይወስዱ ነበር ።

ነገር ግን በኋላ እህሉን ከጐተራው አውጥተው ለወታደሩና ለሌላም የመንግስት ቀለብተኛ ሲሰጡ በትንሹ ቁና እየሰፈሩ የሚተርፈውን ለራሳቸው በመውሰድ በአንድ ጊዜ እንዴት በመንግስቱም ፤ በገባሩም ፤ በወታደሩም በሕብረተሰቡም ላይ ድርብ የብዝበዛ ተግባር እንደሚፈጽሙ አጋልጠው ጸሐፊው አምራቹ የገባር መደብ በሞትና በስደት ከገፀ ምድር ፈጽሞ ከመጥፋቱ በፊት በአስቸኳይ የገባር አገልግሎት ከጉልበት ሥራና ከምርት ቁና ወደ ዓመታዊ የገንዘብ ግብር ተመን ተለውጦ አስጨናቂው የገባር ሥርዓት እንዲቀር ይደረግ ዘንድ ለመንግስቱና ለሕብረተሰቡ የለውጥ አሳብ አቀረቡ ።

ጥንታዊው የገባር ሥርዓት በገባሩ ፤ በሕብረተሰቡ ፤ በመንግስቱና በወታደሩ ላይ ያስከተለውን ድርብ ጉዳት የሚገልፅ ይህ የአስቤ ኃይሉ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የገባር ሥርዓት ታሪክ አንድ ታላቅ ትምህርታዊ ሰነድ ስለሆነ በከፊል እንደሚከተለው በምንባብ ቀርቧል ። በደራሲው ቃል ፤

" በኢትዮጵያ የመኳንንቱና የወይዛዝሮቹ ርስትና ጉልታቸው ምናልባት በግምት አንድ መቶ ሺህ የጋሻ መሬት ይሆናል ። ያንዱ ጋሻ መሬት ባመት ግብሩ አስራ አምስት ብር ቢሆን በመቶው ሺህ የጋሻ መሬት አስራ አምስት መቶ ሺህ ብር ማለት አንድ ሚሊዮን ተኩል ካንድ ዓመት ግብር ገቢ ለመንግስት ይቀርበታል ።

" ከዚሁም ከመቶው ሺህ የጋሻ መሬት ካሥሩ ጋሻ አንደኛው ነውና የሚታረሰው እንኳን እራሳቸው አሳርሰው ለመንግስት ጥቅም ያስራት እህል ማግባታቸው ይቅርና ከቶ ውንም እነዚያ መከረኛ ደሆች ከምስለኔና ከዱግ ( ዱግ ከምስለኔ በታች የአካባቢ ሹም ነው) እየታገሉ አርሰው ካገቡት ያሥራት እህል ምድራችንን እናቅናበት እያሉ እህሉን ከጉተራ ብሩን ከግምጃ ቤት እየተዳረጉ ቀለብተኛውንና ደሞዝተኛውን ሲያውኩት ሲያስጨንቁት ይኖራሉ ።

" የሕዝቡን ጉዳትና ችግር አንዱን እጅ እንኳ ከጻፍነው ሰው መሆን ባላስፈለገም ነበር። እነሆ የኢትዮጵያ መከረኛ ደሀ በስተምሥራቅ አንኮበር ይፋትና ተጉለት ቡልጋና ሞረት መካከል አገር የተባለ ሁሉ የመጫሚያ እላቂ በምታህል ባንዲት ጋሻ መሬት ከሶስቱ የሥራ ቀኖች አንዱን ለመልከኛ ወይም ለሻለቃ ካመት እስካመት ይሰራል ። የእጅ ሥራውንም እንደዚሁ ። በእጅ ሥራ አንዱን ቀን ለወረዳ ምስለኔ አንዱን ቀን ለዱግ ይሰራል ።

" ደግሞ ባንዱ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ አምስት ጊዜ ጭነት ጭና መሄድ አለበት ። ያምስት ጊዜ ጭነቱ ዝርዝር ይህ ነው ። ሶስት ጊዜ ለመልከኛ አምስት አምስት ቁና እህል እየፈጨ ዱቄቱን ይጭናል ። አራተኛ ማር ይጭናል ። አምስተኛ ለመንግስት አሥራት ባወጣሽ ዱቄት ይጭናል ።



"ለመልከኛ ዱቄት ጭና አዲስ አበባ በደረሰ ጊዜ ተጭና የመጣው ዱቄት ገና ከአህያው ጀርባ ላይ ሳይወርድ እንኳን መጣህልኝ ነገ ግለዳ አዋሽ ከቀላዴ ሄደህ አንድ ጤፍ ጭነህልኝ እንድትመጣ ይባላል ።

" ይህ መከረኛ ደሀ የደም እንባ እያነባ እያለቀሰ ምነው ጌታዬ ዛሬ እኮ አገራችን ያገዳ እህል አዝመራ ነው ። ዝናሙ ሳይነሳ ካልደረስኩ ጭራሽ መሰደዴ ነው እያለ ይጮሀል ። ይለፈልፋል ። ግን ማን ይሰማዋል። ከዚህ በኋላ እንደ ኢዮብ የተወለደበትን ቀን እየረገመ ወደ ታዘዘበት አገር ሄዶ ይደርሳል ።

" ከዚያ ደግሞ ይኸው እድሉ ቀድሞ ቆይቶታልና ከመልከኛው ቀላድ ላይ ያለው ምስለኔ የጌቶቹ የመኝታ ቤት ፈርሷልና በዚህ ሰሞን የቤቱን ሥራ ረድተኸኝ ትሄዳለህ ይለዋል ። ቤቱን ሲያሰራው ሰንብቶ እንዲጭን የታዘዘውን እህል ጭኖ አዲስ አበባ በደረሰ ጊዜ እንደገና ጭነህ ያመጣኸውን እህል በመዘውር አስፈጭተህ አምጣ ። ፊት ያመጣውንም ዱቄት አንድነት አስፍረህ ትሄዳለህ ይባላል ።

" በመካከሉ ስንቅ አልቆበት ተዝካር ዝክር ወደ አለበት ለቅልውጥ ሲዞር ሲንከራተት በየከተማው ተስቦ ወይም የሆድ በሽታ ተቅማጥ ዘርፎ ይመጣል ። እንደ አሮጌ ውሻ ከመልከኛው አጥር የአህያውን ፋንድያ ተንተርሶ ሲያጣጥር ሲንገላታ ሰንብቶ እምላክ ነፍሱን ከሥጋው በለያት ጊዜ የመልከኛው ሎሌዎች በሁለት እንጨት አጣብቀው ወስደው ወደ አንድ ጉድባ አስጠግተው ጫር ጫር አድርገው ይቀብሩታል ።

" አህያውንማ ገና ታሞ ሳለ ሌባ አጠናቆለታል ። ወደዚያው ከመልከኛው አቅራቢያ ካሉት ከጐረቤቶቹ አንዲት ሴት እትዬ ዛሬ ከሰፈራችን ሬሳ ሲወጣ አየሁ ። ማነው የሞተው ብላ ከመልከኛው አሽከሮች አንደኛዩቱን ስትጠይቃት " እባክሽን ተይኝ እቴ ! ሰውም አይደለ ገባር ነው" ትላታላች ። "[25]



11. የወሊጋው ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ሞሮዳ (1864 - 1916)

ምንጭ፤ Donham and James, Ethiopia (1986)



11. የወለጋው ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ሞሮዳ (1864 - 1916)

ምንጭ ፡ Donham and James, Ethiopia (1986)

## የገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ትምህርት

ከ1900ዎቹ እስከ 1920ዎቹ ድረስ የኢትዮጵያ የአዳጊ ኢንቴሌጀንሲያ የፖለቲካ ትምህርትና ትግል በአንድ በኩል ለገባር ሥርዓት መጥፋት በሌላ በኩል ደግሞ በማዕከላዊ መንግስት የፖለቲካ አመራር በጃፓኑ ሞዴል ለካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባታ እንደነበር ይታወሳል[26]። ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓት በአምራቹ ገባር ላይ የተመሠረተ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ፀረ ትምህርትና ፀረ ኢንቴሌጀንሲያ እንደነበር ደግሞ የሚታወስ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ አዳጊው ኢንቴሌጀንሲያ ከመነሻው በእነ ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ በእነ ነጋ ድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ትምህርትና ቅስቀሳ ፀረ ገባር ሥርዓት ሆኖ መከሰቱና ማደጉ የሚያስገርም ነገር አይደለም ።

በዚህ ረገድ ከ1909 የጉልተኛው ኩዴታ ጀምሮ እስከ 1922 ድረስ የኢትዮጵያ የመንግስት መሪዎችና ባለሥልጣኖች በሥልጣን ትግል በንግሥት ዘውዲቱና በአልጋ ወራሽ ተፈሪ አንጃዎች በተከፈለበት ዘመን የአገሪቱ የኢንቴሌጀንሲያና የነጋዴ ክፍሎች በተለይ የአልጋ ወራሹ አንጃ ደጋፊዎች እንደ ነበሩ የሚታወስ ነበር ።

በዚህ ወቅት አልጋወራሽ ተፈሪ የመስተዳደሩን አመራር ይዘው ወጣቶችን ወደ ውጭ አገር ልከው ለመንግስት ሥራ በማሰልጠን ፣ በአገር ውስጥም ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት ማተሚያ ቤትና ጋዜጣ በማቋቋም ፣ ሚሲዮናውያን በአገሪቱ በተለያዩ ከተሞችና አካባቢዎች ከሃይማኖታቸው ጋር ለሕዝቡ ዘመናዊ ትምህርት እንዲያስተምሩ ፈቃድ በመስጠት ፣ በመንግስት ሥራ ከውጭ አገር ኤክስፐርቶችና አማካሪዎች ጋር የአገሪቱን የተማሩ ወጣት ሠራተኞችንና ባለሥልጣኖችን በማሰማራት ፣ እንዲሁም የንግድ ፣ የሕግ ፣ የፍርድ ፣ የጤና ፣ የፖሊስ ፣ የጦር ፣ የገንዘብ ፣ የባንክ ፣ የመንገድ ፣ የኤሌክትሪክ ፣ የፖስታ ፣ የስልክ ድርጅቶችን ፣ ሥራዎችንና አገልግሎቶችን በማስፋፋት በአገሪቱ ለብሔራዊ ኢንቴሌጀንሲያ ዕድገትና ለካፒታሊዝም ጅምር የበለጠ አመቺ ሁኔታዎች ፈጠሩ ።[27]

በዚህ የሽግግር ዘመን የኢትዮጵያ የኢንቴሌጀንሲያ ፀረ ገባር ሥርዓት ትምህርት ከዚህ በላይ ከነጋ ድራስ አፈወርቅና ከፀሐፊው አስቤ ጽሑፎች በዝርዝር ታይቷል ። በአስቤ እንደ ተገለጸው በዘመኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በገባር ሥርዓት "እንደ ጭቃ ተረግጦ እንደ ገል ተቀጥቅጦ በጭንቀት ኑሮው ውስጥ ይኖራል ።"[28] ከዘመኑ የኢትዮጵያ ኢንቴሌጀንሲያ መሪ- አባሎች የብሔራዊ ካፒታሊዚም ሥርዓት ትምህርትን በተለይ በከፍተኛ ደረጃ ያብራሩት ሁለት ምሁራን ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝና ብላታ ደሬሳ አመንቴ ናቸው ።



ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፀረ ገባር ሥርዓት አቋማቸውንና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባታ ትምህርታቸውን አስፋፍተው የገለጹት በ1904 አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ በ1908 መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር በተሰኙ ጽሑፎች ነው ። በነጋ ድራሱ አመለካከትና ግንዛቤ ፣ ሰው በተፈጥሮው የአእምሮ ጌታ በአእምሮው መሣሪያ እያሰበ የሚሠራ አካል ነው ። "በአእምሮም ላይ በጊዜ ብዛት እውቀት ጨምሮ በት የምድር ጌታ ሆነ ። ይህንን ዕውቀቱንና ትጌነቱን"[29] ሰው ያገኘው ግን በአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን በረጅም ታሪካዊ የሥራና የትግል ልምድ ነው ።

በመሆኑም "ሰው ኑሮው ከምድር ጋር ሲታገል ነው እሱ ጌታዋ ለመሆን እሷ አልገዛም ስትለው ዘወትር ዕረፍት አልባ ሲታገል ይኖራል ። ይህም የሰው ትግል ሥራ ይባላል ።... የሰው ጥረቱ ምድርን ለመግዛት ነው።ስለዚህም አንድ ሥራ በሆነለት ቁጥር ለዚሁ ጌትነት ይቃረባል።"[30]

በታሪክ የሥርዓትና የግለሰብ ሚና አስመልክተው ነጋድራስ ገብረ ሕይወት እንደ አስቀመጡት ደግሞ ፣

"ማናቸውም ሕዝብ ቢለማም ቢጠፋም በገዛ እጁ ነው ። ሕዝብ የሚጠፋበት አንዳንድ ጊዜ ምክንያት ቢገኝ ያውም ምክንያት ባንዳንድ ሰው ቢመካኝ ነገሩ ትክክል አይሆንም ። የልማትን መንገድ ለማግኘት የሚጥር ሕዝብ ቢገኝ ባንዳንድ ክፉ ሰው ምክንያት ሊጠፋ አይችልም ። እንዲሁም ደግሞ የልማትን መንገድ ለማግኘት የማይጣጣር ሕዝብ ባንዳንድ ደህና ሰው ኃይል ልማት ሊያገኝ አይችልም ።"[31]

በ1904 ነጋ ድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ በተሰኘው ጽሑፋቸው ለኢትዮጵያ ፈጣን ብሔራዊ ዕድገትና ልማት ባቀረቡት የሥራ ፖሊሲና ፕሮግራም በአገሪቱ ለካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባታ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችንና እርምጃዎችን እንደሚከተለው ዘረዘሩ ። የገብረ ሕይወት የ1904 ያገር ግምባታ ፕላን በአስቸኳይ ፣

1. በመንግስትና በንጉሡ ግምጃ ቤቶች መካከል ልዩነት እንዲደረግ
2. የገባር አገልግሎትና የማደሪያ መሬት ስሪት ቀርቶ የመንግስት ሠራተኞች በደሞዝ እንዲሠሩ ፣
3. የመሳፍንቶችና የሹማምንቶች የግልና የአካባቢ ጦር እንዲቀር ፣
4. በንጉሡ ጠቅላይ አዛዥነት የሚመራ ብሔራዊ የጦር ሠራዊት እንዲመሠረት ፣
5. የጦርና የመንግስት ሹማምንቶች ለየብቻቸው እንዲሆኑ ፣
6. ሕዝቡ እንደገቢው መጠን ለመንግስት ተመጣጣኝ ግብር በገንዘብ እንዲከፍል ፣

7. በየጊዜው ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ እንዲካሄድ ፤
8. የመንግስት ግብር ገቢ በእህል ፤ በማርና በገባር ጉልበት መሆኑ ቀርቶ በገንዘብ እንዲከፈል ፤
9. ለአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ሕግና ሥርዓት እንዲበጅለት ፤
10. በአገሪቱ ታላላቅ ከተሞች ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ፤
11. በአዲስ አበባ መዲና ብሔራዊ የጦር ትምህርት ተቋም እንዲከፈት፣
12. የፍትሐ ነገሥት ሕግ ቀርቶ ዘመናዊ ሕገ መንግስት እንዲዘጋጅ፤
13. አንድ ወጥ ብሔራዊ የገንዘብ ሚዛንና አገልግሎት እንዲዘጋጅ ፤
14. ለብሔራዊ የንግድ ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት እንቅፋት በመሆኑ በየመንገዱና በየአካባቢው የኬላ እገዳና ዘረፋ እንዲቀር ፤
15. በአገር ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ የመንግስቱን አስተዳደርና ሕዝቡን በብሔራዊ አንድነት የሚያደራጅና የሚያስተባብር አንድ ማዕከላዊ የቅስቀሳና የቁጥጥር መምሪያ እንዲመሠረት ፤
16. የሃይማኖት ነጻነት እንዲታወጅ ፤

የሚል ግልጽ የካፒታሊዝም ግምባታ ፖሊሲና ፕሮግራም ነው ። [32]

በ1908 መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር በተሰኘው የፖለቲካ ኢኮኖሚ መጽሐፋቸው ነጋድራስ ጨምረው እንዳሉት ፤ በዘመኑ በኢትዮጵያ በማዕከላዊ መንግስት አመራር ለብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባታ በአስቸኳይ የሚያስፈልጉ ተግባራዊ መንገዶች ፤ መግሪያዎችና እርምጃዎች ደግሞ ፤

1. የግል መሬት ይዞታ ፤
2. ጥሩ የጉምሩክ ፖሊሲና አሠራር ማለትም ጥሩ የውጭ ንግድ ፖሊሲ ፤
3. በተለያዩ የሙያ መስኮችና ዘርፎች የሕዝብ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች ፤
4. የመንገድና የምድር ባቡር መገናኛዎች ፤
5. ብሔራዊ የሚታተል ገንዘብ ፤
6. ለአገር ልማት የሚውል የግል መዋዕለ ንዋይ ፤
7. የተዋሀደ የእርሻ የዕደጥበብና የንግድ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ዕድገትና መስተጋብር ናቸው ። [33]

በደራሲው የብሔራዊ ካፒታሊዝም ግምባታ ትምህርት መሠረት ፤ በጥቂት ከበርቴዎች እጅ የመሬት ሞኖፖሊያዊ ይዞታ ለአገር የከፋ ነገር ምልክትና መጀመሪያ ነው ።በሌላ በኩል የመሬት ተከፋፍሎ በብዙ ሰዎች እጅ የግል ይዞታ መሆን ግን የሕዝብ ሀብትና የመንግስት ጥንካሬ ምልክት ነው ። በነጋድራሱ ቃል ፤



" መሬት በጥቂት ሰዎች እጅ ሲገባ ላገሩ ክፉ ምልክት ነው ።ሕዝቡ እንደ ደኸየና የመንግስት ኃይል እያነሰ እንደሄደ ይመሰክራል ። መሬቱ ተከፋፍሎ በብዙ ሰዎች እጅ የሆነ እንደሆነ ግን የሕዝቡን ሀብትና የመንግስቱን ኃይል ያመለክታል ። ይህ ስለ ተባለ ግን መሬት አይሸጥ ተብሎ ቢታወጅ ለሕዝቡ የበለጠ ጉዳት ይሆንበታል ። ባላገሩ ያለው ገንዘቡ መሬት ነውና ይህንንም ያለውን ገንዘቡን እንደ ልቡ ካልሸጠ ካለወጠ ገንዘቢ ነው የሚለውን ነገር ፈጽሞ ያጣል ። በዕዳም ቢያዝ እጁን የሚያወጣበት ነገር አያገኝም ። " [34]



ምንጭ ፡ በቤተሰብ ትውውር (1982)

12. የቢጋሻውንጉሉ ሀጂሌ አልሀሰን (1818 - 1930)

በነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትምህርት አንድ ሌላ መሠረታዊ የግንዛቤ ነጥብ በአንድ አገር ከምርት ኃይሎችና ከምርት ዕድገት በሬት የመሠረተ ልማት ግምባታ ትርፉ ብሔራዊ ኪሳራ ይሆናል የሚለው በተለይም የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ለሚያመርቱ ለዛሬው የሶስተኛ ዓለም አገሮች የበለጠ ሊያገለግል የሚችል ጠቃሚ ቲሲስ ነው ። ይህ ከነጋድራሱ የዋጋ ተመን ግንዛቤ የተገኘው መሠረታዊ ትምህርት ነው ። በነጋድራሱ ትምህርት መሠረት ፤ በገበያ ሚዛን የንግድ ዕቃ ዋጋ ወይም እሴት በትክክል የሚወሰነው ዕቃውን በማዘጋጀት ሂደት ለሥራ በሚፈሰው የሰው ጉልበት መጠንና ሥራውን ለመጨረስ በሚወስደው የጊዜ ልክ ነው ።



ምንጭ ፣ በቤተሰብ ትብብር (1982)

12. የቤኒሻንጉሉ ሆጃሌ አልሀሰን ( 1818 - 1930 )



13. የአፋሩ አቡበከር (1808 - 1879) ለኢትዮጵያ የታጁራ ጂቡቲ የንግድ መንገድ በመከፈት ተግባር ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ያካባቢ መሪ

ምንጭ ፡ P. Paulitschke. Harar (1888)

በዚህ ረገድ ደግሞ ለአንድ የገበያ ዕቃ ዋጋ ወይም የእሴት ተመን መሠረት የሆነውና የሚሆነው የሰው ሥራ ወይም ጉልበት የሰለጠንና ያልሰለጠነ ሥራ ተብሎ የደረጃ ልዩነት አለው ። በመሆኑም የእውቀት ደረጃቸው የሥራ መሣሪያቸው ዓይነትና ደረጃ ተመጣጣኝ ያልሆነ ሁለት ሠራተኞች ወይም አገሮች የሥራ ውጤቶቻቸውን በገበያ ሚዛን ሲለ ዋወጡ የዕቃዎቻቸው ዋጋ ወይም እሴት እኩል ሊሆን አይችልም። በነ ጋድራሱ ቃል ፤

" የሠሩትን ሥራ የሚለዋወጡ ሠራተኞች እንደ ድካማቸው መጠን የሚለዋወጡ ለየሥራቸው የሚያስፈልጋቸው እውቀት ሚዛኑ ትክክል ሲሆን ነው ፤ የእውቀታቸው ሚዛን ትክክል ካልሆነ የሚለዋወጡበት ዋጋ ትክክል አይሆንም ።

" ስለዚህም እውቀት የሌላቸው ሕዝቦች እውቀታቸው ከፍ ካለ ሕዝቦች ጋራ የሠሩትን ነገር ሲለዋወጡ እውቀት የሌላቸው ሕዝቦች የሚ ያገኙት ጉዳት ትልቅ ነው ።" [35]

- በዚህ በደራሲው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሳይንስ ፤ በሰለጠኑና ባልሰለ ጠኑ ሰዎችና አገሮች መካከል ይህ ዓይነት የብዝበዛ ሥስተጋብር እስካለ ድረስ ያልሰለጠነው ወገን ሊሰለጥንና የራሱ የሆነ ነጻ ሥርዓት ግምባታ ለማካሄድ አይችልም ።

በተጨማሪም በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚገኘው የእውቀት ደረጃ ሳይስተካከል በፊት ባልሰለጠነው አገር ውስጥ የፈረሰ ጋሪ ፤ የመንገድ፤ የባቡር ፤ የመርከብ ፤ የአየር መገናኛዎች ፤ የትምህርት የባንክ ፤ የንግድና የእርሻ ሥራዎችና ድርጅቶች ቢስፋፉም እንኳን ጥቅሙ ገና ለሚሰለጥ ነው ወገን ሳይሆን ቀድሞ ለሰለጠነው ወገን ብቻ ይሆናል ። በዛሬው አነ ጋገር ጥሬ የእርሻና የማዕድን ዕቃዎችን ለሚያመርቱ ለሶስተኛው ዓለም አገሮች ሳይሆን ጥቅሙ በከፍተኛ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ጥበብና መሣ ሪያ የፋብሪካ ዕቃዎችን ለሚያመርቱ በኢንዱስትሪ ለዳበሩ አገሮች ብቻ ይሆናል ማለት ነው ። በነጋድራሱ የማስጠንቀቂያ ቃል ፤


" እውቀት በሌለው ሕዝብ አገር መንገድና የምድር ባቡር ቢሠራ ሕዝ ቡእንዲደኸይ ያፋጥናል እንጂ አይጠቅመውም ። ጥቅሙ ከርሱ ጋር ለሚገ በያዩ አዋቂ ሕዝቦች ነው ።" [36] በወቅቱ በገባር ኢኮኖሚና ሥርዓት ደረጃ ከሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት አኳያ ሲናገሩ ነጋድራሱ ጨም ረው እንዳሉት ፤ የሕዝቡ የእውቀት ደረጃ ማለትም የምርት ኃይሎች ሳያ ድጉ " የምድር ባቡርና ባንክ ወዳገራችን አመጣጣቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ መቃብር ለመማስ እንደሆነ ጥርጥር የለም ። " [37]

በነጋድራሱ የመፍትሔ አሳብና ትምህርት ፤ ለኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ ከዚህ ዓይነት የኢምፔሪያሊዝም ጥገኝነትና ሥርዓታዊ ብዝበዛ



ነጻ ለመሆንና የራስን ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት በጃፓኑ ሞዴል ለመ ገንባት ጥሩ የጉምሩክ ፖሊሲና ሰፊ የሕዝብ ማሰልጠኛ ሥርዓተ ትምህ ርት አስፈላጊ የመከላከያ መሣሪያዎችና መንገዶች ይሆናሉ ። በጥሩ የጉ ምሩክ ፖሊሲ በአንድ በኩል በከፍተኛ ቀረጥ ለምርት ዕድገት አስተዋ ጽኦ የማያደርጉ ርካሽ የፍጆታ ዕቃዎች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ እንዳይ ገቡ ማድረግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የማምረቻ መሣሪያዎችን በብዛትና በፍ ጥነት ከቀረጥ ነጻ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ነው ። በተጨማሪም " ያለ ቀረጥ እንዲገቡ በተፈቀዱ መኪናዎችና መሣሪያዎች ሊሠራ በሚ ቻል ነገር ሁሉ በአገር ውስጥ በብዙ እንዲቀረጥ ይደነገጋል ። " [38]

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ምንም የጃፓንን ከውጭ ኃይሎች ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የካፒታሊዝም ግም ባታ ሞዴልና አሠራር ለምሳሌ ቢያቀርቡ በኢትዮጵያ የአገሪቱን የጠረ ፎች ዙሪያ በቀለበት ከበው የያዙ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችና ዓለም አቀፍ የኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት በነጻ ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግም ባታ ፕሮግራም ላይ ሊያሳድሩት የሚችሉትን ተጽዕኖ በትክክል የተረ ዱት አይመስልም ። በአንድ አዳጊ አገር ላይ ይህንን የኢምፔሪያሊዝ ምን አፍራሽ ተጽዕኖ ለአገሪቱ ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባ ታ ባቀረቡት አሳብ ብላታ ደሬሳ አመንቴ የበለጠ የተረዱት ይመስላል ።



13. የአፋሩ አቡበከር (1808 - 1879) ለኢትዮጵያ የታጁራ ጂቡቲ የንግድ መንገድ በመከፈት ተግባር ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ያካባቢ መሪ

ምንጭ ፡ P. Paulitschke. Harar (1888)

## የደረሳ አመንቴ ትምህርት

ብላታ ደሬሳ አመንቴ የእርሻ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር የነበሩ ፀረ
ገባር ሥርዓት አቋማቸውንና ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግምባታ
ትምህርታቸውን ያሳወቁት በ1924 በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ “ ስለአገር
አካሄድ ማሻሻል ” ፤“ስለ አራቱ የችግር መሠረቶች ማመልከቻ ” እና
“ ስለጊዜው የገንዘብ ችግር ” በተባሉ ተከታታይ ጽሑፎች ነው ።

በ1924 በተጠቀሱት ጽሑፎች ብላታ ደሬሳ አመንቴ እንዳስቀመ
ጡት ፤ በዘመኑ የኢትዮጵያ መሠረታዊ የሀብት ምንጮች መሬት ፤ የሰ
ው ጉልበትና እንስሳት ሲሆኑ በገባር ሥርዓት ተፅዕኖ ምክንያት ሁሉም
ለአገር ዕድገትና ልማት ጥቅም ላይ አልዋሉም ። ስለዚህ እነዚህን ብሔ
ራዊ የሀብት ምንጮች ለአገር ግምባታ ለማዋል ፤ በብላታ ደሬሳ አመ
ንቴ ጽሑፎች መሠረት ፤ የገባር ሥርዓትን ማጥፋት ፤ ለመንግስት የመሬ
ትን ግብር በብር ማስከፈል ፤ በየአካባቢው ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችንና
የመኪና መንገዶችን መክፈት የእንስሳት ሕክምናን በአገር አቀፍ ደረጃ
መጀመር ተቀዳሚ እርምጃዎች ናቸው ።

በብላታ ደሬሳ አመንቴ መረጃ መሠረት ፤ የኢትዮጵያ ጠቅላላ
የመሬት ስፋት 840,000 ጋሻ ነበር ። ከዚህ 480,000 ጋሻ መሬት የአ
ፋር ፤ የሶማሌና የቦረና የዘላን አካባቢዎችን ጨምሮ የማይታረስ ቆላማ
መሬት ሲሆን 360,000 ጋሻ መሬት ደግሞ በእርሻና በዕደ ጥበብ ተግባ
ራት የተሰማሩ ማህበረሰቦች የሚኖሩበት የደጋና የወይና ደጋ አካባቢ
ነው ። ይህንን የአገሪቱን ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታ ሲገልጹ ብላታው
እንዳሉት ፤

“ በኢትዮጵያ የሚገኘው ሀብት በደጋው መሬት በግ ፤ የጋማ ከብት፤
እህል ፤ በወይናደጋው ልዩ ልዩ አታክልት ፤ እህል ፤ የቀንድ ከብት ፤ በቆ
ላው ጥጥ ፤ እህል ፤ የቀንድ ከብት ፤ ግመል ፤ ፍየል ናቸው ። ከዚህም ሌላ
ብዙ ደን ፤ ልዩ ልዩ ማዕድናት ማለት ወርቅ ፤ ብር ፤ መዳብ ፤ ብረት ሌላም
ይህን የመሰለ ሀብት ሞልቷል ። የአገሩዋ አየር ራሱ ከብዙ ሀብት ይቆጠ
ራል ። ይህችን የመሰለች የምድር ገነት አገር ይዘን እንደ አሜሪካ ሌላ
ውን ዓለም መመገብ እንችል የነበረውን እስከኛው ድሆች ያደረጉን እነ
ዚሁ ” ከላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ የገባር ፤ የአፈርሰታ ፤ የግብር ፤
የትምህርት ፤ የመንገድና የእንስሳት በሽታ ችግሮች ናቸው ።

ብላታ ደረሳ አመንቴ ጨምረው በዓለም አቀፍ ንጽጽር እንደ
አስረዱት ፤ በግብርና ሥራ የሚኖረው አትራባቹ የግብጽ መንግስት ዘመ
ናዊ የእርሻ ትምህርትና መሣሪያ በመጠቀም ፤ ከ72,246 ጋሻ መሬት በዓ
መት ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር ገቢ ሲያገኝ ፤ እንዲሁም የሕዝቡ ብዛት



ስምንት ሚሊዮን ሲሆን የአገሩ ዋናው የኢኮኖሚ ምንጭ ከብት ርባታ
የሆነው የደቡብ አሜሪካ አገር አርጀንቲና ከእንስሳት ምርት በዓመት አንድ
መቶ አስራ ሁለት ሚሊዮን ብር ብሔራዊ ገቢ ሲያገኝ ፤ የኢትዮጵያ መን
ግስት ግን ከ840,000 ጋሻ መሬት በልዩ ልዩ መንገዶች በዓመት የሚያገ
ኘው የገቢ መጠን በድምሩ አስራ ስድስት ሚሊዮን ተኩል ብር ብቻ ነው ።

የብላታ ደሬሳ አመንቴ ጥናት ጨምር እንዳመለከተው ፤ በዘመኑ
በኢትዮጵያ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ልማትና ማህበራዊ ዕድገት ላይ በአንድ
ነት ወሳኝ ተፅዕኖ ያሳደሩ መሠረታዊ ነገሮች የእንስሳት በሽታ ፤ የገባር
ሥርዓትና ዓለም አቀፍ የካፒታሊዝም ሥርዓት የገበያ ቀውስ ናቸው ።

በዚህ ረገድ ከምጽዋ የተስፋፋው የ1880-1884 ታላቁ የእንስሳት
እልቂት በሰሜን ፤ በመሀል ፤ በደቡብና በምሥራቅ ኢትዮጵያ አሳማ ፤ተኩ
ላና ጉሽ ሳይቀር የአገሪቱን የዱርና የቤት እንስሳትን እንደጨረሰና በዚ
ህም ምክንያት የእርሻ በሬ በማለቁ በምግብ እጦት ብዙ ሕዝብ በችጋር
እንደ አለቀ ይታወሳል ። በብላታ ደሬሳ አመንቴ ዘገባ መሠረት ፤ በታ
ላቁ በሽታና ችጋር ፍጻሜ የከብት ዘር የተገኘው በምዕራብ በወቅቱ ከኢ
ትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ውጭ ከነበሩት ከአናርያ ፤ ከከፋ ፤ ከኩሎ ፤
ከኮንታ ፤ ከጊሚራና ከጉራፋርዳ ነበር ።

በተጨማሪም ብላታ ደሬሳ አመንቴ በ1920ዎቹ በጉምሩክ በኩል
ወደ ውጭ የሚላከውን የቆዳ መረጃ በማገናዘብ በከፊል እንደገመቱት ፤
በአገሪቱ በዓመት በሶስት ሚሊዮን የሚቆጠሩ ከብቶች በበሽታ ያልቁ
ነበር ። በብላታው አስተያየት ፤ በዘመኑ በአገሪቱ የእንስሳት ሕክምና
አገልግሎት ቢኖር ኖሮ ፤ እነዚህ በየአመቱ በበሽታ የሚያልቁ ከብቶች
በአምስትና በስድስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ምናልባትም እስከ አስራ አም
ስት ሚሊዮን ይረቡ ነበር ። ከእነዚህ ከብቶች ቢያንስ እስከ ሶስትና አራት
ሚሊዮን ወደ ውጭ አገር በመላክ አገሪቱ በውጭ ምንዛሪ እስከ ሁለት
መቶ ሚሊዮን ብር መንግስት ደግሞ በቀረጥ ቢያንስ እስከ አንድ መቶ
አስራ አምስት ሚሊዮን ብር ገቢ ሊያገኝ ይችል እንደነበር በትችት ለማገ
ናዘብ ሞክሮአል ። ከዚህም አስተያየታቸው በመነሳት ብላታው ደሬሳ
አመንቴ በአገሪቱ የእንስሳት ሕክምና ሥራ እንዲጀመር የሚከተለውን
ብሔራዊ ጥሪ አቅርበዋል ። በ1924 ብላታው እንዳሉት ፤

“ ዛሬ ዋና የኢትዮጵያ ጥቅም የንግድ ሥራ መሥራት ፋብሪካ አቁሞ
በፋብሪካው መሥራት ማዕድን መቆፈር አይደለም ። እነዚህ ሁሉ ሰፊ
ትምህርትና ብዙ ገንዘብ ይፈልጋሉ ። እኛ ግን ዛሬ ለዚህ የሚያበቃን
ገንዘብና ትምህርት ስለሌለን ጥቅም አናገኝባቸውም ። ጥቅም ማለትም
የአንዳንድ ሰው ማግኘት አይደለም ። ዋና ጥቅም የምንለው የኢትዮጵያ
ሕዝብ ሁሉ የሚጠቀምበትን ጥቅም ነው ። ስለዚህ ዛሬ ኢትዮጵያ የም
ትጠቀምበት ዋና ሀብቷ የከብት ርቢና እርሻ ነው ። እርሻም እንኳ ከብት

ረብቶ በሬ ከተገኘ በኋላ ነው ። . . . .ኢትዮጵያ ወደፊት ትልቅ ጥቅም የምታገኘው በከብት ርቢ ነው ። ከብት ማርባት የሚቻለውም የከብት ክትባት ቤት ቋሞ ከብቶች ተከትበው ከማለቅ ሲድኑ ነው ።

" አሁን በቶሎ የከብት ርቢ ሥራ ፤ የእርሻ ሥራ ፤ የአታክልት ሥራ ባገሩ እንዲለማ እንዲበዛ ከእኛ ተርፎ ወደ ውጭ አገር በብዙ ተሸጦ ከውጭ አገር ገንዘብ እንዲያመጣልን ማድረግ ሌላውን የአውሮፓ ሥልጣኔ እስከናገኝ ለጊዜ የሚሆን ሥልጣኔ ይህ ነው ።"



14. የሶማሌው ኡጋዝ ሮቢሌ ፋራሂ (በ1870ዎቹ)

ምንጭ ፥ P. Paulitschke, Harar (1888).

በዘመኑ የገበያና የገንዘብ ሁኔታ ፤ እንዲሁም የገባር ሥርዓትና ዓለም አቀፍ የኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት መስተጋብር በፋሽስቶች ወረራ ዋዜማ በኢትዮጵያ መንግስትና ሕብረተሰብ ላይ ያሳደረውን የኢኮኖሚና የባህል ተጽዕኖ ጸሐፊው በትክክል አገናዝበው በ1920ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ የሕዝቡ የኑሮ ወጪ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት አራት እጥፍ እንደ አደገ እንደሚከተለው አሳይተዋል ።

በዘመኑ የኢትዮጵያ መንግስት በአዲስ አበባ ፤ በሐረር ፤ በድሬዳዋ፤ በጅጅጋ ፤ በጋምቤላ ፤ በመተማና በምጽዋ የንግድ በሮች ወደ ውጭ አገር በመላክ የውጭ ምንዛሬ የሚያገኝባቸው መደበኛ የንግድ ጥሬ ዕቃዎች



ቡና ፤ ቆዳ ፤ ሰም ፤ ከብትና እህል ሲሆኑ ከውጭ ገዝቶ ወደ አገሪቱ የሚያስገባቸው መደበኛ የኢንዱስትሪ ውጤት ዕቃዎች ደግሞ ጨርቃ ጨርቅ፤ ሐር ፤ ድር ፤ ማግ ብረት . . . ነበሩ ።

በታላቁ የ1921 - 1923 ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ ዋዜማ ( በ1918 ) የኢትዮጵያ መንግስት በአዲስ አበባ ጉምሩክ በኩል የንግድ ዕቃዎችን በዓለም ገበያ ሸጦ ያገኘው የውጭ ምንዛሬ መጠን 9,157,651 ብር ፤ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ለገቡ ዕቃዎች የከፈለው ጠቅላላ ዋጋ ደግሞ 6,999,296 ብር ሲሆን ከዚህ ልውውጥ የተገኘው የውጭ ምንዛሬው ትርፍ 2,158,355 ብር ነበር ።

ነገር ግን በ1921- 1923 ታላቁ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ ወቅት የኢትዮጵያ የቡና የቆዳ የእህልና የከብት ዋጋ በዓለም ገበያ ላይ በኃይል በመቀነሱ ፤ በ1922 ከአገሪቱ በዓለም ገበያ ላይ የተሸጠው ዕቃ ድምር ዋጋ 7,364,286 ብር ፤ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ለገባ የኢንዱስትሪ ዕቃ የተከፈለው ጠቅላላ ዋጋ ደግሞ 15,544,481 ብር ሲሆን በዚህ የንግድ ሂደት በአንድ ዓመት በአገሪቱ ላይ የደረሰባት የውጭ ምንዛሬ ኪሳራ 8,180,190 ብር ነበር ። በ1923 ደግሞ ወደ ዓለም ገበያ ተልኮ የተሸጠው ዕቃ ዋጋ 7,184,946 ብር ወደ አገሪቱ ውስጥ ለገባው ዕቃ የተከፈለው ዋጋ ደግሞ 14,146,454 ብር ሲሆን በአገሪቱ ላይ የደረሰባት የውጭ ምንዛሬ ኪሳራ 6,961,508 ብር ነበር ።

በአጭሩ በ1921-1923 ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ ተጽዕኖ ፤ በጸሐፊው እንደ ተገለጸ ፤ በሐረር ፤ በድሬዳዋ ፤ በጅጅጋ ፤ በጋምቤላ ፤ በመተማና በምጽዋ የንግድ በሮች የተካሄደው የንግድ ልውውጥ ሂሳብ ተጨምሮ ሳይታሰብ፤በሁለቱ ዓመታት በአዲስ አበባ የንግድ በር ብቻ በኢትዮጵያ ላይ15,141,698 ብር የውጭ ምንዛሬ ኪሳራ ደረሰ ።

በተጨማሪም በዘመኑ የኢትዮጵያ የገዥ መደብ አባሎች የኑሮ ዘይቤ በአገሪቱ ለገንዘብና ለገበያ ችግር ሁለተኛው ምክንያት እንደነበር ጸሐፊው ጨምረው እንደሚከተለው ያብራራሉ ። በ1924 " ስለጊዜው የገንዘብ ችግር " በተሰኘው የትንተናና የምክር ጽሑፋቸው ብላታው እንዳሉት ፤

" አሁን ዛሬ የገንዘብ ወጭአችን በየቤታችን ሁሉ አራት እጥፍ ሆኖ አል ። ሁለቱ እጥፍ በብር መርከስ ምክንያት ፤ ሁለቱ እጥፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቤቱ ሁለት ዓይነት ኑሮ አለው ።

" አንዱ ሰው እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ከልብስ ወገን ጥበብ ፤ ኩታ ቡልኮ ፤ ሱሪ ፤ እጀ ጠባብ ፤ በርኖስ ፤ ካባ አለው ። አሽከሮች በቅሎች ፤ ፈረሶች ፤ ለጓሚዎች ፤ ጥልፍ ኮርቻ ፤ የነብር ቆዳ ፤ የፈረስ ቤንቻ ( መጣብር) ፤ ሌላም መጣሪያ አለው ። ደግሞ ከዕቃ ወገን መሶብ ፤ ዋንጫ ፤



14. የሶማሌው ኡጋዝ ሮቤሌ ፋራሂ (በ1870ዎቹ)

ምንጭ ፡ P. Paulitschke, Harar (1888).



15. አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (1860 - 1939)

ምንጭ ፤ ከብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት

ብርሌ ፣ ሉግት ፣ ቢላዋ ፣ ምንጣፍ ፣ መጋረጃ ፣ ይህ ንንም የመሰለ አለው። እንደ አገሩ ልማድ ግብር ያበላል ። ዝክር ይዘክራል ። ተስካር ያበላል ። ይህ ለአንድ ሰው ኑሮ ሙሉ ነውና በቂ ነበር ።”

“ . . . ይኸው አንዱ ሰው እንደ አውሮፓውያን ኑሮ ደግሞ ከልብስ ወገን ኮት ፣ ወፍራም ሹራብ ፣ ሱፍ ፣ የብርድ ልብስ ፣ ፍራሽ ፣ የአልጋ ልብስ ፣ የዝናብ ልብስ ፣ ጫማ ፣ ገምባሌ ፣ ባርኔጣ ፣ የባርኔጣ መስቀያ ፣ የቁም ሳጥን ፣ ሻንጣ ፣ ሌላም የአውሮፓውያን ዕቃ አለው ። ከዕቃ ወገን የፈረንጅ ወምበር ፣ ልዩ ልዩ ጠረጴዛ ፣ ፋኖስ ፣ መብራት፣ የብረት አልጋ፣ ሳህን ፣ ብርጭቆ ፣ ማንካና ሹካ ፣ የሻይ ጀበናና የፍንጃል ማቅረቢያ ፣በየ አይነቱ የአበባ ማስቀመጫ ፣ትልቅና ትንሽ ሰዓት ፣ መስታወት ፣ ፎቶ ግራፍ ፣ አቶሞቢል ፣ ሹፌር ፣ የአንድ ፈረንጅ ዕቃ በሙሉ አለው ።ድግ ስም ሲደግስ ወይም በሌላ ዘወትር ቀን ሲሆን እንደ አገር ልማድ ነጭ እንጀራ ፣ ጠጅ ፣ ጠላ ፣ የኢትዮጵያ ወጥ በየአይነቱ ቡና ፣ ሰንጋና ሙክት ታርዶ ይቀርባል ። ደግሞ የቶርና ዳቦ ፣ የፈረንጅ ወጥ በየአይነቱ ፣ ወይን ጠጅ ፣ ቢራ ፣ ሻምፓኝ ፣ አረቄ በየአይነቱ ፣ ሻይ ፣ ሱኳር ፣ ቸኮሌት ሁሉ ቱም አይነት ይቀርባል ። ”

“ የገንዘባችን ወጭ አራት እጥፍ ሆናአል ያልሁት መጀመሪያ ከብር መርከስ የተነሳ በአንድ ብር ይገዛ የነበረው ዕቃ ዋጋ ሁለት ብር ሆነ ። ዳግመኛ የዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ የአንድ ሰው የሁለት ሰው ንብረት ሆነ ። ይህ እንኳን ለድሀ ሕዝብ ይቅርና ለመንግስትም ቢሆን ችግር የሚያበዛ ይመስላል ።

“ ይህንን አካሄድ ልብ አድርጐ ለተመለከተው ሰው ትልቅ ጉዳት መሆኑ በጉልህ ይታያል ። ጉዳት መሆኑም መንግስትም ሆነ ሕዝብ ለቀድሞ ኑሮ አይነትም ሆነ ለአዲሱ የሥልጣኔ ሥራ አካሄድ ማስኬጃ የሚሆነውን ገንዘብ የሚያገኘው ከዚችው ከአንዲት አገር ነው ። ለውጭ የምንፈልገው ገንዘብ ግን አካሄዳችን ሁለት ዓይነት ስለሆነ ለሁለት ነገር የሚበቃ ገንዘብ የሚያስፈልገን ሆነ ።

“ ስለዚህ ይህ አራት እጥፍ ወጭ ወደፊት ለአገሪቱ ትልቅ ጉዳት የሚሆናት ይመስለኛል ። ሁላችንም በዚህ ነገር ማሰብ ያስፈልገናል ። ተረት ስንሰማ ሁለት የሚያባርር በአንዱም አይደርስ ይባላል ።


“ ይህን ማለቴ ዛሬ ልክ አውሮፓውያን ኑሮ ለማድረግ እንችላለንና የቀድሞው ይቅር ወይም የአውሮፓን ሥልጣኔ መቀበልን እንተውና በቀድሞው እንቆይ ማለቴ አይደለም ። አስቀድመን ሥልጣኔ ማለት ምን እንደሆነ ለይተን እንወቅ ። ሥልጣኔ ማለት የሰለጠነ ሕዝብ ለንግድና ለትርፍ የሰራውን ዕቃ በብዙ ዋጋ ገዝቶ ከቤት ማኖር ወይም መልበስ አይመስለኝም ። ትምህርትና ሥልጣኔ ያላቸው ሰዎች በሠሩት ቤት መቀመጥ የሠሩትን ልብስ ገዝቶ መልበስ መልካም መልካሙን ዕቃቸውን



ገዝቶ ከቤት ማስቀመጥ ጥቅምና ሥልጣኔ አይሆንልንም ። ይልቁንም ገንዘባችንን አባክና ችግር ያመጣብናል እንጂ ። ሥልጣኔ ማለትስ እኛ የትምህርት ሥራ አጠንክረን ባገሩ ችግርና ድህነት በዝቶ እንዳንቸገር በገንዘብ ቁጠባ ሥራ ሕዝቡን እየመከርን ልጆቻችንን የሥልጣኔና የእጅ ሥራ ትምህርት እያስተማርን በአገራችን ብዙ አይነት ሥራ እየተሠራ ራሳችንን እንድንችል ማድረግ ነው ።

“ ደግሞ አሁን በቶሎ የከብት ርቢ ሥራና የእርሻ የእታክልት ሥራ ባገሩ እንዲለማ እንዲበዛ ከእኛም ተርፎ ወደ ውጭ አገር በብዙ ተሸጦ ከውጭ አገር ገንዘብ እንዲያመጣልን ማድረግ ሌላውን የአውሮፓ ሥልጣኔ እስክናገኝ ለእኛ ለጊዜው የሚሆን ሥልጣኔ ይህ ነው ።

“ ይህም አሳብ የአገር ታላላቅ ሰዎች ለዚህ ለማይረባ ለውጭ አገር ዕቃ ብዙ ወጭ ማድረግ ትተው ለሕዝባቸው የጥንቃቄ መንገድ ቢያሳዩት ይጠቅማል ። ብዙዎቹ የሥልጣኔ ትምህርት የሌላቸው የምሥራቅ አገሮች እንደዚሁ የሌላ አገር ዕቃ መግዛትና ብዙ የገንዘብ ወጭ ማድረግ ጌትነትና መከበር መስሎአቸው በዚህ አካሄድ ፍጻሜ ለሌላው ለትልቅ ጉዳትና ውርደት ደርሰዋልና ከዚህ መንገድ በቶሎ እንራቅ ። ሕዝቡ እየተስማማ ይህ የማይረባ አካሄድ የሥልጣኔ ሥራ መስራትና ጌትነት መስሎት በሁለት ክፍል ኑሮ የሚያወጣውን የገንዘብ ወጭ ቢተወው ይጠቅማል ። ” [39] በማለት ብላታ ደሬሳ አመንቴ አስጠንቀቁ ።



15. አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (1860 - 1939)

ምንጭ ፡ ከብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት

በኢትዮጵያ በጉልተኛ የገዥው መደብ አመራር በተካሄደው የአ
ጼው መንግስት የፖለቲካ ምዕከልና ሂደት ( 1850 - 1900 ) ከመንግ
ስት ሥልጣንና የአላፊነት ሥፍራ የተገለሉ የኢትዮጵያ የኢንቴሌጀን
ሲያና የነጋዴ ወገኖች በሀያኛው ምዕተ ዓመት በመጀመሪያ ሶስት
አሥርታት በአንድ በኩል ለጥንታዊ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች መጥፋት
በሌላ በኩል ደግሞ በጃፓኑ ሞዴልና ልምድ መሠረት በማዕከላዊ
የአጼ መንግስት የፖለቲካ አመራር ለብሔራዊ ካፒታሊዝም ግምባታ
ያካሄዱት ትግል በመጨረሻ በአያሌ የውስጥና የውጭ ምክንያቶች ባይ
ሳካም እንኳን በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ተራማጅ የፖለቲካ አንጃ
መሪነት በተጻራሪ የአካባቢ የሥልጣን ተቀናቃኞች ላይ ለማዕከላዊ የዘ
ውድ ሥርዓት ምዕከልና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አደረገ ።

በዚህ ረገድ ከ1909 የጉልተኛ ኩዴታ እስከ 1922 ድረስ በንግሥት
ዘውዲቱ ፤በአቡነ ማቴዎስና በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በሚደገፈው
ወግ አጥባቂ አንጃና በአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን በሚመራው ተቃ
ራኒው አንጃ መካከል በተካሄደው ረጅም የሥልጣን ትግል በአገሪቱ
የኢንቴሌጀንሲያና የነጋዴ ወገኖች ድጋፍ የአልጋ ወራሹ አንጃ የን
ግሥቲቱን አንጃ አሸንፎ የ1923 ሕገ መንግስት ጨምሮ በዘመናዊ የቢ
ሮክራሲ ፤ የትምህርት ፤ የሕግ ፤ የጦር ፤ የፖሊስ ፤ የገንዘብ ፤ የመገናኛ
ድርጅቶችና ተግባራት ዘውዳዊ ሥርዓትን በአዲሱ የኃይለ ሥላሴ
ሥርወ መንግስት ስም የበለጠ አጠናከረ ።

ነገር ግን - የኃይለ ሥላሴ አንጃ ዘውዳዊ ድል ለአገሪቱ ውስ
ብስብ የሥርዓት የገባር ፤ የባርያ ፤ የገበያ ፤ የነጋዴ ፤ የኢንቴሌጀንሲያ ፤
የመሬት ፤ የጠረፍ ፤ የኢምፔሪያሊዝም የአገር መከላከል ችግሮች መፍ
ትሔ አላስገኘም ። የዘመኑ ትልቁ የፖለቲካ ሥራ እንደሆነ በተነገረለት
በ1923 ሕገ መንግስት የኃይለ ሥላሴ ሥርወ መንግስትና የመሳፍንቱ
ጥምር የፖለቲካ ድልና ጥቅም ሲረጋገጥበት የአገሪቱ የኢንቴሌጀንሲያና
የነጋዴ ወገኖች አሁንም ከመንግስት ሥልጣንና የአላፊነት ሥፍራ
ተገለሉ ። ብሔራዊ የገባር የባርያ ፤ የመሬትና የአገር መከላከል ጥያቄ
ዎች ከነጭራሹ በሕገ መንግስቱ አልተጠቀሱም ።

ባጭሩ የኢትዮጵያ የ1923 ሕገ መንግስት በአገሪቱ ሠርቶ አደር
ሕዝብ ላይ የኃይለ ሥላሴ ሥርወ መንግስትና የመሳፍንቱ መደባዊ የፖ
ለቲካ ውል ነው ለማለት ይቻላል ። በዚህ ረገድ በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ
የጉልተኛው መደብ በሚለው ክፍል የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 2 ፤3 ፤5 ፤15፤
19 ለኃይለ ሥላሴ ሥርወ መንግስት የሰጠው ትውልዳዊ የመንግስት ሥል



ጣንና መብት እንዲሁም አንቀጽ 34 ፤35 ፤36 ፤37 ፤38 ፤39 ፤74 ፤75 ፤
ለመሳፍንቱ ወገን በዘውዳዊ ሹመትና ጉልት አማካይነት የሰጠው የኢ
ኮኖሚ መብትና ጥቅም ይታወሳል ። በተጨማሪም የሕገ መንግስቱ አን
ቀጽ 30 ፤31 ፤እና 32 ደግሞ በሕግ መወሰኛና በሕግ መምሪያ ምክር ቤቶች
አማካይነት ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ወገኖች ከሉአላዊው ንጉሥ ጋር
የመንግስትን ሥልጣን እንደሚከተለው ቀርሶ ይሰጣል ።

አንቀጽ 30 ፤ " የንጉሠ ነገሥቱ መንግስት አማካሪዎች በሁለት ክፍል
ይከፈላሉ ። አንደኛው ክፍል የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አማካሪዎች ፤
ሁለተኛው ክፍል የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎች ፤"

አንቀጽ 31 ፤ " የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አማካሪዎችን የሚመርጧ
ቸው ንጉሠ ነገሥቱ ነው ። የሚመረጡትም በመስፍንነትና በሚኒስትር
ነትም ፤ በዳኝነትና በጦር አለቅነትም መንግስታቸውን ብዙ ዘመን ካገ
ለገሉ መኳንንቶች ወገን ነው ። "

አንቀጽ 32 ፤" የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎችን ለጊዜው
ሕዝብ መምረጥ እስኪችል እስከ ተወሰነው ዘመን ድረስ መኳንንቶችና
ሹሞች ይመርጧቸዋል ። "

ከ1909 እስከ 1922 የገባርና የባርያ ሥርዓቶችን ከጉልተኛ
መሳፍንቱና መኳንንቱ ጋር የሚቃወሙ የኢትዮጵያ የኢንቴሊጀን
ሲያና የነጋዴ ወገኖች በጃፓኑ ሞዴልና ልምድ መሠረት በማዕከላዊው
መንግሥት የፖለቲካ አመራር በአገሪቱ ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት
መገንባት ይቻላል በሚል የፖለቲካ አቋም በንግሥት ዘውዲቱ ወግ አጥ
ባቂ የመሳፍንቶች ፤ የመኳንንቶች ፤ የጦር አለቆችና የካህናቶች የሕብረት
አንጃ ላይ በወቅቱ በተራማጅነት ታክቲክ የቀረበውን የአልጋ ወራሽ
ተፈሪን አንጃ መደገፉ ይታወሳል ።

ነገር ግን ወግ አጥባቂው የንግሥቲቱ አንጃ በልዩ ልዩ ምክንያቶችና
መንገዶች እስከ 1922 ድረስ ቆይቶ ከፈረሰ በኋላ በ1923 ሕገ መንግ
ሥት የቀድሞ " ተራማጁ " የአልጋ ወራሽ አንጃ ራሱ በኃይለ ሥላሴ
ሥርወ መንግሥት ስም አሁን ወግ አጥባቂ "የኢትዮጵያ ጳጳሳትና መሳ
ፍንት መኳንንት ፤ ሹማምንትና ሊቃውንት " [40] አዲስ አንጃ ሆኖ ተገኘ ።
የአልጋ ወራሽ ተፈሪ ታክቲካዊ ተራማጅነት በአፄ ዘውድና ዙፋን ላይ
ተወሰነ ።

ቡመሆኑም የኢትዮጵያ የኢንቴሊጀንሲያና የነጋዴ ወገኖች በጃ
ፓኑ ሞዴል መሠረት በአገሪቱ በማዕከላዊ መንግሥት የፖለቲካ አመ
ራር ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት መገንባት ይቻላል በማለት ያካ
ሄዱት ትግል ከውጭ በጠንካራ የኢምፔሪያሊዝም ግፊት ከውስጥ ደግሞ
በተጠናከረ የገባር ሥርዓት ተፅዕኖ ምክንያቶች ተግባራዊ የማይሆን
ምኞት ብቻ ሆኖ ቀረ ።

በአለፈው ምዕተ ዓመት ኢትዮጵያና ጃፓን በአገር ውስጥ ተመሳሳይ
የጦር አበጋዞች ሥርዓት ነበራቸው ። ከውጭም ደግሞ በ1850ዎቹ ሁለ
ቱም በአንድ ዘመን ተመሳሳይ ግፊት ደረሰባቸው ። ስለዚህ በዘመናዊ
የኢትዮጵያና የጃፓን ታሪክ ተቃራኒ የኋላ ቀርነትና የዕድገት ልዩነት
ያስከተለው መሠረታዊ ነገር ዘመናዊ ትምህርትና የፖለቲካ አሳብ በሚመ
ለከት የሁለቱ አገሮች መሪዎች የነበራቸው የፖሊሲ ፤ የአመራርና የተ
ግባር ልዩነት ነው ለማለት ይቻላል ።



16 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ (1877 - 1911)

ምንጭ ፡ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፡ መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር (1916)

በጥንታዊ የአገሩ ትውፊት መሠረት ፤ የጃፓን መንግሥት የተመሠ
ረተው ከዛሬ 2600 ዓመታት በፊት በ660 ዓመተ ዓለም ነው ። በዘመነ
ክርስትና በአራተኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ጃፓን በማዕከላዊ የአፄ
መንግሥት የሚገዛ አገር እንደ ነበር በሰነድ ተረጋግጧል። ከዚያ በኋላ
ከ1192 እስከ 1867 ድረስ በጃፓን ሾጉኖች የተባሉ አካባቢያዊ ጉልተኛ
የጦር አበጋዞች ዘመን ነበር ። በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት እስከ
1867 ድረስ በአካባቢ ሾጉኖች የሚገዛው የጃፓን አገር ከውጪ ዓለም



የሩሲያ ፤ የአውሮፓና የአሜሪካ መንግሥታት የንግድና የፖለቲካ ግፊት
ሥር ዋለ ። [41] የተጠቀሱ የውጭ ኃይሎች የአገሪቱን የአካባቢ ሾጉኖች
በጦርና በፖለቲካ ግፊት በማስገደድ በውል ስም የጃፓንን ብዙ የጠረፍ
ወደቦችና ደሴቶች በቀጥታ ያዙ ።


በዚህ ጊዜና ሁኔታ የጃፓን መሪዎች ዘመናዊ ትምህርትና ጦር
ታጥቆ የመጣውን የውጭ ኃይል በራሳቸው ጥንታዊ የግባር ኢኮኖ
ሚና በጦር አበጋዙ ጉራዴ መቋቋም እንደማይችሉ በትክክል በማወቅ
የማይጂ ተሀድሶ ( 1861-1881) ተብሎ በሚታወቀው ብሔራዊ የለውጥ
እንቅስቃሴና የፖለቲካ ፕሮግራም (1) ለማዕከላዊ የዘውድ መንግሥት
ምዕክልና ፤(2) በሾጉን የጦር አበጋዞች ለሚመራው የግባር ሥርዓት ፍጻ
ሜና (3) በአገሪቱ ለዘመናዊ የትምህርት ፤ የሳይንስ ፤ የቴክኖሎጂ ፤ የሕግ
የኢኮኖሚ ፤ የፖለቲካና የጦር ድርጅቶች ዕድገትና መስፋፋት ፈጣን ብሔ
ራዊ እርምጃዎችን ወሰዱ ።

በዚህ የማይጂ ተሀድሶ ወቅትና ፕሮግራም የጃፓን ጥንታዊ የግባር
ሥርዓት ከሾጉን የጦር አበጋዞችና ወታደሮች ጋር ተለወጠ ፤ ዘመናዊ
የጦር ድርጅት ተፈጠረ ፤ ከፍተኛ የጥናት መልእክተኞች ወደ አውሮፓና
አሜሪካ ተልከው ዘመናዊ የትምህርት ፤ የሕግና የፖለቲካ ሥርዓቶችንና
ድርጅቶችን በፍጥነት ተምረው ተመለሱ ። ዘመናዊ ሕገ መንግሥትና
የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈጠሩ ። ባጭሩ ከ1861 እስከ 1881 ድረስ በሀያ
ዓመታት ውስጥ ጃፓኖች በማይጂ ማዕከላዊ መንግሥት የፖለቲካ አመ
ራር የራሳቸውን ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት በመገንባት አገራቸ
ውን ከውጭ ኃይሎች ግፊትና ተፅዕኖ ነፃ ከማድረግ አልፈው ከዘመኑ
ኃያላን የዓለም መንግሥታት አንዱ ለመሆን በቁ ።

በዘመነ ግባር የኢትዮጵያ አገር መሪዎችና ባለሥልጣኖች በውጭ
ኃይሎች ግፊትና ተፅዕኖ ላይ የአገር ግምባታ ዓላማ ቢኖራቸውም በሌላ
በኩል እንደ ጃፓኑ አቻዎቻቸው የአገር ግምባታ ዓላማቸውን ተግባራዊ
ለማድረግ የሚያስችላቸው ብሔራዊ ተጨባጭ የሥራ ፕሮግራም አልነ
በራቸውም ። የሥልጣን ጠላቶቻቸውን ለመግዛት ከሚያስችላቸው ጠመ
ንጃ ሌላ እንደ ጃፓኑ አቻዎቻቸው የኢትዮጵያ ጉልተኛ ነገሥታትና መሳ
ፍንቶች ከውጪ ዓለም ዘመናዊ ትምህርትና ቴክኖሎጂ ከአዲስ የፖለ
ቲካ አሳብና ትምህርት ጋር ወደ አገር ለማስገባት በቂ ጥረት አላደረጉም።
በተቃራኒው ከውጪ ዓለም ከፍተኛ ወጭ ከፍለው ባስገቡት የጦር መሣ
ሪያ ጥንታዊ የግባር ሥርዓትን የበለጠ አጠናከሩ ። በዚህ ሁኔታ የፖለቲካ
መድረክና ሥልጣን ያልነበራቸው የኢትዮጵያ የኢንቴሊጀን ሲያና
የነጋዴ ወገኖች በጃፓኑ ሞዴል ብሔራዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ግም
ባታ የማይቻል ነገር ሆነ ።



17. የገባር አገልግሎት በ1870ዎቹ በሸዋ
ምንጭ ፡ J. Borelli, Ethiopie Meridionale (1890)



17. የገባር አገልግሎት በ1870ዎቹ በሸዋ
ምንጭ ፡ J. Borelli, Ethiopie Meridionale (1890)

ባጭሩ የጃፓን መሪዎች ከ1861 እስከ 1881 ድረስ በሀያ ዓመታት ውስጥ በሩሲያ ፤ በአውሮፓና በአሜሪካ መንግሥታት ግፊትና ተፅዕኖ ላይ በዘመናዊ ትምህርትና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት መዋሪያ በአገራቸው ፈጣን የኢኮኖሚና የሥርዓት ለውጥ አካሂደው የአገራቸውን ብሔራዊ ነፃነትና የግዛት አንድነት ከኢምፔሪያሊዝም ጥፋት ለማዳን ሲችሉ ፤ በአንፃሩ በሥልጣን ጉዳይ እርስ በርሳቸው ዘወትር የሚዋጉ አንዱ የሠራውን ሌላው የሚያፈርሰው የኢትዮጵያ ነገሥታትና ባለሥልጣኖች ከ1850 እስከ 1928 በሰማንያ ዓመታት ውስጥ የጃፓን አቻዎቻቸው እንደ አደረጉት በዘመናዊ የትምህርትና የፖለቲካ መዋሪያዎች በአገሪቱ ውስጥ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሥርዓት መሠረታዊ ለውጥና ዕድገት ለማካሄድ ባለመቻላቸው በመጨረሻ የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ለፋሽስቶች ወረራና ጥፋት ተጋልጦ ተገኘ ።

## የዘመን ገባር ፍጻሜ

የ1928- 1933 የፋሽስቶች ወረራ [42] በዘመናዊ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብና ታሪክ ላይ ያስከተላቸው ነገሮች ፤ ሁኔታዎችና ሂደቶች በጣም



ብዙና መሠረታዊ ናቸው ። አንደኛ ፤ በ1928 በትግራይ ፤ በኦጋዴን፤በባሌና በሲዳሞ የጦር ግምባሮች የመሳፍንቱ የግል ጦር ፈረሰ ። ሁለተኛ ፤ የአፄው መንግሥትን ምዕክልና ይቃረኑ ከነበሩት ኃይለኛ መሳፍንቶች ፤ መኳንንቶችና ባለሥልጣኖች ብዙዎቹ በሞትና በስደት ተወገዱ ።

ሦስተኛ ፤ በቅድመ ጦርነት ለካፒታሊዝም ሥርዓት ይታገሉ ከነበሩት የኢንቴሊጀንሲያና የነጋዴ ወገኖች ብዙዎቹ በሞትና በስደት አለቁ ። አራተኛ ፤ ጥንታዊ የገባርና የባርያ ሥርዓቶች ተደመሰሱ ። አምስተኛ ፤ ጠላት በአገሪቱ የካፒታሊዝም ገበያና ሥርዓት ለማስፋፋት በነበረው ፕሮግራም ሰፊ የመሠረተ ልማት ሥራ ዘረጋ ። ስድስተኛ ፤ ለኤርትራ በነፃነት እንደገና ከእናት አገር ጋር ለመቀላቀል አመች ሁኔታዎችና ምክንያቶች ተፈጠሩ ።

እነዚህ የጦርነቱ ውጤቶች ከ1933 እስከ 1966 ድረስ በኢትዮጵያ ለዘውዳዊ ሥርዓት ምዕክልናና ለጅምር የካፒታሊዝም ሥርዓት ዕድገት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በሚቀጥለው ክፍል በዝርዝር ይታያል ።

## ምዕራፍ 3.

## የ1928-1933 ጦርነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ውጤቶች

በ1928-1933 የፋሽስቶች ወረራ ዘመን ከትግልና ልምድ የተገኘው የኢትዮጵያ የብሔረሰቦች ግንዛቤና በድህረ ጦርነት የአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ የፖለቲካ ምዕክልና ፖሊሲ በመጋጨት በ1930ዎቹና በ1940 ዎቹ በአገሪቱ በየአካባቢው የብሔረሰብና የሃይማኖት ጭቆና ምዕራፍ አስከተሉ ።

በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ የ1928-1933 የሽግግር ዘመን በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ሉአላዊነት በውጭ ጠላት የተደፈረበት በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱ ረጅም ብሔራዊ አብዮት በየፈርጁ የተጠነሰሰበት ታላቅ የፖለቲካዊ ፤ የኢኮኖሚያዊ ፣ የማህበራዊና የባህላዊ እንቅስቃሴ ዘመን ነው ለማለት ይቻላል ። በዚህ ረገድ አንደኛ ፣ በ1928 የኢትዮጵያ ጉልተኛ የገዥው መደብ በወራሪው ጠላት ተሸንፎ ሲፈርስ ከመደቡ ከፍተኛ የመሳፍንት ፣ የመኳንንት የካህናትና የጦር አባሎች ግማሾቹ በጠላት ተገደሉ ። ከፊሎቹ ከንጉሡ ጋር በስደት ከአገር ወጡ ። የአገሪቱ የባርያና የገባር ሥርዓቶች ከጉልተኛ የገዥው መደብ ጋር ፈረሱ ። በመሆኑም የቀድሞ ባሮች የአገሪቱ ነጻ ዜጎች ሆኑ ።

ሁለተኛ ፣ የገባር ሥርዓት የፖለቲካ መሳሪያ የነበረው የጉልተኛው የግል ጦር በ1928 በትግራይ ፣ በኦጋዴን በባሌና በሲዳሞ የጦር ግምባሮች ፈረሰ።

ሶስተኛ ፣ በገጠር በቀድሞ የገዥው መደብ አባሎች ተይዞ የነበረው የሕዝቡ መሬት እንደገና በሕዝቡ ተወሰደ ።

አራተኛ ፣ በፋሽስቶች ሰፊ የኮንስትራክሽንና የውትድርና ሥራዎች ብዙ የቀድሞ ባሮችና ገባሮች ቅጥር ሠራተኞች ሆኑ ። በዚህ አኳያ ለምሳሌ በ1928 - 1932 ፋሽስቶች በአገሪቱ ከ4400 በላይ ኪሎሜትር መንገዶችን ከ8,334 ድልድዮች ጋር በ2,967 300,000 ሊሬ ወይም በ32, 970,000 ፓውንድ እስቴሪሊንግ እንደሠሩና በሥራውም ከ60,000 ነጮች ጋር 43,000 ኢትዮጵያዊ ሠራተኞች በቅጥር እንደተሰማሩበት ታውቋል ።[1] እንዲሁም በአገር ደረጃ 25 ሆስፒታሎችና 14 ሆቴሎች ከብዙ የፖስታና የቴሌፎን ድርጅቶች ጋር በጠላት ተሰርተው ነበር ።[2]

<u>ሠንጠረዥ 1</u>

<u>በ1928—1932 በኢትዮጵያ በፋሽስቶች የተሰራ የመንገድና የድልድይ ሥራ ፣ የሠራተኞች ብዛትና ወጪ በሊራ</u>

| የመንገድ ስም | የመንገድ ርቀት በኪ.ሜ. | የድል ድይ ብዛት | የሠራተኞች ብዛት ነጭ | የሠራተኞች ብዛት ኢትዮ. | የወጭ መጠን በሊራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. አሥመራ-ጎንደር-አአ | 1246 | 8334 | 60,000 | 43,000 | 2,967,300,000 |
| 2. አሥመራ —ደሴ—አአ | 1093 | | | | |
| 3. አሰብ—ደሴ | 531 | | | | |
| 4. ጎንደር — ደሴ | 496 | | | | |
| 5. አሥመራ - ተሰነይ - ሰብ. | 382 | | | | |
| 6. አዲስ አበባ - ጂማ | 350 | | | | |
| 7. አዲስ አበባ — ነቀምት | 333 | | | | |
| | 4421 | 8334 | 60,000 | 43,000 | 2,967,300,000 |

ምንጭ ፣ F. Quaranta, Ethiopia . . (1939)

አምስተኛ ፣ በአንድ በኩል ከቀድሞ የገዥው መደብ ከፍተኛ የመሳፍንት ፣ የመኳንንት የካህናትና የጦር አባሎች ከፊሎቹ በትግራይ በኦጋዴን ፣ በባሌና በሲዳሞ የጦር ግምባሮች ሞቱ ። ከፊሎቹ ከንጉሡ ጋር ከአገር ተሰደዱ ። የተቀሩት ወደ ጠላት ገቡ ።[3] በሌላ በኩል በእነብላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያት ፣ ባላምባራስ አበበ አረጋይ ፊታውራሪ ገረሱ ዱኪ ፣ ልጅ ዘለቀ በላይና በሌሎችም መሪነት በአገሪቱ የበታች ሹማምንቶችና ተራ ዜጎች ታላቁ የኢትዮጵያ የአርበኞች ትግል ተጀመረ ። ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል የኢትዮጵያ አርበኞች በጋራ ብሔራዊ ጠላት ፋሽስቶች ላይ በየአካባቢያቸው በአመጽ ከመነሳት ባሻገር በመካከላቸው ብሔራዊ ሕብረትና የፖለቲካ ፕሮግራም አልነበራቸውም ። ይህም ሁኔታ ከዚህ በታች እንደሚታየው ፣ በድህረ ጦርነት በቀድሞ አርበኞችና ስደተኞች መካከል በሚከሰተው የሥልጣንና የፖለቲካ ትግል በአርበኞቹ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል ።[4]



ምንም እንኳ በመካከላቸው አንድ ብሔራዊ ማዕከልና የፖለቲካ ፕሮግራም ባይኖር ፣ በአገሪቱ ረጅም ታሪክ የኢትዮጵያ የ1928-1933 የአርበኞች እንቅስቃሴ ፖለቲካዊና ታሪካዊ ውጤቶች ብዙ ናቸው ። በዚህ አኳያ የአርበኞች ትግል በአንድ በኩል ፋሽስቶች ከከተማ ክልልና ከመንገድ ዳር አልፈው በገጠር ሥልጣናቸውንና ሥራቸውን እንዳይመሠርቱ አደረገ። ከሁሉም በላይ የቀድሞ ንጉሳዊ የገዥው መደብ በወታደራዊና በፖለቲካዊ ሽንፈት ከአገር ከወጣ በኋላ ሕዝባዊው የአርበኞች ትግል የኢትዮጵያን ሕዝብ በወራሪው ጠላት ላይ በብሔራዊ አንድነት አስተባበረ ።[5] በመጨረሻም የኢትዮጵያ የአርበኞች ትግልና ድል በ1932 - 1933 በፋሽስቶች ላይ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሕብረት ለተካሄደው ወታደራዊ ትግልና ድል መነሻ ሆነ ።[6]

ስድስተኛ ፣ በ1928 - 1933 የወረራ ዘመን ፋሽስቶች ከፋፍለህ ግዛ በሚለው አሠራር የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጐት ለማጠናከር በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎችና ማህበረሰቦች ዘንድ በሥፍራ ፣ በሥራ ፣ በብሔረሰብ፣ በማህበራዊ ጉዳይ ፣ በቋንቋ ፣ በሃይማኖት ፣ በሥልጣን ፣ በመሬትና በዜግነት ጥያቄዎች አንዱን ክፍል የሚያጠቃ ሌላውን ደግሞ የሚጠቅም መንቲያ ፖሊሲ መሠረቱ ።[7]

በዚህ ረገድ ፣ በግንቦት 1928 ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ከኤርትራና ከሶማሊያ ኮሎኒዎቻቸው ጋር አጣምረው በአንድ የኢጣሊያ ምሥራቅ አፍሪካ ግዛተ አጼ ሥር በአዋጅ መሠረቱ ። እርሱንም ከአስተዳደር አኳያ በስድስት የአማራ ፣ የሐረር ፣ የኦሮሞ - ሲዳማ ፣ የሸዋ ፣ የኤርትራና የሶማሊያ የአስተዳደር ክልሎች ከፈሉ ።[8]

በዚህ ታላቅ የኢጣሊያ ምሥራቅ አፍሪካ ግዛተ አጼ የፖለቲካ ቅንጅትና ድርጅት ፣ የኢጣሊያ ፋሽስት ባለሥልጣኖችና ምሁራን በሰሜን የኢትዮጵያን የትግራይና የአፋር አካባቢዎችን ከኤርትራ ኮሎኒያቸው ጋር አጣምረው በኤርትራ ክልል ፣ በምሥራቅ የኢትዮጵያን የኦጋዴን ክፍል ከሶማሊያ ኮሎኒያቸው ጋር አጣምረው በሶማሊያ ክልል ፣ በደቡብ ምሥራቅ የሐረርጌና የአርሲ ክፍላተሀገር አጣምረው በሐረር ክልል ፣ በደቡብና በምዕራብ የኢትዮጵያን ብዙ ኩሻዊ ፣ ኦሞአዊና ናይሎቲካዊ የቋንቋ ቤተሰቦችንና ማህበረሰቦችን በአንድነት አጣምረው በኦሮሞ - ሲዳማ ክልል ፣ በመሀልና በሰሜን ምዕራብ የአማራ ማህበረሰቦችንና ከፊል የኦሮሞ ማህበረሰቦችን አጣምረው በሁለቱ የአማራና የሸዋ ክልሎች አደራጁ ።

በፋሽስቶች አመለካከትና ግንዛቤ ፣ በምኒልክ ፖሊሲ መሠረት የኢትዮጵያን በሀውርታዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ በበላይነት የሚገዛው ብሎም በአገሩ ለኢጣሊያ ኮሎኒያዊ ጥቅምና ፀጥታ አደገኛ ጠላት የአማራ ማህበረሰብ ነው ።[9] ፋሽስት ባለሥልጣኖች ከዚህ አቋማቸው

በመነሳት በመጀመሪያ ዓመታት ከሞሶሎኒ በተሰጣቸው የፖሊሲ መመ
ሪያ በአማራ ማህበረሰብና በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ መንግሥታዊ
የጥቃት እጅ አነሱ ።

በዚህ ረገድ ለምሳሌ ከ600,000 እስከ 800,000 የሚገመቱ አማ
ርኛ የሚናገሩ ነዋሪዎች ከሐረርና ከኦሮሞ - ሲዳማ የአስተዳደር ክልሎች
ወደ ሸዋና አማራ የአስተዳደር ክልሎች እንዲባረሩ ፣ የአማራ ማህበረሰብ
አባሎች በሌላ የአስተዳደር ክልሎች የፖለቲካ ሥልጣን እንዳይዙ ተቀ
ጥረው እንዳይሠሩ ፤ [10] በሌላ የአስተዳደር ክልሎች በአማርኛ ቋንቋ
መንግሥታዊ ሥራ እንዳይሠራበት ለማድረግ ፋሽስቶች ብዙ የፖሊሲ
እርምጃዎችን ወሰዱ ። [11] በአማራና በሸዋ የአስተዳደር ክልሎች አማር
ኛን ፣ በኤርትራ ክልል ትግርኛን በሐረር ክልል አረብኛን ፣ በኦሮሞ-ሲዳማ
ክልል ኦሮምኛንና ከፍኛን የሥራና የትምህርት ቋንቋዎች አደረጉ ። [12]

በሌላ በኩል ፋሽስቶች በምሥራቅ አፍሪካ ያጼ ግዛታቸው በክብር ፣
በመብት ፣ በጥቅም ፣ በማህበራዊ አገልግሎት የኤርትራና የሶማሌ ተወላ
ጆችን የመጀመሪያ ምርጫ የአማራ ተወላጆችን ደግሞ የመጨረሻ ምርጫ
ያደርጉ ጀመር ። [13] ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በሁሉም ጉዳይ
የመጀመሪያ ዕድል ይሰጡ ነበር ። [14] በዚህ ነገር በዲፕሎማሲና በንግድ
ዓለም አቀፍ ድጋፍ ለማግኘት የኢጣሊያ ፋሽስት መሪ ሞሶሎኒ ለዓለም
በአጠቃላይ ለመካከለኛው የእስላሙ ዓለም በተለይ ራሱን በኢትዮጵያ
የእስላም ሕዝቦች ጠበቃና ሐዋርያ አድርጎ ያቀርብ ጀመር ። [15]

በተዋሃደው የሐረርጌ - አርሲ ክልልና በሐረር ከተማ ፋሽስት ባለሥ
ልጣኖች በፖለቲካ ምክንያት በመንግሥት ሥራ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በሃይማ
ኖት ጉዳይ ፣ በውትድርና አገልግሎት ለአደሬ ማህበረሰብ አባሎች የቅድ
ሚያ ሥፍራ ይሰጡ ነበር ። ለምሳሌ በሐረር ብቻ ለአርባ ሰባት ቃዲ
ዎች ( የመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ) እና ለአርባ የዲዋን አላፊዎች ( የሃ
ይማኖት ጉዳይ ሹሞች ) በድምር የ100,000 ሊራ ደሞዝ ይከፈላቸው
ነበር ። [16] በ1929 በሐረር የቁራን ትምህርት ቤት 450 ተማሪዎች ነበሩ ።
በተጨማሪም ፋሽስት ባለሥልጣኖች ለአፍሪካ ቀንድና ለቀይ ባህር
አካባቢ እስላሞች በሐረር ከተማ የእስላማዊ ጥናት ዩኒቨርስቲ ለማቋቋም
ፕላን ነበራቸው ። [17]

ፋሽስት ባለሥልጣኖች በኢትዮጵያ ሁለተኛው እስላማዊ ማዕከልና
የኦሮሞ-ሲዳማ የአስተዳደር ክልል መዲና አድርገው በገነቡት የጂማ
ከተማ እንዲሁም አንድ እስላማዊ ጥናት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም ፕላን
ነበራቸው ። ከኢትዮጵያ የእስላም ማህበረሰብና ከውጪ የእስላም ዓለም
ጋር የቀረበ ግንኙነት ለመፍጠር በነበራቸው ዓላማ ደግሞ ፋሽስቶች ለኢ
ትዮጵያ እስላሞች ዓመታዊ የመካ ጉብኝት ፕሮግራም ጀመሩ ። በዚሁ



ፕሮግራም መሠረት በ1931 ብቻ 3,585 ምዕመናን ወደ ሳውዲ አረቢያ
እንደሄዱ ታውቋል ። [18]

በአገር ውስጥም እስልምና ለማስፋፋት በነበራቸው የፖለቲካ ዓላ
ማና ፕላን ፣ በ1928 -1933 ፋሽስቶች በኢትዮጵያ በትንሹ አምሳ አዳዲስ
የድንጋይ መስጊዶችን እንደገነቡ ፣ አሥራ ስድስት አሮጌ የድንጋይ መስ
ጊዶችን እንደ አደሱና በየአካባቢው ሁሉ ከእንጨትና ጭቃ ብዙ መስ
ጊዶች እንደሠሩ ተረጋግጧል ። [19] በእያንዳንዱ መስጊድ ትምህርት
ቤት ነበር ። ከሁሉም በላይ በጦርነቱ ዘመን በፋሽስቶች ድጋፍ የኢት
ዮጵያ እስላሞች በንግድና በእርሻ ሥራዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ተሰማር
ተው እንደነበር የዘመኑ ታሪክ ያሳያል ።

ሰባተኛ ፣ በ1928 -1933 ጦርነት ዘመን በኢትዮጵያ አንድ ታላቅ
ማህበራዊና ባህላዊ ክስተት በከተማና በደቡብ የገጠር አካባቢዎች ከእስ
ስልምና ጐን የሚሲዮናውያን ሃይማኖትና ትምህርት መስፋፋት ነው ።
በዚህ ወቅት የፋሽስቶች ጦርነት ራሱ በኢትዮጵያ ለአገር አቀፍ
የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ሥራ ዕድገት አመቺ ሁኔታና መን
ገድ ሆነ ።

በሌላ በኩል በጦርነቱ መጀመሪያ ዓመታት ፋሽስቶች የፕሮቴስ
ታንት ሚሲዮናውያንን ከአገር እንዳባረሩና በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ
ቤተ ክርስቲያን ላይ ደግሞ ብርቱ የጭቆና እጃቸውን እንደአነሱ
ይታወሳል ። ይሁን እንጂ ፣ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ፣ የፕሮቴስ
ታንት ሚሲዮናውያን በፋሽስቶች ከተባረሩ በኋላ በአገሪቱ በተለይም
በደቡብ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትና ትምህርት በአገር ተወላጆች አመ
ራር እያደገ እየተስፋፋ ሄደ ።

ስምንተኛ ፣ በ1933 - 1945 በሰሜን ኢትዮጵያ የኤርትራ ነፃነትና
ከእናት አገር ጋር እንደገና አንድ የመሆን ትግልና ድል ከ1928-1933
የፋሽስቶች ጦርነት ጋር በቅርብ የተያያዘ ብሎም የጦርነቱ አንድ ታላቅ
ፖለቲካዊና ብሔራዊ ውጤት ነው ።

በዚህ ወቅት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት የኤርትራ ክፍለ
ሀገር ተወላጆች መጀመሪያ በፀረ ፋሽስቶች ጦርነት በልዩ ልዩ የውጊያ
መስኮችና ግምባሮች ተሰልፈው በኋላ በኤርትራ ነፃነት ትግል ወቅት
ደግሞ በአገር አንድነት ማህበር አርማ ሥር ተደራጅተው የፈጸሙት
ሥራ በታሪክ የታወቀ ነው ። በሚከተሉት ሠንጠረዦች በ1928 - 1933
ጦርነትና በ1930ዎቹ በመልሶ ያገር ግምባታ ወቅት በልዩ ልዩ የት
ግል መስኮችና ግምባሮች የተሳተፉ የኤርትራ ተወላጆች ዝርዝር ይታ
ያል ።

## ሠንጠረዥ 2

### በ1928 — 1933 ጸረ ፋሽስቶች ጦርነት በልዩ ልዩ የጦር ግምባሮች የተሳተፉ የኤርትራ ተወላጆች

| ተ.ቁ. | በተለያዩ የጦር ግምባሮች የተሰለፉ ወታደሮችና አርበኞች | የጦርነት ዘመን | የጦርነት ግምባር | የሰው ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በደቡብ ግምባር የተዋጉ የሞቱ የተሰደዱ ሰዎች | 1928 | ደቡብ | |
| | ሀ. ፊታውራሪ የጦር አለቆች | | | 1 |
| | ለ. ቀኛዝማች የጦር አለቆች | | | 1 |
| | ሐ. ግራዝማች የጦር አለቆች | | | 14 |
| | መ. ባላባራስ የጦር አለቆች | | | 58 |
| | ሠ. ባሻ የጦር አለቆች | | | 16 |
| | ረ. ተራ ወታደሮች | | | 146 |
| 2. | በምዕራብ ግምባር የተዋጉ፣ የሞቱ የተሰደዱ ሰዎች፣ | 1928 | ምዕራብ | |
| | ሀ. አምሳ አለቃ የጦር አዛዦች | | | 14 |
| | ለ. ሻምበል የጦር አለቆች | | | 2 |
| | ሐ. ተራ ወታደሮች | | | 75 |
| | መ. ሲቪል የጦር አባሎች | | | 10 |
| 3. | የኤርትራ አርበኞች በአምስቱ የጦርነት ዘመን | 1928—1933 | በአገር አቀፍ ደረጃ | 445 |
| 4 | በ1928 የጠላትን ግምባር እየከዱ ከወገን ጦር ጋር የተቀላቀሉ ወታደሮች | 1928—1933 | | |
| | ሀ. በ1928 በትግራይ ግምባር | | በትግራይ ግምባር | 5000 |
| | ለ. በ1928 በኦጋዴን ግምባር | | በኦጋዴን ግምባር | 2000 |
| | ሐ. በ1933 በትግራይ ግምባር | | በትግራይ ግምባር | 10000 |
| | መ. በ1933 በኦጋዴን ግምባር | | በኦጋዴን ግምባር | 3000 |
| 5 | በ1928 የጠላትን ግምባር እየከዱ ከወገን ጦር ጋር የተቀላቀሉ የጦር አለቆች | | | |
| | ሀ. ፊታውራሪ የጦር አለቆች | | | 1 |
| | ለ. ቀኛዝማች የጦር አለቆች | | | 7 |
| | ሐ. ግራዝማች የጦር አለቆች | | | 24 |
| | መ. ሻምበል የጦርአለቆችች | | | 7 |
| | ሠ. የመቶ አለቃ የጦር አዛዦች | | | 24 |
| | ረ. ባለሌላ ማዕረግ የጦር አለቆች | | | 3 |
| | ጠቅላላ ድምር | | | 20757 |

ምንጭ ፡ UN, Documentation de L'Ethiopie (1948)



## ሠንጠረዥ 3

### በድህረ ጦርነት በኢትዮጵያ ያገር ግምባታ ተግባር የኤርትራ ተወላጅ በልዩ ልዩ መስኮችና ደረጃዎች

| ተ.ቁ. | የመንግሥት መሥሪያ ቤት | የኤርትራ ተወላጆች ብዛት በመ/መ/ቤት | በጦር ሠራዊት የኤርትራ ተወላጅ ብዛት | በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች የኤርትራ ተወላጆች | በመሀል አገር የሚኖሩት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግርማዊ ጃንሆይ ጽሕፈት ቤት | 1 | 2065 | 2279 | 200,000 |
| 2 | ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ | 6 | | | |
| 3 | ጽሕፈት ሚኒስቴር | 4 | | | |
| 4 | በፕሬስና ፕሮፓጋንዳ ክፍል | 29 | | | |
| 5 | ባገር ግዛት ሚኒስቴር | 107 | | | |
| 6 | ባገር ግዛት ሚ/ር በጸጥታ ክፍል | 532 | | | |
| 7. | ጦር ሚኒስቴር | 342 | | | |
| 8. | ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር | 6 | | | |
| 9 | ፍርድ ሚኒስቴር | 38 | | | |
| 10 | እርሻ ሚኒስቴር | 8 | | | |
| 11 | ፖ ቴሌና ቴሌግ. ሚኒስቴር | 154 | | | |
| 12 | መገናኛ ሚኒስቴር | 39 | | | |
| 13 | ገንዘብ ሚኒስቴር | 189 | | | |
| 15 | አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት | 13 | | | |
| 16 | ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት | 7 | | | |
| 17 | ጠላት ንብረት ክፍል | 139 | | | |
| | ድምር | 1645 | 2065 | 2279 | 200,000 |

ምንጭ ፡ UN, Documentation de L'Ehtiopie (1948)

ከዚህ በላይ በቀረበው የሠንጠረዥ መረጃ እንደሚነበበው ፥ በ1933 - 1945 በኢትዮጵያ ብሔራዊ መልሶ ያገር ግምባታና የኤርትራ ነፃነት ትግል ዘመን ፥ ከኤርትራ ተወላጆች ከ1600 በላይ የሚሆኑት በመንግሥት ሥራ በልዩ ልዩ የሥልጣንና አላፊነት ደረጃዎች አገሪቱን በግምባር ያገለግሉ ነበር ። በ2000 የሚቆጠሩት ሌሎች ደግሞ በልዩ ልዩ ማዕረግና አላፊነት የአዲሱ ብሔራዊ የጦር ሠራዊት አባሎችና አደራጆች ነበሩ ። እንዲሁም ከ2200 በላይ የሚሆኑት በመሀል አገር በልዩ ልዩ ከተሞችና የአስተዳደር አካባቢዎች በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው የሚኖሩ ዜጎች ነበሩ ።

ባጭሩ በ1940ዎቹ በአንድ ሚሊዮን ከሚገመተው ከኤርትራ ጠቅላላ ሕዝብ በ200,000 የሚቆጠረው ወይም ሀያ በመቶ የሚሆነው በልዩ ልዩ መንገዶችና ምክንያቶች በባዕዳን እጅ ከነበረው ከትውልድ ክፍለ ሀገሩ ሸሽቶ በመሀል አገር በተለያዩ ከተሞችና የአስተዳደር አካባቢዎች ይኖር ነበር ።[20]

ከዚህ በላይ በቀረበው ጥቅል የታሪክ ትንተና የ1928 - 1933 የፋሽስቶች ጦርነት በኢትዮጵያ ፤

1. የቀድሞ ባሮችና ገባሮችን ማህበራዊ አርነት ፤
2. በ1928 በትግራይ በአጋዴን በባሌና በሲዳሞ የጦር ግምባሮች የአካባቢ ጦርና የጦር አበጋዞች ፍጻሜ ፤
3. በደቡብ ኢትዮጵያ ዱሮ በማዕከላዊው መንግሥት ሥር የተያዘው የሕዝብ መሬት እንደገና በሕዝቡ እጅ መግባት ፤
4. ብሔራዊ የከተማ ፥ የመገናኛ የንግድ ፥ የፋብሪካ የወዛደር መደብ ዕድገት ፤
5. ብሔራዊ የአርበኞች ክስተትና የነፃነት ትግል ፤
6. የንጉሡ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ስደት ፥
7. በአገሪቱ የእስላም ማህበረሰብ የፖለቲካ ንቃትና ዕድገት ፥
8. የሚሲዮናውያን ሃይማኖትና ትምህርት ዕድገትና መስፋፋት ፥
9. የኤርትራ ብሔራዊ የነፃነት ትግል መነሻ ፥ ጥያቄዎችን ጨምሮ በፖለቲካ ፥ በኢኮኖሚ ፥ በሃይማኖት ፥ በትምህርት በባህል

መስኮችና ተግባራት ብዙ መሠረታዊ ሁኔታዎችን ሂደቶችንና ኃይሎችን ያስከተለ ሁለአቀፍ አገር አቀፍ የመከራ የሞት ፥ የጥፋት ፥ የአርነት ፥ የለውጥ ፥ የዕድገት ባጭሩ የብዙ ቅራኔዎች ዘመን እንደሆነ ለማየት ተችሏል ።



# ክፍል ሁለት

## የድምር ካፒታሊዝም ላዕላይ መዋቅር

## 1933-1966

### ምዕራፍ 1. ፍጹማዊው የዘውድ ሥርዓት ምዕክልና የመንግሥት አደረጃጀትና አገልግሎት

በአለፈው ምዕተ ዓመት በተከታታይ የተነሱ የኢትዮጵያ ነገሥታት ቴዎድሮስ ፤ ዮሐንስና ምኒልክ በየዘመናቸው ጠንካራ የሆነ ማዕከላዊ የዘውድ ሥርዓት ለአገሪቱ ብሔራዊ አንድነትና ግምባታ አስፈላጊ የፖለቲካ መሠረትና መሣሪያ ነው የሚል ብርቱ የፖሊሲ አቋም ነበራቸው ።

በዚህ አቋማቸው አጼ ቴዎድሮስ በተቃዋሚ ጉልተኛ መሳፍንቶችና ቤተ ክርስቲያን ላይ በጦር ኃይል ጠንካራ የሆነ ማዕከላዊ የዘውድ ሥርዓት ለመገንባት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረ ። እንዲሁም አጼ ዮሐንስ ሃይማኖትን እንደ መሣሪያ በመጠቀም በኢትዮጵያ በሀውርታዊ ሕብረተሰብ ብርቱ ማዕከላዊ የዘውድ ሥልጣንና ሥርዓት ለመገንባት የነበራቸው የፖሊሲ ዕቅድና ተግባር በውጭ ኃይሎች ግፊት ከሸፈ ።

የአጼ ቴዎድሮስና የአጼ ዮሐንስ የአገር ግምባታ ፖሊሲና ተግባር በተከታታይ በመቅደላና በመተማ ጦር ሜዳዎች ከፈረሰ በኋላ ፤ አፄ ምኒልክ በአርሶ አደሩ መደብ ላይ የጉልተኛ መሳፍንቶችንና የቤተክርስቲያንን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅም በማስከበር በዘመናቸው የማዕከላዊውን ዘውድ ሥልጣንና ሥርዓት በኃይል አጠናከሩ ።

ነገር ግን በዘመነ መንግሥታቸው ፍጻሜ በአካባቢ ኢኮኖሚና በግል ጦር የተደራጁ ጉልተኛ መሳፍንቶች የማዕከላዊው ዘውድ ሥልጣን ባላንጣዎች ፤ ታላላቅ የገባርና የባርያ ጌቶች ፤ ዘመናዊ ትምህርትና አዲስ የፖለቲካ አሳብ የማይደግፉ ኃይሎች ሆነው ተከሰቱ ። በመሆኑም በድህረ ምኒልክ ከውጭ የአገሪቱን ቀለበት ዙሪያ የያዙ ኢምፔሪያሊስቶች ከውስጥ ደግሞ የአካባቢ ጉልተኛ መሳፍንቶች ፤ የመሬት ፤ የገባር ፤ የባርያ ፤ የአገር መከላከል ፤ የጉሳ ፤ የቋንቋና የሃይማኖት ጥያቄዎች የኢትዮጵያ ድርብርብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ብሔራዊ ችግሮች ሆነው ተከሰቱ ። በአካባቢ ኢኮኖሚና በግል ጦር ተጠናክረው የተደራጁ ኃይለኛ መሳፍንቶችና ከፍተኛ የጦር ሹማምንቶች እርስ በርሳቸው በሥልጣን አንጃ ተከፍለው በሥልጣን ጉዳይ ሕብረተሰቡን ወደ የእርስ በርስ ጦርነት መሩ ። ዘመናዊ ትምህርትና የአገር ግምባታ ሥራ ተረሳ።